# የትንሣኤው ማኅተም

ዛሬ ጠዋት እዚህ ፊኒክስ በሚገኘው፡ ፉል ጎስፕል ቢዝነስ ሜንስ ማኅበር የልደት በዓል ላይ መገኘት፡ እንዲሁም ጌታ በዚህ ኅብረት ውስጥ ጥቂት ተሳትፎ እንዲኖረኝ፡ እድል እንደሰጠኝ ማወቄ መታደል ነው። ወንድም ካርል ዊሊያምስንና ባለቤቱን፡ ወንድም ስትሮሜይን፡ እዚህ መድረክ ላይ ያሉትን ሌሎችን፡ ወንድም ሾርስን፡ ወንድም አውትሎን፡ አገልጋዮቹንና፡ እናንተን ምርጥ ሕዝቦችን ሁሉ ሰላም እላለሁ።

2 ታውቃላችሁ፡ እ—እኔም፡ ባለፈው ሳምንት ልደቴን አክብሬ ነበር። ከማኅበሩ እድሜ በትንሹ እበልጣለሁ። “ለማህበሩ አምስት ዓመት ከ… እንደሆነው፡” የተናገረ ይመስለኛል።

3 ስሞኑን፡ አንድ ሰው፡ እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ዕድሜህ ስንት ነው? ”

4 እኔም “ሃያ-ስድስት” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “የመጀመሪያዎቹን ሃያ-አምስት ዓመታት ሰርዣቸዋለሁ። በእነዚያ ዓመታት እርሱን በሚገባ አላገለገልኩትም ነበርና” አልኩት። እኔም፡ “እርሱም፡ እንደዚያ እንደሚያደርግ ተስፋ አደርጋለሁ” አልኩ። እርሱ እንዲያደርገው ማድረግ ግን የተለየ ነገር ነው።

5 እዚህ መገኘት ግን መልካም ነው። አሁን ብዙ ጊዜያችሁን መውሰድ አንፈልግም። ምክንያቱም… እ—እንዲህ ያሉ ድንቅ ምስክርነቶችን፡ ዝማሬዎችንና፡ እእየተከናወኑ ያሉ ነገሮችን… ከሰማሁ በኋላ፡ ያንን ድባብ የሚረብሽ ነገር እንዳላደርግ ሁልጊዜ እሰጋለሁ። የሆነ ነገር መጨመር የምችል ከሆነ፡ በእርሱ ላይ ለመጨመር እፈልጋለሁ። እነዚህ እህቶች…

6 ዛሬ ጠዋት ያንን መዝሙር፡ **ዓይኑ በድንቢጥ ላይ ናት** የሚለውን የዘመረው፡ ያ ጥቁር ወንድም፡ ያንን አድንቄዋለሁ።

7 እነዚህ ይህንን መዝሙር የዘመሩትን እህቶች ደግሞ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ከመጣሁ ጀምሮ ካበረቱኝ ነገሮች አንዱ ናቸው። እኔም ያ መዝሙር አለኝ። በሪከርድ አለኝ፡ ደጋግሜም እጫውተዋለሁ፡ **ከእርሱ ጋር ልነጋገርበት እፈልጋለሁ** የሚለውን። ጓደኛዬ፡ ወንድም ዳውሰን ራይሊን፡ ከነዚያ እመቤቶች፡ አንዳንዶች ካሉ፡ አሁንም በምድር ላይ ካሉ፡ ዛሬ ጠዋት ደግመው እንዲዘምሩት ሊያገኛቸው ይችል እንደሆነ ጠይቄው ነበር። ቴሪ እንደቀረጸው ተስፋ አደርጋለሁ። እንደቀረጸውም እገምታለሁ። ያንን መዝሙር በእውነት ስለምወደው፡ ምናልባት፡ በሪከርድ ወይም በሌላ ነገር፡ ከዚያ ልወስደው እፈልጋለሁ። የእኔም… የእኔም መሻት ከእርሱ ጋር መነጋገር ነው። ሁላችንም ያንን ማድረግ የምንፈልግ ይመስለኛል። ዛሬ ጠዋት እዚህ የተገኘነውም ለዚያ ነው።

8 አሁን፡ በሚቀጥለው ሳምንት ስለሚኖሩት፡ ስብሰባዎች ልናገር። ብናገረው ችግር የለውም? [አንድ ወንድም፡ “ተናገር” አለ—አርታዒ።] በ—በሚመጣው ሳምንት፡ በሚቀጥለው እሑድ፡ ለትንሣኤ አገልግሎት፡

ተብርናክል ውስጥ እገኛለሁ፥ ቅዳሜ ምሽት፡ እሑድና፡ እሑድ ምሽት። ከዚያም ወደ ካሊፎርኒያ እመለሳለሁ። በካሊፎርኒያ ዙሪያ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ፡ እዚያ በሚኖረው ስብሰባ ላይ ብትገኙ በእርግጥ ደስ ይለኛል። ቢሊ የተሳሳተ ማስታወቂያ የላከ ይመስለኛል። እንዲህ... እርሱም፡ “በቢልትሞር ሆቴል ይሆናል፡” ብሎ ነበር መሰለኝ፡ “እዚያ ይሆናል” አለ። የ... [አንድ ሰው፡ “ቦታውን ማግኘት አልቻልንም” አለ።] ማግኘት አልተቻለም። ታዲያ በኢስትሞንት ነው? [“ኤምባሲ።”] ኤምባሲ፡ በኤምባሲ ሆቴል። ስለዚህ እዚያ አካባቢ ካላችሁ፡ እዚያ ያሉ የፋል ጎስፐል ሰዎች ያሳውቋችኋል።

9 ከዚያም ከዚያ ተመልሰን፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ እሄዳለሁ። ከዛሬ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንጓዛለን፡ በዚያም በሦስት አገሮች ውስጥ፡ በጌታ ታላቅ ጊዜ ይኖረናል ብለን እንጠብቃለን። ስ—ስለዚህ ጸሎታችሁ እጅግ ያስፈልገናል። ጌታ ፈቅዶ የምንሄድ ከሆነ፡ ተመልሼ እስክመጣ ድረስ፡ ምናልባት ዳግመኛ ላያችሁ አልችል ይሆናል። ስመለስም ታላቅ ዜና ይዤላችሁ እንደምመጣ ተስፋ አደርጋለሁ።

10 ባለፈው ጊዜ እዚያ በነበርኩበት ወቅት፡ ጌታ እስካሁን ካደረጓቸው ስብሰባዎች ሁሉ ታላቁን የሰጠኝ ይመስለኛል። አንድ ጊዜ፡ ለመሠዊያ ጥሪ... አሁን፡ ይህ ገና ባልሰለጠኑት የሃገሪቱ ተወላጆች መካከል በነበረ ስብሰባ ነው። እኔ እንደማውቀው ከሆነ፡ በአንድ ጊዜ ሠላሳ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ክርስቶስን ተቀብለዋል። እኛ ደግሞ ምናልባት የአካል ፈውስ ፈልገው መሰሎን ነበር፡ ምክንያቱም በአንድ ጊዜ ወደ ሃያ-አምስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ተፈውሰው ነበርና። በሚቀጥለው ቀንም፡ የ—የደርባን ከንቲባ ሲድኒ ስሚዝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወደ መስኮትህ ሂድና፡ በመንገዱ ላይ የሚመጣውን ተመልከት፡” አለኝ። እዚያም በምርኩዞችና በመሳሰሉት ነገሮች ተጭነው፡ አንዱ ከአንዱ ተከታትለው የሚሄዱ ቫኖች፡ ይታዩ ነበር፥ እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩት፡ እነዚያ የአገሪቱ ተወላጆች፡ በመንገዱ ላይ ሆነው፡ **እመን ብቻ** የሚለውን መዝሙር፡ በቋንቋቸው እየዘመሩ ይከተሏቸው ነበር።

11 ይኸውላችሁ፡ ልቤ በደስታ ተነካ። ልክ... ወንድም ሾርስ፡ እንዲህ ያለ ነገር ስታይ፡ ያኔ ድካምህ በከንቱ እንዳልሆነ ይሰማሃል። አያችሁ፡ ሞክራችኋል። እግዚአብሔር ይህን ደግሞ እንዲደግመው ተስፋ አደርጋለሁ፡ ይህን የ—የምለው እኛ ወደዚያ ስለምንሄድ ሳይሆን፡ የጌታን መምጣት ስለምንጠባበቅ ነው።

12 መዝሙሩ እንደሚለው፡ ያንን የጠፋውን፡ ትንሹን በግ እየፈለግን ነው፡ ያ... ያ—ያ በግ እስከሚገባ ድረስ እርሱ አይመጣም። እያንዳንዳቸው በበረቱ ውስጥ መገኘት አለባቸው። የመጨረሻዋ በግ እስከምትገባ ድረስ በሩን አይዘጋም። ስለዚህ፡ አገልጋይ ወንድሞቼ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ያቺን የመጨረሻ በግ ለመፈለግ፡ ከእናንተ ጋር አንድላይ እንደማድን እርግጠኛ ነኝ። ምናልባት ዛሬ ጠዋት፡ እዚሁ ፊኒክስ ውስጥ ትሆን ይሆናል፡ አላውቅም። ነገር ግን የመጨረሻዋ ስትገባ፡ ያኔ እረኛው በሩን ይዘጋዋል።

13 [አንድ ወንድም እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም? ”—እርታዒ።] አቤት? [“አንድ ነገር ልናገር? ”] አዎን ትችላለህ። [“አንድ ነገር ረሳሁ። አንድ ነገር እያወራን ነበር... ” በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ።] ምንም ችግር የለውም።

[“አውቃለሁ፡ ሁሉም ሰው አልፎ አልፎ፡ የሆነ ነገር ይረሳል።”] እኔ ግን አልረሳም። [“ኦህ!”]

14 የምናገረውን ሁሉ ማለት ይቻላል፡ መጻፍ ያለብኝ እኔ ነኝ። እኔ… እየሸመገልኩ በመምጣቴ፡ ጥቅሶቼን ለማስፈርና፡ ሌላውንም ነገር፡ ለማስታወስ አስቸጋሪ እየሆነብኝ መጥቷል። ቀደም ሲል፡ ሃምሳ ያህል ጥቅሶችን በአእምሮዬ መደርደር እችል ነበር፡ እንዲያውም ሳልቸገር… በቀጥታ እናገራቸው ነበር፡ ነገር ግን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ብዙ አድካሚ መንገዶችን አልፌአለሁ።

15 ስለዚህ፡ የጌታን መምጣት እንጠባበቃለን። ጌታ ሁላችሁንም ይባርካችሁ!

16 ከዚያም እዚህ ሰወጣ እንዲህ ብዬ አስባለሁ… እዚህ ተቀምጣችሁ እነዚህ ሰዎች ሲመሰክሩ ትሰማላችሁ። “ደህና፡ ሰወጣ፡ ስለዚህ ነገር አንድ ነገር እናገራለሁ፡” ብላችሁ ታስባላችሁ። ከዚያም፡ የሚነገረው ነገር በጣም ብዙ ስለሚሆን፡ ቀኑን ሙሉ ስትናገሩ ብትውሉ እንኳ አይበቃም። ነገር ግን፡ በእርግጥ ሁላችሁንም አደንቃችኋለሁ። ይህች ትንሽ ማኅበር ማደጓን ትቀጥል ዘንድ እመኛለሁ። በፊኒክስ ያለች እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ፡ ማደጓን ትቀጥል ዘንድ የልብ ጸሎቴ ነው።

17 አሁን፡ ትንሽ እንድናርፍ፡ ለጸሎት ብንነሳ፡ ብዬ አስባለሁ። ትነሳላችሁ?

18 ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፡ እርሱን ከሙታን ያስነሳኸው፡ እንደ መሥዋዕት፡ እንደ ጌታና እንደ አዳኝም አድርገህ የሰጠኸን፡ ዛሬ ጠዋት በተቤዡትና ክቡር የሆነውን፡ ለራሱ ሊቀበለን የሚመጣውን ሁለተኛ መምጣቱን፡ በሚጠባበቁት ሕዝቦችህ መካከል፡ በፊትህ ለመቆም ስላገኘነው እድል እጅግ እናመሰግንሃለን። በመካከላችን ኃጢአት ቢኖር፡ ጌታ ሆይ፡ በሂሶጵህ አንጻን። የሰማይ አባት ሆይ፡ በመካከላችን ያለውን የታመመ ሰው ሁሉ እንድትፈውስ፡ እንጸልያለን።

19 ምናልባት፡ በማነኛውም አጋጣሚ፡ ለዚህ ለመጨረሻው ዘመን፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ግዴታ ነው እያልን አንተን የማያውቁህ ቢኖሩ፡ አጥብቀን በምንጋደልለት፡ በዚህ ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ውስጥ ሆነው፡ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ፡ እርሱ በሁላችንም ላይ፡ እንዲወርድ፡ እንደገናም ወደ አካሉ እንዲያጠምቀን፡ በውጭ ያሉትንም፡ ወደ ውስጥ፡ እንዲያመጣቸው እንጸልያለን፡ አባት ሆይ።

20 ቃልህን ስናነብና ከቃልህ የሆነውን እውነት ለመናገር ስንጥር ባርከን። ራሳችንን ለአንተ አሳልፈን ስንሰጥ፡ እውነት ላልሆነው ነገር አፋችንን ዝጋ፡ ለእውነት ለሆነው ግን ልባችንንና አፋችንን ክፈት። አፋችንን ለመናገር፡ ጆሮአችንን ለመስማት፡ ልባችንንም ለመቀበል ተጠቀምበት። እንዲህ እንዲሆን በወሰነው፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

21 ከቅዱስ ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ሦስት ቦታዎችን ላነብላችሁ እወዳለሁ። እነዚህን ምልክት ብታደርጉባቸውና፡ ለተጨማሪ ግንዛቤ፡ ለማንበብ፡ ብትይዟቸው በጣም ደስ ይለኛል። የማነባቸው ክፍሎች ማቴዎስ 28፡1-10፣ ከዚያም ራዕይ 1፡17-18፣ ሮሜ 8፡11 ናቸው። ደግሜ ልጥቀሳቸው። አሁንም ማቴዎስ 28፡1 እስከ10፣ ራዕይ 1፡17 እስከ 18፣ እና ሮሜ 8፡11።

22 አሁን ወደ ትንሣኤ በዓል እየቀረብን ነው። ቦታዎቹን እያወጣችሁና፡ ማስታወሻ እየያዛችሁ ሳለ፡ ይህ የሚመጣው ሳምንት በዓመቱ ውስጥ ካሉት ሳምንታት ሁሉ ይበልጥ ታላቅና ታሪካዊ ሳምንት እንደሆነ አስባለሁ። በዚህ በሚመጣው ሳምንት፡ የምናከብረው ታላቅ ነገር፡ በምድር ላይ ከተከናወኑት ክስተቶች ሁሉ ታላቁ እንደሆነ አምናለሁ። ከእርሱ የሚበልጥ ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም። "እንግዲህ፡ ስ—ስቅለቱ ታላቅ ነበር፡" ትሉ ይሆናል። ነገር ግን በጌታችንም ዘመን እንኳ ሳይቀር፡ ብዙ ሰዎች ሞተዋል፡ ብዙዎችም ተሰቅለዋል። ነገር ግን ከሙታን መካከል የተነሳው አንድ እርሱ ብቻ ነበር። ያም ሁሉንም ነገር አተመው።

23 አሁን ላነብ እፈልጋለሁ። ይህም ጌታ ቢፈቅድ፡ ለአርባ ደቂቃ ያህል የምናየው፡ ትንሽ ቅድመ-ትንሳኤ መልእክት ነው። አሁን ከማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 28፡ ከመጀመሪያው እናንብብ።

> **በሰንበትም መጨረሻ፡ መጀመሪያው ቀን፡ ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።**
>
> **እነሆም፡ የጌታ መልአክ፡ ከሰማይ ሰለ ወረደ፡ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፡ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ፡ በላዩ ተቀመጠ።**
>
> **መልኩም እንደ መብረቅ፡ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ፥**
>
> **ኳከሮቹም... ጠባቆቹም** (ይቅርታ) **እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ፡ እንደ ሞቱም ሆኑ።**
>
> **መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፡** እናንተስ **አትፍሩ፡ የተሰቀለውን፡ ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና።**
>
> **እንደ ተናገረ፥ ተነሥቶአልና፡ በዚህ የለም። የተኛበትን ሰፍራ ኑና እዩ።**
>
> **ፈጥናችሁም ሂዱና፡ ከሙታን ተነሥቷል ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፡ እነሆም፡ ወደ ገሊላ፡ ይቀድማችኋል፥ በዚያም ታዩታላችሁ ብሏቸው፥ እነሆም፡ ነገርኋችሁ።**
>
> **በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ።**
>
> **እነሆም፡ ኢየሱስ፡ አገኛቸውና፡ ደስ ይበላችሁ፡ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው፡** ሰገዱለት።
>
> **በዚያን ጊዜ ኢየሱስ፡ አትፍሩ፣ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፡ በዚያም ያዩኛል አላቸው።**

24 ራእይ፡ ምዕራፍ 1፡ ከቁጥር 17 እና 18።

> **ባየሁትም ጊዜ፡ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ፡ እንዲህም አለኝ፡ አትፍራ፥ ፊተኛውና መጨረሻው፣**
>
> **ሕያውም እኔ ነኝ፡ ሞቼም ነበርሁ፥ እነሆም፡ ከዘላለም፡ እሰከ ዘላለም ድረሰ ሕያው ነኝ፡ እሜን፥** የሞትና የሲኦልም **መክፈቻ አለኝ።**

25 በሮሜ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 8 ላይ፡ ከቁጥር 11 ጀምሮ እናነባለን።

**ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፡ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።**

26 ጌታ ኢየሱስ በእነዚህ ቃላት ንባብ ላይ በረከቱን እንዲጨምር እታመናለሁ። ይህንን በማየት፡ ትንሣኤን፡ በራሴ ልብ ውስጥ የዓመቱ ታላቁ ስብሰባ፡ ወይም ክስተት አ—አድርጌ እትሜዋለሁ።

27 አንድ አፍታ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እፈልጋለሁ። ያ ድምፅ እዚያ ጋር አልጮኸባችሁም፡ እንደ ማንጎዳጎድ? ደህና ነው? እንዲህ ሆኖ በትክክል ይሰማችኋል? ኦህ! አይሰማችሁም። እንዲህ ቢሆን፡ ይሻላል? በጣም መጠጋት አልፈለግሁም ነበር።

28 አሁን፡ ይህንን የምለው፡ ምክንያቱም፡ በትንሣኤ ዕለት፡ እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን ስላረጋገጠ ነው። እርሱ እንዲያደርጋቸው የተጻፉት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት ሁሉ፡ ከሙታን ሲነሳ መሲሕነቱን አተመ፡ ይህም የትንሣኤ ማኅተም ነው። ዛሬ ይህም፡ ስለ ትንሣኤ ማኅተሞች መግዛት፡ ብዙ እናወራለን። እሺ፡ ዛሬ ጠዋት መናገር የምፈልገው፥ ስለ **ትንሣኤው ማኅተም** ነው። በገንዘባችን ከምንገዛው የተለየ ማኅተም ነው፡ በደብዳቤዎች ላይ እንደሚለጠፍ ቴምብር፡ እንደሚመስለኝም፡ እነዚያ የቲዩበርክሎሲስ ማሕበር ወይም ሌሎች እንደሚሉት አይደለም። ይህ ማኅተም ትንሽ ለ—ለየት ያለ ይመስለኛል። እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን ለምንል ክርስቲያኖች ትንሣኤ የዓመቱ ታላቅ ቀን በመሆኑ፡ ወደ ቃሉ ዘልቀን በመግባት ክርስቶስ ለእኛ ካደረገው ከዚህ ታላቅ ነገር ጋር እንዴት ኅብረት ሊኖረን እንደሚገባ ለማየት እሞክራለሁ።

29 የእግዚአብሔር ቃል እርሱ ከመምጣቱ በፊት፡ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት፡ ስለ ስቅለቱ፡ ስለ ሞቱ፡ ስለ መከራው፡ እንዲሁም ስለ ትንሣኤው ተነግሮ ነበር። ምናልባትም፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ የ—የራዲዮ ፕሮግራሞቻችንን ስንሰማ፥ በእነዚህ ላይ አገልግሎቶች ይኖሩናል፥ በቀጣይ ሳምንት፡ በቤተክርስቲያኖቻችን፡ ከፓስተሮቻችን ጋር፡ ወዘተ እናደርጋለን።

30 ነገር ግን ከቀናቶቹ እና ኢየሱስ ካደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለማረጋገጥ ላደረጋቸው ሁሉ በእርግጥ እናደንቃለን፥ ድውያንን መፈወስ፡ ሙታንን ማስነሳት፡ አጋንንትን ማውጣት፡ ለድሆች ወንጌልን መስበክና፡ እርሱ እንደሚመጣ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሁሉ ለመፈጸም፥ ከዚያም አልፎ በእኛ ምትክ፡ ስለ ኃጢአታችን መሠቃየቱን፡ በመስቀል ላይ፡ ለኃጢአት ማስተስረያ መሆኑን፡ ይህም እርሱ ካልሆነ በቀር ሌላ ማንም ሊያደርገው የማይችለውን ነገር ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን፡ ትንሣኤ ሁሉንም ነገር አተመው ብዬ አስባለሁ።

31 ምክንያቱም፡ ከእርሱ በፊት በምድር ላይ፡ ትንቢት የተናገሩ ነቢያት ነበሩ። የታመሙትን የፈወሱ፡ ሙታንን እንኳ ያስነሱና፡ ኢየሱስ ያደረጋቸውን ምልክቶች ያደረጉ፡ ነቢያት በምድር ላይ ነበሩ።

32 ነገር ግን ትንሣኤው ይህንን አረጋገጠው። ለእውነተኛው አማኝ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለዘላለም አተመው። በዚያች ብሩህ ማለዳ፡ ጭንቀትና ጥርጥር ሁሉ ተገፈፈ። ሰው ከዚህች ቀን በፊት፡ በእስር ቤት ውስጥ እንደታሰረ ሆኖ፡ ተዘግቶበት ነበር፡ ለሃይማኖት ሰዎች ሳይቀር፡ ምክንያቱም እ... ታላላቅ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች፡ የመንፈስ ቅዱስን ሥራዎችና፡ የመሳሰሉትን አይተዋል። ሰው ሲሞት፡ ያበቃለት ነበር። ይህኛው መጥቶ፡ “ሕይወቴን ላኖራት ሥልጣን አለኝ፥ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ፡” ባለ ጊዜ ግን፡ የተናገረውንም በተግባር አረጋገጠ፡ ለእኔ፡ የነገሩ ማኅተም ያ—ነው፡ አ—አንድ ነገር ተነግሮ ከዚያም በተግባር ሲረጋገጥ።

33 አንድ ሰው፡ እንደ ኮሎምበስ፡ እሱ ዓለም ክብ እንደሆነች አምኖ ነበር፡ እንደሚነገረንም፡ መርከቦቹ ሲመጡ ሲመለከት፡ መርከቧን ከመመልከቱ በፊት፡ የመርከቧን ምሰሶ ማየት ይችል ነበር። ይህም ዓለም ድቡልቡል መሆኗን አረጋገጠለት። በዚያን ጊዜ ሰዎች ይህን አያምኑም ነበር፡ እርሱ ግን የራእይ ሰው ነበረ። ያየውን ራእይ እውነት መሆኑን፡ በትክክል ለማረጋገጥ ተነሳ።

34 እግዚአብሔርም ቃሉንና እውነቱን፡ ለማረጋገጥ ወሰነ። ስለዚህም... ይህን ሊያደርግ የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበር፡ እርሱም ኢየሱስ ነው። እርሱም መጥቶ ያ እውነት መሆኑን አረጋገጠ። ይህም አተመው። ይህም የጭንቀትን ማኅተሞች ሁሉ ሰበረ፡ የ—የሌሎች ሃይማኖቶችን አጉል እምነቶችና፡ የመሳሰሉትን ሁሉ በታተነ፡ ብዙ ታላላቅ ሰዎች ተነስተው፡ የሚደንቁ ነገሮችን ተናግረዋል፡ ነገር ግን እያንዳንዳቸው፡ በመቃብር፡ ውስጥ ናቸው። የእኛ የክርስቲያን ሃይማኖት ግን ባዶ መቃብር ያለው ብቸኛው ነው። ይህም እርሱ የሙታንና፡ የሕያዋን አምላክ መሆኑን፡ ሙታንንም መልሶ ወደ ሕይወት ማምጣት እንደሚችል፡ ለእኔ ያረጋግጥልኛል። እኔም... ይህ ሕያው የሚያደርግ ኃይሉ፡ ሕያው የሚያደርግ መንፈሱ፡ ሙታንን መልሶ ሕያው ማድረግ የሚችል እርሱ ብቻ መሆኑን፡ ለዘመናት አረጋግጧል።

35 በትንሣኤ ዕለት ይህን ታላቅ የማሸነፍ ኃይሉን፡ በተሰፋው ቃል አረጋገጠ፡ ሞትን፡ ሲኦልንና፡ መቃብርን ድል ማድረግ እንደሚችል አሳየ። “ሞቼ ነበርኩ፡ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ፡ ሕያው ነኝ፥ የ—የሞትና፡ የሲኦልም፡ መክፈቻ አለኝ።” ማ—ማንም ሰው ቢናገረው ምንኛ ታላቅ ንግግር ነው! ይህን መናገር ብቻ ሳይሆን፡ አለኝ የ—የሚለውን ነገር አስቀድሞ በተግባር አረጋግጧል።

36 ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ የምናምን ክርስቲያኖች፡ የምንናገረውን፡ ማረጋገጥ የምንችልበትን፡ ያንን ቀን እግዚአብሔር ያፋጥነው ብዬ እሰባለሁ። አያችሁ? አንዲት እህት፡ ቀደም ሲል እንዳለችው፡ “የምድር ጨው፡” የሚያደርገን ያ ነው። በትክክል። ዓለም ይህንን ጨው እየፈለገች ነው። ሕይወታችን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ያ ቃል ዛሬ ሕያው ለመሆኑ እንደሚያጸና ስናረጋግጥ፡ የምንጠባበቀው ቀን ያው ነው።

37 ቃሉ... “ይህ መንፈስ፡” በሮሜ 8፡11 ላይ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው ይህ መንፈስ በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ ለሚሞተው ሥጋችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጣል” ይላል። እርሱ ይሖዋ ተቤዢ መሆኑንና፡ በሞት፡ በሲኦልና በመቃብር ላይ፡ ሥልጣን እንዳለው ለእኛ ማረጋገጡ ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን

እኛም በዚያው መንፈስ ሕያው መሆናችንን እርግጠኞች እንድንሆን፡ ወደዚያው መንፈስ የምንደርስበትን መንገድ ሰጥቶናል። ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል። አሁን፡ **ሕያው ማድረግ** የሚለው ቃል ትርጉም “ከሞት በኋላ ወደ ሕይወት መመለስ” ማለት ነው። ሕያው የሚደረገው፡ ከሞተ በኋላ ነው።

38 ዓለም እስከዚያ ጊዜ ድረስ፡ ለብዙ ዘመናት በጥርጣሬ ውስጥ ተዘግቶባት ነበር። የተረጋገጠ ነው፡ እንዲሁ በወሬ ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን የተረጋገጠ ነገር ነው። ጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ነገር ቢኖር...

39 ኢየሱስ፡ “እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፥ የእግዚአብሔርን ኃይል በተግባር በማሳየትም፡ አረጋግጡላቸው። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል” አለ። ቃል የገቡትንና እናምናለን የሚሉትን፡ ግልጽ የሆነ መረዳትን ሰጥቶናል፡ ይህም፡ “እነዚህ ምልክቶች ያመኑትን ይከተሏቸዋል” አለ። ይህም ለምስክርነታቸው ማስረጃ ይሆናል። አሁን እናምናለን ልንል እንችላለን። ነገር ግን እርሱ በእኛ ላይ ይሆናል ያለው የተረጋገጠ ምልክት እስከሚኖረን ድረስ፡ አማኞች ነን ብለን **ከመናገር** ባለፈ፡ የአማኞች **ድርሻ** የለንም።

40 ምክንያቱም፡ አስታውሱ... ከጥቂት ቀናት በፊት፡ በቱሰን በኬኤአይአር ሬዲዮ ላ—ላይ አንድ ፕሮግራም አዳምጥ ነበር። ይህ ሰባኪ በእኛ ላይ ተነስቶ እንዲህ ይል ነበር፡ ይህም፡ “የጴንጤቆስጤ ሃይማኖት ከማታለል በቀር ምንም አይደለም። ይህም... አትስሙት። የማይረጋጋ ነው” አለ። እንዲህም አለ፡ “በልሳን የሚናገር፡ እነዚህን ነገሮች፡ የታመሙትን፡ በጸሎት እፈውሳለሁ የሚልና፡ የመሳሰሉትን ከሚናገር፡ ማንኛውም ሰው፡ ከእርሱ መራቅ ያስፈልጋል። በእነዚያ ቅዠት ውስጥ ባሉ፡ ምስኪን ደካማ ሰዎች ላ—ላይ፡ የሆነ ችግር ስላለባቸው ጸልዩላቸው” አለ። ኦህ፡ ያንን ወንድም ለጥቂት ጊዜ ማነጋገር በቻልኩ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር! እርሱም እንዲህ አለ... “ያ፡ ለሐዋርያት በጰንጤቆስጤ ቀን ብቻ የተሰጠ ነበር፡ ያ ነው በቃ” አለ።

41 ከሰላሳ ዓመታት በኋላም፡ ጳውሎስ እነዚህን ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓት ሲያስይዛቸው፡ ደርሼበታለሁ። በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡ ላይ፡ “እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳን የመናገር ስጦታን፡ ተአምራትን አኖረ። እነዚህም ሌሎች ስጦታዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠዋል” ይላል።

42 ኢየሱስም እንዲህ አለ። “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።” እስከ የት? “ወደ ዓለም ሁሉ።” ለማን? “ለፍጥረት ሁሉ።” እስካሁንም ገና አልተቀበሉትም። “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።” እስከ የት? “በዓለም ሁሉ።” ለማን? “ለፍጥረት ሁሉ። እነዚህ ምልክቶች፡ በዓለም ሁሉና፡ በፍጥረት ሁሉ መካከል ያመኑትን ይከተሏቸዋል። እነዚህም ምልክቶች ይከተሏቸዋል፣ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፥ በአዲስ ልሳን ይናገራሉ፥ የሚገድልም ነገር፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፥ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ።” ይህም በማርቆስ ምዕራፍ 16 ላይ የተጠቀሰው፡ የእርሱ የመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ነበር።

43 ጳውሎስ ከሰላሳ ዓመታት በኋላ፡ እነዚህን ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሾመ ነበር። በገላትያ 1፡8 ላይም፡ እንዲህ አለ፡ “ከሰማይ የመጣ መልአክ ቢሆን እንኳ አስቀድሞ ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፡” እያችሁ፡ አስቀድሞ ተሰብኳል፡ “የተረገመ ይሁን።” የጴንጤቆስጤ ፍጻሜ የሌለው ሆኖ እንደጀመረ አምናለሁ። ለፍጥረት ሁሉ፡ በሁሉም ዘመንና፡ በሁሉም ስፍራ፡ የጴንጤቆስጤ ሁልጊዜ ሊቀጥል እንደሚገባ አምናለሁ። የጴንጤቆስጤ በረከቶች በሕዝቡ ላይ ሊሆኑ ይገባል።

44 አሁንም፡ ይህ የጴንጤቆስጤ በረከት ምንድን ነው? እርሱ የትንሣኤው ማረጋገጫ ነው። “ወንጌል” የሚለው ቃል ራሱ “የምሥራች” ማለት መሆኑ አይደንቅም። የምሥራች ስለ ምን? እርሱ ከሙታን ተነስቷል። “እኔ ሕያው ስለሆንኩ፡ እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።” ቀድሞ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን የነበራችሁ እናንተን፡ ኢየሱስን ከሙታን ባስነሳው በዚያ መንፈስ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር፡ አብሮ ሕያው አደረገን። አሁንም ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል፡ ከእርሱ ጋር ኅብረት እያደረግን ነው፡ እያወራነው ነው። ይህን ታሪክ እውነት ነው ብለው ለሚያምኑ ሰዎች፡ መንገር ምንኛ ደስታ ነው!

45 ዛሬ፡ አስባለሁ። እየሆነ ያለው ነገር ይህ ነው። ሰዎችን በእውነት ወደ እግዚአብሔር እያመጣናቸው ነው፡ ወይስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ? ይህ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ወዳለበት፡ ወደ ክርስቶስ ልናመጣቸው ይገባል። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ መልካም ነው። እርግጥ ነው። ነገር ግን መድረሻችን እዚያ ብቻ ከሆነ፡ በቂ አይደለም። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትመጡ፡ ጥሩ ነው፥ ነገር ግን ከቤተ ክርስቲያን፡ ወደ ክርስቶስ ቀጥሉ፡ ምክንያቱም በዚያ አጠቃላይ ትንሣኤ ውስጥ ለመገኘት የምንጠባበቅ ከሆነ፡ ይህን ሕያው የሚያደርግ ኃይል መቀበል አለብን፡ ከሙታን ሊያስነሳን የሚችል ብቸኛው ነገር እርሱ ነውና። “ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ያ መንፈስ በእናንተ ቢኖር፡ ለሚሞተው አካላችሁ፡ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል፡ ሕያው ያደርገዋል።” ምንኛ ታላቅ ተስፋ ነው!

46 አሁን አስተውሉ። የዚህ ትንሣኤ ዋናው ይዘት ኢየሱስ ከሙታን መነሳቱን መናገር፡ ማሳየትና ማረጋገጥ ነው። እርሱ አልሞተም። ሕያው ነው። እዚህ ይኖራል። በእኛ ውስጥ ነው። “ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ እንዲያውም በውስጣችሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም አያየኝም። እናንተ ግን፡ ታዩኛላችሁ፡ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር፡ እንዲያውም በውስጣችሁ እሆናለሁና።”

47 አሁን፡ እንደ ክርስቲያኖች፡ ሁላችንም እርሱ ሕያው እንደሆነ፡ ወይም በመንፈሱ—ከሞት ወደ ሕይወት... ሕያው እንደሆንን፡ እንመሰክራለን። ሕያው ካልተደረግን ደግሞ፡ ሕያዋን አልሆንንም።

48 አሁን ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደዚህ ርዕስ እንገባለን፡ ለጥቂት ደቂቃዎችም እናስተምራለን፡ ይህም፥ ሕያው ተደርገናልን፡ ይህ እውነት ለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን?

49 አሁን፡ ይህ የአንተ ሕይወት ነው፡ ይህ የእኔ ሕይወት ነው። ይህን ነገር... አሁን ልናገር ያለሁት ነገር፡ እውነት ካልሆነ፡ እኔ በዓለም ላይ ካሉ ሞኙ ሰዎች አንዱ ነኝ። ሕይወቴን ለከንቱ ነገር ሰጥቻለሁ ማለት ነው፡ እናንተም እንዲሁ።

ነገር ግን እውነት ከሆነ፡ ላሆንኩበት ሁሉ ባለዕዳ ነኝ። ለቆምኩለት ዓላማ፡ ለምሆንለት ሁሉ፡ ባለዕዳ ነኝ። ትጋታችንንም ልናጣ አይገባም ብዬ አስባለሁ።

50 የትንሣኤ በዓል ሲቃረብ ስመለከት፡ በውስጤ የሆነ ነገር ይሰማኛል፡ ያ—ያ ቀን በእግዚአብሔር ፊት፡ ነገሩ ለዘላለም የታተመበት ቀን እንደሆነ አውቃለሁና።

51 አሁን፡ እርሱን ከመቃብር ያስነሳው ያው መንፈስ፡ በእኛ ውስጥ እንደሚኖር፡ እናስተውላለን። አሁን፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር፡ ኢየሱስን፡ ከሙታን ያስነሳበት ያ መንፈስ፡ በእኛ ውስጥ ይኖራል።

52 አሁን፡ አሁን፡ ሕያው የሚያደርገው መንፈስ ነው። ሕያው የሚያደርገው ቃሉ አይደለም። ቃሉን ሕያው የሚያደርገው፡ ወይም ለቃሉ ሕይወትን የሚሰጠው፡ እንዲበር ክንፍ የሚሰጠው፡ መንገድ የሚከፍትለት መንፈስ ነው። ይህን የሚያደርገው መንፈስ ነው።

53 አሁን፡ ስንዴ፡ በራሱ፡ ስንዴ ብቻ ነው፥ ነገር ግን ያ ሕያው የሚያደርገው ሕይወት፡ ወደ ስንዴው ውስጥ ሲገባ፡ ሕይወትን ይሰጠዋል። እኛም ቀድሞ ሙታን የነበርን፡ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን፡ በኃጢአትና በበደል ሙታን ነበርን፡ እግዚአብሔር ይህን ሕያው የሚያደርግ ሕይወት ወደ እናንተ ሟች አካል ውስጥ የሚያስገባበት የሆነ መንገድ ነበረው። ስለ አካላችሁ እያወራሁ ነው።

54 አሁን፡ ኢየሱስ ቃሉ ነበረ። ይህን ታምናላችሁ፡ አይደል? "በመጀመሪያ... " በዮሐንስ 1 ላይ፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።"

55 አሁን፡ እርሱ እንደተሰፋው መሲሕ፡ እንዲያደርጋቸው ትንቢት የተነገረባቸውን ቃላት ሁሉ ሕያው አደረገ፡ የታመሙትን መፈወሱ፡ ከድንግል መወለዱ፡ ያን ሁሉ፡ ፈጸመው። እውነት ነው። እርሱ እዚህ ምድር ላይ የተገለጠው፡ ቃሉ ነበር፡ ነገር ግን ይህንን እንዲሁ እንደ ሰው ብቻ ሊያደርገው አልቻለም። እነዚህን ተሰፋዎች ለእርሱ ሕያው ለማድረግ፡ በእርሱ ውስጥ የሚኖረው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አስፈላጊ ነበር። አሁን ይህ በደንብ ግልጽ እንዲሆንልን ተሰፋ አደርጋለሁ። ኢየሱስ፡ ራሱ፡ ሰው እንደመሆኑ፡ አካሉ፡ ሆኖም በእርሱ ውስጥ ያለው መንፈስ፡ መንፈሱ አስፈለገ። "ሥራውን የሚሠራው እኔ አይደለሁም። በእኔ የሚኖረው አባቴ ነው እንጂ። ሥራውን የሚሠራው እርሱ ነው" አለ። አያችሁ? ኢየሱስ ራሱ ቃሉ ነበረ፡ ምክንያቱም እርሱ... በእግዚአብሔር ፊት...

56 ይህ በሕዝብ ፊት ለመናገር፡ ትንሽ አስቸጋሪ ቃል ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን በትክክል እንደምትረዱት ተሰፋ አደርጋለሁ። እርሱ በእግዚአብሔር አስቀድሞ በማወቅ የተወሰነ ነበር፡ የእግዚአብሔር ዕቅድም፡ ቤዛን መላክ እንደነበር፡ ይህ ቤዛም ልጁ ብቻ ሊሆን እንደሚገባ ነበር። ስለዚህ፡ ያኔ፡ ኢየሱስ እዚህ እንደሚመጣ፡ ከኤደን ገነት ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር ተሰፋ ነበር። ከድንግል የተወለደ፡ ሰው ሆኖ እዚህ ነበር፡ ነገር ግን ያንን ቃል በእርሱ ውስጥ ሕያው ለማድረግ የእግዚአብሔር መንፈስን ፈለገ። እርሱም ለዚያ ዘመን፡ ሕያው የሆነ፡ የተገለጠ ቃል ነበረ። ቤዛ የሚያስፈልግበት ጊዜ ደርሶ ነበር። ሕጉ አልተሳካለትም ነበር። ሌሎችም ነገሮች አልተሳኩም ነበር። አሁን፡ ቤዛ

ያስፈልጋል፡ እርሱም የተሰፋው ቤዛ ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ሕያው የሆነ ነበር።

57 አሁንም በዚያ ዘመን ቤዛ እንዲሆን በእርሱ ላይ የነበረው ያው መንፈስ፡ በእነዚህ በመጨረሻው ዘመን ምን እንደሚፈጠር የተሰጠውን ተስፋ አሁን ከተቀበልን፥ የእርሱ የቃሉ ክፍል ከሆናችሁ፡ ከእርሱ ጋር ተቤዥታችኋል፡ ምክንያቱም በክርስቶስ የነበረው ያው መንፈስ በእናንተ ውስጥ እየኖረ፡ ሕይወታችሁን ለዚህ ዘመን ሕያው እያደረገው ነው። በመጨረሻውም ዘመን፡ ሟች ሰውነታችሁን ሕያው ያደርጋቸዋል፡ ያስነሳቸዋል፡ መልሶም፡ ያመጣቸዋል። ይህንን ስንመለከት ጨለማውን ያሰወግድልናል። ይ—ይህም እውነት ነው። አያችሁ?

58 ሮሜ ላይ፡ ጳውሎስ ይህን አረጋግጦልናል። አያችሁ? "ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፡ ለሚሞተው ሥጋችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጣል።" ይህ እርሱን ያስነሳው፡ እውነተኛውን እማኝ ለዘላለም ሕይወት ያስነሳው ያው መንፈስ ነው። ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ በአማኙ ውስጥ ይኖራል፡ አማኙንም ለዘላለም ሕይወት ያስነሳዋል።

59 አንድ ሕይወት ብቻ፡ አንድ የዘላለም መንፈስ፡ አንድ የዘላለም ሕይወት አለ፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር፡ ብቻ ነው፡ ዘላለማዊ። እኛም፡ ልጆቹ ስለሆንን፡ የእርሱ ክፍል ነን፡ ማለትም፡ የእርሱ ሐሳብ መገለጫዎች ነን። ሐሳብ ሲገለጥም ቃል ይሆናል። ስለዚህ፡ በዚህ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ፡ ይህ የዘላለም ሕይወት ያለው፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ ነበር። ይህ ሊሆን የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡ ምክንያቱም እናንተ የእርሱ መገለጫዎች ናችሁ። ያ የሐሳብ መገለጫ፡ ቃል ሆነ፥ ቃሉም ሕይወትን አገኘ፡ ዘላለማዊም ነው። የዘላለም ሕይወት ያለንበት ምክንያት ይህ ነው። ታላቁ የእግዚአብሔር ልጅና ቤዛው፡ በሆነበት በዚያው መርህ፡ እኛም በዚያው መንፈስና፡ በዚያው በእግዚአብሔር አስቀድሞ በማወቅ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንሆናለን።

60 ኢየሱስ እዚህ በነበረበት ጊዜ ይህንን ያልተቀበሉትን በምድር ላይ ያሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ተመልከቱ። ነገር ግን በዚያ ታላቅ የትንሣኤ ጥዋት፡ በዚያ ታላቅ ፋሲካ ውስጥ እንደምንካተት፡ ቀጥተኛ ማስረጃና የመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ እንዳለን በማወቃችን ዛሬ ጥዋት ምንኛ አመስጋኞች መሆን አለብን! አሁን በዚህ ሟች አካላችን ውስጥ፡ የእርሱ መያዣ አለን። መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆኑትን ለመውሰድ በሚመጣበት ጊዜ፡ በእርግጥም፡ መጀመሪያ ሕያው የሚደረጉት፡ አስቀድመው የተወሰኑት ናቸው።

61 አሁን፡ አንድ ታላቅ ነገር ልናገር ነው፡ አገልጋይ ወንድሞቼም ይህንን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ። አያችሁ? በመጀመሪያ፡ ታላቁ መንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ያኔ "አምላክ" እንኳ አልነበረም። እርሱ ብቸኛው ዘላለማዊ ነበረ። **አምላክ** ማለት "የሚመለክ ነገር" ማለት ነው። የሚያመልከው ምንም ነገር አልነበረውም። መ—መላእክትም ሆነ፡ ምንም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ብቻውን፡ እርሱ ብቻውን፡ ዘላለማዊ ነው። ነገር ግን፡ አምላክ ለመባል፡ የሚያመልከው ነገር ሊኖር ይገባ ነበር፡ ስለዚህ ያመልኩት ዘንድ፡

መላእክትን፡ ፍጥረታትን፡ ኪሩቤልንና፡ ሌሎችንም ፈጠረ። ያ ታላቅ ዕቅዱም መገለጥ ጀመረ።

62 ነገር ግን አስታውሱ፡ ዛ—ዛሬ ጠዋት፡ ባላችሁበት በዚህ ደረጃ፡ ያኔ በሃሳቡ ውስጥ ካልነበራችሁ፡ አሁንም የላችሁም። ምክንያቱም ለእናንተ፡ በእናንተ ውስጥ ያለ የሆነ ክፍል አለ፡ እርሱም ዘላለማዊ ነው፡ ዘላለማዊነትም የእግዚአብሔር ብቻ ነው። አሁን እዚያው በተቀመጣችሁበት ስፍራ እንደምትቀመጡ እግዚአብሔር አስቀድሞ በሃሳቡ ያውቃችሁ ነበር። እርሱ ወሰን የሌለውና ሁሉን የሚያውቅ ስለሆነ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ መድረክ ላይ እንደምቆም፡ በሃሳቡ ነበር። ስለዚህ እርሱ ዘላለማዊ ስለሆነ፡ መጨረሻውን ከመጀመሪያው መናገር ይችላል። እናንተም፡ የእግዚአብሔር ወንድ ወይም ሴት ልጅ በመሆናችሁ፡ በመጀመሪያ በሃሳቡ ውስጥ ነበራችሁ።

63 ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በሚመጣበት ጊዜ፡ እናንተም እዚህ ምድር ላይ፡ እንደ ኃጢአተኛ እየተመላለሳችሁ ሳላችሁ፡ ነገር ግን በሕይወታችሁ ውስጥ የሆነ ነገር አለ። ምን እየሆነ እንደሆነ አታውቁም፡ ነገር ግን ትራባላችሁ። ያ የፕሬስቢቴሪያን ወንድም ሲናገር ሰምቻለሁ፡ የ—የባፕቲስት ወንድምም፡ እዚያ ኋላ ሆኖ ሲናገር ሰምቻለሁ፡ እርሱ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚሰብክ፡ ፍ—ፍሪዊል ባፕቲስት ነበረ። ወንድሜ ሆይ፡ በአንተ፡ የሆነ ነገር አለ፡ አንተ እራስህ ያላስቀመጥከው የሆነ ነገር አለ። እዚያ እንዲኖር መፈለግ እንኳ የማትችለው ነገር። ከገዛ ተፈጥሮህ ጋር የሚቃረን ነገር። ይህም የእግዚአብሔር ቃል፡ የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅን፡ መፈጸም ነው።

64 ኢየሱስ አማኑኤል ይሆን ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እንደተወለደ፡ ይህም እግዚአብሔር በአንድ ሰው ውስጥ ያለው ሙሉ መግለጫ ነው። በዮርዳኖስ ወንዝም፡ በዚያ ነቢይ ሲጠመቅ፡ እግዚአብሔር ፍጹም በሆነ ታዛዥነት አገኘው። እርሱም በታዘዘውና፡ ከውሃው በወጣ ጊዜ፡ ሰማያት ለዮሐንስ ተከፈቱ። መንፈስ ቅዱስም፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው” እያለ፡ ከሰማይ ሲወርድ አየ። አያችሁ? ፍጹም ታዛዥነት፡ መንፈሱ በታዛዥነት ውስጥ፡ አገኘው።

65 ኦህ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ዓመፀኛ ወንድ ወይም ሴት፡ እዚህ ተቀምጣችሁ ሳላችሁ፡ በውስጣችሁ ይህ ትክክል እንደሆነ የሚነግራችሁ የሆነ ነገር ካለ፡ መንፈስ ቅዱስ እየፈለጋችሁ መሆኑ ነው፡ ይህም ስላለፈው ዘመን ሳይሆን፡ አሁን ስለምንኖርበት፡ ስለ አሁኑ ሰዓት እውነት ወደ ማወቅ ሊያመጣችሁ ነው።

66 ያለፈውን ዘመን ሲታዘዙ የነበሩ በሺዎች የሚቆጠሩ እዚያ ነበሩ። ነገር ግን ኢየሱስ ሊገለጥበት የነበረው፡ የአሁኑ-ጊዜ ሰዓት ነበረ፡ ቃሉም እዚያ ቆሞ ነበር። ሕዝቡም እዚያ ነበሩ። ያ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥም፡ የእግዚአብሔር መገለጥ እዚያው ይከናወን ነበር።

67 ዛሬም፡ እንደ ጴንጤቆስጤ ሕዝብ፡ ይህን ልናገር፡ እግዚአብሔር መንፈሱን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እንደሚያፈስ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት እንደሚናገሩ ቃል በገባበት፡ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት ውስጥ ቆመናል። እርሱም፡ “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል” ብሏልና። ዘመኑ አሁን ነው። በውስጣችሁም ያንን አዲስ ፍጥረት የሚፈጥረው ያ ነው።

68 በቅርቡ፡ እዚህ ሰናገር፡ ትንሽ እንደ አጉል መንፈሳዊነት መሰሎ ነበር፥ ነገር ግን ዛሬ ጠዋት፡ ለእናንተ፡ እንደዚያ እንደማይሆን ተሰፋ አደርጋለሁ። ንሰርን፡ ወይም ዶሮን ያስታቀፈውና፡ የንሰር እንቁላል የነበረው ገበሬ ታሪክ። ብዙዎቻችሁ የዚህችን የወለደች ንሰር—ታሪክ ታስታውሳላችሁ... ወይም፡ ዶሮ ጫጩቶችን ስትወልድ፡ ወ—ወ—ወይም የንሰር እንቁላል በዶሮዋ ላባ ስር ሆኖ ስትፈለፍል። አያችሁ? ዋናው ድባብ ነው።

69 የፕሬሰቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን፡ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን፡ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን፡ ማንኛቸውም ቢሆኑ እነዚህን ንሰሮችን ሊያመጡ ይችላሉ። እርግጥ ነው። ይህን የሚያደርገው ድባቡ ነው። ዶክተር ቦሰወርዝ እንዲህ ይል ነበር፡ “የዶሮ እንቁላል ወሰደህ... ቡችላ ስር ብታደርገው፡ አሰረህ ብታቆየው፡ ቡችላው ጫጩት ይፈለፍላል።” ለምን? ድባቡ ስለሆነ ነው። ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ማንኛውም ቡድን ተሰብሰበው፡ የሃይማኖት መግለጫቸውንና መሰል ነገሮቻቸውን ጥለው፡ ቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት እስኪመለከቱ ድረስ ቢጸልዩ፡ ልክ እኔ እዚህ መቆሜ እርግጥ እንደሆነ ሁሉ በእርግጠኝነት ንሰሮችን ይፈለፍላሉ።

70 ይህ የቢዝነስ ሜን ቡድንም እያደረገ ያለው ይህንኑ ይመሰለኛል፡ ድባቡን ለመለወጥ እየሞከሩ ነው። በጣም ጎጠኞች እየሆንን ነው። አንዱ **የዚህ** ነው **ሌላው** የዚያ ነው። እሰቲ ድባቡን እንሰበረውና ወደ ሰማያዊ እምልኮ ድባብ ውሰጥ እንግባ። ድባቡን አሰተካክሉት፡ ያኔ ንሰሮች ይወለዳሉ፡ ከ—ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን፡ ከየትኛውም ቦታ ይወለዳሉ።

71 ይህ ትንሽ ንሰር ከዶሮዋ ጋር ለረጅም ጊዜ ተመላለሰ፡ ነ—ነገር ግን ጩኸቷ ለእርሱ እንግዳ ነገር ነበር። በግቢው ውሰጥ ባለው የፍግ ክምር ቆሻሻ ው—ውሰጥ ሰ—ሰትጭር ምን ማለቷ እ—እንደሆነ አልገባውም ነበር። ለእርሱ፡ ያ ምግብ አልነበረም። እርሷም ንሰር የማይበላውን፡ ትልና፡ የመሳሰሉትን ትበላ ነበር። ሰለዚህ፡ ሁሉም ነገር፡ ለእርሱ እንግዳ ሆኖበት ነበር። እርሱም እንደ አሰቀያሚ ዳክዬ፥ እንደዛ ነበር፡ ይህንን የምለው አጉል መንፈሳዊ ለመሆን አይደለም፡ ምናልባት የፍሪዊል ባፕቲሰት፡ ወይም፡ እንደዚህ ያለ ነገር፡ ወይም የፕሬሰቢቴሪያን ነበር።

72 ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ አንድ ቀን እናቱ የሆነ ቦታ እንቁላል ጥላ እንደነበር ታውቃለች። ልጇ በሆነ ቦታ ሊኖር እንደሚገባ ታውቅ ነበር። ሰለዚህ ታላላቅ ክንፎቿን ወደ ንፋሱ ዘርግታ፡ በሙሉ ድምፅዋ እየጮኸች፡ ደጋግማ ፈለገች። አንድ ቀን፡ በበረት ግቢ በላይ አለፈች። ትንሹ ንሰር የራሱን ዓይነት ድምጽ በሰማ ጊዜ፡ ከዚህ በፊት ሰምቶት ባያውቅም፡ ነገር ግን ለእርሱ ልክ እንደ ጓንት በእጅ ላይ እንደሚገጥም ሆኖ ተሰማው። እናቱ እንደሆነች አወቀ። እርሷም ልጇ እንደሆነ አወቀች። እየፈለገችው ነበርና።

73 እግዚአብሔርም፡ በእያንዳንዱ ዘመን፡ ቤተክርስቲያኑን ለዚያ ዘመን፡ ለዚያ ዘመን መልእክት አድርጎ ይወሰናል። እነርሱም የፈለጉትን ሕግና ማንኛውንም ነገር ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ያ ዘመን ሲመጣ፡ በመጀመሪያ ለዚያ ዘመን የታሰበውና የተነገረው፡ የእግዚአብሔር መንፈሰ ቅዱስ፡ ያ መንፈሰ ያንን እንቁላል ይፈልገዋል። ያንንም መልእክት ሲሰማ፡ የትኛውም የሃይማኖት ተቋም ሊይዘው አይችልም። ወደ ከፍታው ይወጣል። መውጣትም አለበት።

ምክንያቱም እርሱ የተለየ ወፍ ነው። የተለየ ፍጥረት ነው። እርሱ ንሰር ነው፡ ጩኸቱንም ይሰማል። “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ።”

እንድ ሰው እንዳለው፡ ወንድም ዊሊያምስ እንዳለው፡ “የበጎች ምግብ” ነው።

74 “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ። እንግዳን አይከተሉም።” ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ታማኝ ብትሆን፡ ወይም ምንም ያህል ትልቅ ሰም ቢኖራት ግድ የለውም። “በጎቼ ድምፄን ሲሰሙ፡” ይህም ቃሉ የሆነውን ሲሰሙ፡ “እንግዳ አይከተሉም።” በቀጥታ ወደዚያ ቃል ይሄዳሉ፡ ይህንንም ማድረግ ይችላሉ። ል—ል—ልክ እንደ ማግኔት ነው።

75 አንድ ቀን፡ በኢንዲያና የሚገኙ፡ የብረት ፋብሪካዎችን እየጎበኘሁ ሳለ፡ ፊሽካ ተነፋ። ሁሉም ሰው አፕሮኑን አውልቆ፡ በቀኑ ውስጥ የፈጠሩትን... የብረት ቁርጥራጭ፡ ከመቅረጫ ማሽኖቻቸው ስር፡ ወደ ወለሉ መሃል መጥረግ ጀመሩ። እኔም በፋብሪካው ውስጥ ከሚመራኝ ሰው ጋር እየተጓዝኩ ሳለ፡ “ይህን ተመልከት፡” አለ። ሰ—ሰለዚህ እያንዳንዱ ሰው የሥራ ልብሱን በ—በጠረጴዛው ላይ አኖረና፡ ወጣ።

76 ከበስተጀርባ በኩል፡ አንድ ትንሽ ቁልፍ ነካ። ያኔም አንድ ትልቅ ማግኔት መጣና፡ ከእነዚያ ቁርጥራጮች ላይ የተፋቀውን፡ የብረት ፍቅፋቂዎች ሁሉ ለቅሞ፡ ይዞ ወጣ። ማግኔትነቱ መሳቡን ሲያቆም፥ ቁርጥራጮቹ ወደ ማቅለጫው ውስጥ ወደቁ። ከዚያም ልክ እንደ ቀድሞው ዓይነት፡ እንደገና ለ—ለሌላ ዕቃ፡ ለአክሰል ወይም ለሚሠሩት ለማንኛውም ነገር እንዲሆን፡ ቀለጡ።

77 እ—እኔም ራሴን እስክረሳ ድረስ፡ ቆሜ ይህንን እመለከት ነበር። እኔም “አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ” አልኩ።

እርሱም፡ “ምንድን ነው፡ ጌታዬ” አለኝ?

እኔም፡ “እንዳንዶቹ ወደ ላይ እንዳልወጡ አስተውያለሁ” አልኩት።

78 እርሱም፡ “እነርሱ አሉሚኒየም ሰለሆኑ ነው፡ ማግኔቱም አሉሚኒየምን የመሳብ ባህሪ የለውም” አለኝ።

79 እኔም፡ “ገባኝ” አልኩ። እሱም እንዲህ አለ... ከዚያም፡ “እንግዲህ፡ ካስተዋልክ፡ አንዲት የብረት ቁራጭም **እዚያ** ተኝታ ትታያለች” አልኩት።

“ነገር ግን፡ አየህ፡ ጌታዬ፡ እርሷ እኮ በቦልት ተቸንክራ ነው” አለኝ።

80 እኔም፡ “ገባኝ” አልኩ። ይዞት ሲወጣም፡ “ታዲያ **በ**ውጭ ያለውስ፡ ምን ይሆናል፡” አልኩት?

81 እንዲህም አለ፡ “ተመልሶ ወደ ፋብሪካው ይገባል፡ በማቅለጫው ውስጥ ፈስሶ፡ ተመልሶ ሌላ ጎማ ሆኖ ይወጣል” አለ።

እኔም “ጌታ ይመስገን!” አልኩ፡ ያ ነው በቃ። አያችሁ?

82 አንድ ቀን እግዚአብሔር በጣቶቹ የሚነካው፡ በሰማይ የተቀመጠ አንድ ታላቅ ማግኔት አለ። የሚመጣበትን ጊዜ ማንም አያውቅም፡ የሰማይ መላእክትም እንኳ፡ አያውቁትም። እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው። ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች፡ ለዚህ ሰዓት አማኞች ከሆኑት መካከል የወጡ አንዳንድ ቁርጥራጮች አሉ። አንዱ በሌላ

ዘመን ኤክሰል የነበረ ይሆናል። **ይህ** ደግሞ ሌላ ክፍል ሊሆን ይችላል። ታላቁን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመፍጠር ሥራው እየቀጠለ ነው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ታላቅ ማቅለጫ ውስጥ ይቀረጻል፡ እንደገናም ወደ እግዚአብሔር አምሳል ይፈስሳል። ወደ እርሱ የሚሳቡት ብቻ ወደ ላይ ይወሰዳሉ። ኦህ፡ እንዴት… በትንሣኤ ውስጥ እኛን የሚመለከት ነገር እንዳለ ማወቅ፡ ምንኛ መታደል ነው!

83 አሁን፡ አስተውሉ፡ እርሱ የዚሁ አካል የሆነበትን፡ የእግዚአብሔርን ቃል ጥሪ ይገነዘባል። ነገሩ ንስር ለንስር ነው። አሁን፡ ያቺ እናት እ—እንደ አሞራ ብትጮህ ኖሮ፡ ፈጽሞ አያውቃትም ነበር። በበረቱ ውስጥ ቢቆይም ምንም አይመስለውም ነበር። ነገር ግን ጩኸቱ የንስር ጩኸት ነበር። በዚያ ትንሹ ፍጥረት ውስጥ፡ ንስር መሆኑን የሚያውቅበት የሆነ ነገር በውስጡ ነበረ።

84 ለእያንዳንዱም እውነተኛ አማኝም ነገሩ እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሰብከት ሲወጣና፡ ለዚህ ዘመን የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ሲረጋገጥና ሲታወቅ፡ ያኔ በአማኙ ውስጥ የሆነ ነገር አለ። አባቱ ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ታማኝ ቢሆን፡ ወይም እናቱ፡ ወይም አያቶቹ፡ ያች ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መልእክት ጋር ተቃራኒ የሆነ ነገር ብታስተምርም ግድ አይሰጠኝም። በውስጡ የሚጮህ የሆነ ነገር አለው። በረቱን ትቶ ይወጣል። ይህን ማድረጉ አይቀሬ ነው። ዶሮ መሆን በአንድ ወቅት ጥሩ ነበር ይሆናል፡ አሁን ግን የንስር ዘመን ነው። አያችሁ? የ—የተለየ ነው። ይህም፡ ያንን አሮጌ የዶሮ ቤት ትቶ ወደ ሰማያዊው አየር መብረር ያለበት፡ የሆነ ነገር አለ። ያኔ ይህ ምድራዊ አካል፡ ሕያው በሚያደርገው መንፈስ፡ ሕያው ተደርጎ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥነት ይቀርባል።

85 አሁን፡ በንስር የተወከለው፡ ይህ መንፈስ ቅዱስ፡ በምድሪቱ ላይ እየበረረ፡ አማኙን ሲያገኝ፡ “ማንም ሊመጣ አይችልም፡ እርሱ ካልፈለገ በስተቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም፡ አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣሉ፡ ነገር ግን ማንም በራሱ ሊመጣ አይችልም፡” ይህም የእናንተ አሳብ፡ ወይም የእናንተ መሳብ ሳይሆን፡ እግዚአብሔር፡ ሲስባችሁ ነው። አያችሁ? “አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።”

86 አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ እዚህ ምድር ላይ ነው፡ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ለሕይወት የወሰናቸውን ግለሰቦች እየፈለገ ነው። እንዳገኛቸውም፡ ሁላችንን በቤዝን በዚያ ታላቅ የእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዳደረገው ሁሉ ያደርጋል። ይወርዳል በሰውም ሕይወት ውስጥ መኖሪያውን ያደርጋል፡ አሁን፡ አስተውሉ፡ ሕያው የሚያደርገውን ኃይል ያመጣል። አሁን፡ በኢየሱስ ላይ የመጣው ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል የዚያን ዘመን የቃሉን ተስፋዎች ሁሉ ይገልጥ ዘንድ ሕያው አደረገው። በዛሬው ዘመንም የፌዝ መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ፡ መንፈስ ቅዱስን የሚያስመስል ዲያብሎስ ካልሆነ፡ ነገር ግን እውነተኛውና፡ ትክክለኛው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፡ በእኛ ላይ የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ እንዲሁ ነው፡ የዚህን ዘመን ተስፋ ይገልጣል።

87 በሉተር ላይ በወረደ ጊዜ፡ የዚያን ዘመን ተስፋ ገለጠ። በዌስሊ ላይ በወረደ ጊዜ፡ የዚያን ዘመን ተስፋ ገለጠ። በዚህም ዘመን ሲወርድ፡ የዚህን ዘመን ተስፋ ይገልጣል። በሙሴ ላይ በወረደ ጊዜ፡ የዚያን ዘመን ተስፋ

ገለጠ። በኖኅ ላይ በወረደ ጊዜ፡ የዚያን ዘመን ተስፋ ገለጠ። በኢየሱስ ላይ በወረደ ጊዜ፡ የዚያን ዘመን ተስፋ ገለጠ። አያችሁ?

88 መንፈስ ቅዱስ የሚወርደው፡ የንጥቀት አካል እንዲሆኑ፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰናቸውን ሰዎች ሕያው ለማድረግ ነው። አስተውሉ። ይህም ማለት፡ እርሱ እውነተኛ ነሰር ከሆነ፡ እውነተኛ ነሰር ከሆነ የዘመኑን መልእክት ይረዳል። አሁን፡ ትንሹ ነሰር ምናልባት፡ በረት ውስጥ ሳለ፡ ምግቡን በደንብ እየበላ ነበር፡ ሆ—ሆኖም ልክ እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። ነገር ግን እውነቱን በሰማ ጊዜ፡ ያንን እውነት ተቀበለ። አሁን፡ በዮሐንስ 14...

89 ማለቴ፡ በዮሐንስ 5፡24 ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ነገር ግን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድም አይመጣም።" "የሚያምን" የሚለው ቃል፡ ምንኛ ቀላል እንደሆነ እስቲ አስቡ። አሁን፡ የዚህ ትክክለኛው አባባል፡ "የሚረዳ" ማለት ነው።

90 አሁን፡ ወደ መንገድ ወጥታችሁ ይህችን አመንዝራ፡ "ታምኚያለሽ" ብትሏት?

"አዎን" ትላለች።

"እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኚያለሽ? "

"በእርግጠኝነት።"

"ተጠምቀሻል? "

"በእርግጥኝነት።"

91 ወደ ሰካራሙ ሄዳችሁ፡ "ያንን ሰማህ፡ ሰባኪው ሲሰብክ ሰማህ? " ብትሉት?

"አዎ" ይላል።

"ያንን ታምናለህ? "

"በእርግጥ" ይላል። አያችሁ?

92 ነገር ግን፡ "የሚረዳ፡ በዚህ ዘመን ያለውን ሰፍራውን የሚያውቅ፡ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ ይህ አለው" (አሁናዊ ያመለክታል) "የዘላለም ሕይወት አለው። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድም አይመጣም።" ከዚያም ይህ አዲሱ የዘላለም ሕይወት በእናንተ ውስጥ ሲኖር፡ ከሟችነት ወደ አለመሞት ሕያው ለመደረጋችሁ ማረጋገጫ፡ ወይም መያዣ ነው።

93 እስቲ ደግሜ ልበለው። ይህ መንፈስ፡ እናንተን እንደ ግለሰብ አግኝቶ፡ በእናንተ ላይ ሲመጣ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ስለ እናንተ አስቦ ያዘጋጀላችሁ የዘላለም ርስት ማረጋገጫ ነው። ያ ማረጋገጫችሁ ነው።

94 ልክ የኦክ ዛፍ ብትጠይቁኝና፡ እኔ ደግሞ የኦክ ፍሬውን ብሰጣችሁ እንደማለት ነው። አሁን፡ የ—የ—የኦክ ዛፉ ሕይወት ያለው በዚያ ፍሬ ውስጥ ነው፡ ነገር ግን እስኪያድግ ድረስ መጠበቅ አለባችሁ።

95 እኛም እንደዚሁ ነን። የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ ስትቀበሉ፡ ያ አስቀድሞ እናንተን የለየ፡ የእግዚአብሔር መያዣ ነው። እናንተም በተሰፋው

መንፈስ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ ወደ ክርስቶስ አካል ታትማችኋል። እግዚአብሔር በቀራንዮ ቁልቁል ተመልክቶ ኢየሱስ ሲሞት ባየ ጊዜ፡ እርሱ የሞተው... ለሙሽራይቱ፡ ለአካሉ ጭምር ነው፡ ይህም ለዘመኑ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለምታምን፡ ለቃል ቤተ ክርስቲያን ነው፡ ያም አካል፡ እግር፡ ራስ፡ ወይም ምንም ሊሆን ይችላል። አያችሁ? ይህ... ክርስቶስ ደም እየፈሰሰው ይሞት ነበር። እግዚአብሔርም፡ እርሱን ሲመለከት፡ ትንሣኤውን አየ፡ ቤተ ክርስቲያንም በትንሣኤ ዕለት ከእርሱ ጋር አብራ ተነሳች።

96 አሁን፡ ይህን ሁሉ በአንድ ላይ እንዲትረዱት እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም ጌታ ቢፈቅድ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ የምናገረው ነገር አለኝ።

97 አሁን አስተውሉ። መያዣ፡ ወይም ማረጋገጫ ነው። መንፈስ ቅዱስን ስትቀበሉ፡ የትንሣኤያችሁ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ ቀብድ፡ በውስጣችሁ ይኖራል።

98 አስተውሉ፡ እ—አሁን ወደ ሙሉ ትንሣኤው ለመድረስ፡ በመንገድ ላይ እያደጋችሁ ነው። የትኛውም ዛፍ በአንድ ሌሊት በቅሎ አያድግም። በእግዚአብሔር ጸጋና እውቀት እያደግን ስንሄድ፡ እርሱም ማደግ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃችኋል። አሁን፡ እንደ ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃ፡ ማደግ ጀምራለች። ቅርንጫፎች ደርቀዋል። እነርሱም እየከረከሙ ይጥሏቸው ነበር። ነገር ግን ዛፉ አሁንም እያደገ ነው፡ አሁንም እየቀጠለ ነው፡ ምክንያቱም ወደ ትንሣኤው መድረስ አለበትና።

99 አማኞች ለሆናችሁት እናንተ ቃሉን ሕያው ለማድረግ፡ በመንፈስ ይመራሉ። ወደ መጀመሪያው ቅርንጫፍ፡ ወደ ሁለተኛው፡ ወደ ሦስተኛውና፡ ወደ ላይ ስትወጡ፡ ቃሉ ሕያው መሆኑን ይቀጥላል። ዝም ብሎ ሕያው ማድረጉን ይቀጥላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ለእናንተ ሕያው ማድረጉን ይቀጥላል።

100 አስተውሉ፡ በጴንጤቆስጤ፡ ባገኙት አዲስ ሕይወት አካላቸው ሕያው ተደርጎ ነበር። ይህ በመንፈስ እንድነካ ያደርገኛል። አስቡት። አሁን፡ እዚህ ጋር የነበሩት ሰዎች፡ ዓሣ አጥማጆች፡ ቀራጮች፡ ትሑታን የሆኑ ምስኪን ሴቶች... እና ተራ የቤት እመቤቶችና፡ ትንንሽ ደናግል ልጃገረዶች ነበሩ። አማኞች ነበሩ። ይህ እውነት እንደሆነ ያምኑ ነበር። ይህንን አምነው ነበር፡ ኢየሱስ በሞተ ጊዜ (በእርሱ አምነዋል) እና ከሙታን እንደገና፡ በተነሳ ጊዜ፡ እግዚአብሔር እርሱን ወደ ሕይወት ሕያው እንዳደረገው የሚገልጸው፡ ፍጹም የእግዚአብሔር ምስክርነት እንደሆነ ያምኑ ነበር።

101 አሁን፡ የባለቤትነት ማረጋገጫቸውን ለመቀበል፡ ወደ ጰንጠቆስጤ ቀን፡ ይሄዳሉ። የባለቤትነት ማረጋገጫ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ከማንኛውም ዕዳ ነጻ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ ነው። የባለቤትነት ማረጋገጫቸውን ለመቀበል ወደዚያ ወጡ። ሕያው ተደረጉ፡ ምንኛ አስደሳች ነው! መሬቱን ገዝተውት ነበር፥ ይልቁንም ተገዝቶላቸው ነበር። ተቀብለውትም ነበር።

102 ይህ እውነት ነው ወይስ አይደለም? "እሱ ሲነሳ አይተነዋል፡ አሁን ግን እኛስ? እኛ ምስክሮች ነን። ቆመን ያ ሰው ሲሰቀል አይተናል። ደመና በምድር ላይ መጥቶ ሰማያትን ሲያጨልም አይተናል። ም—ምድርም ተናወጠችና ተንቀጠቀጠች፥ እስክትዝል ድረስም ተንቀጠቀጠች። ከዚያም... በመቃብር

አኖሩት። በጦርም፡ ልቡን ወጉት፡ አካሉንም አውርደው በአርማትያስ ዮሴፍ መቃብር ውስጥ አኖሩት።”

103 ከዚያም፡ በሦስተኛው ቀን እንደገና መነሳቱን፡ አወቁ። ደቀ መዝሙሩም እንዳለው፡ “እኛ ለዚህ ምስክሮች ነን። ሲነሳ አይተነዋል። ሕያው መሆኑን እናውቃለን።”

104 ታዲያ ይህ ምን አደረገ? ፍርሃትን ሁሉ አስወገደ። ኢየሱስ፡ “አትፍራ። ሞቼ ነበርኩ፡ እነሆም ለዘላለም ሕያው ነኝ” ማለቱ ምንም አያስደንቅም። አያችሁ? ያንን ባደረጉ ጊዜ፡ ፍርሃትን ሁሉ አስወገደ።

105 አሁን ግን፡ ወደ ጰንጠቆስጤ በወጡ ጊዜ፡ እዚያ ሕያው የሚያደርገውን ኃይል፡ ሕያው ያደረጋቸውን ያንን ኃይል ተቀበሉ።

106 አሁን እዚህ ጋር ነው እንግዲህ፡ እናንተ የፕሬስቢቴሪያንና የሜቶዲስት ወንድሞች፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምኑ መያዣውን እንደምትቀበሉ አስባለሁ፡ ሆኖም የባለቤትነት ማረጋገጫው ገና አልመጣም። ይህም የይዞታ ሰነዱ ከዕዳ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

107 እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋን ሰጠው። አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፡ ይህም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ነገር ግን ቃል ኪዳኑን በመገረዝ ማኅተም አተመው።

108 እግዚአብሔርም እናንተ እንደምትቀበሉትና፡ እንደምትነሱ፡ ይህ አካልም፡ በመጨረሻው ዘመን ከእርሱ ጋር እንደሚከብር በመያዣ ደረጃ፡ ተስፋ ይሰጣችኋል። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ በዚያ ሰነድ ላይ ማረጋገጫ ማግኘት አለባችሁ። ማረጋገጫው ደግሞ በእርሱ ላይ የነበረው ዕዳ ሁሉ ተደምስሶ፡ ሰነዱን ሰትይዙ ነው። ማኅተሙን አግኝታችኋል። የእናንተ ነው። በእርሱ ላይ ያለው ነገር ሁሉ የእናንተ ነው። አሜን።

109 በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነቱ አምነን፡ ንስሐ ገብተንና ተጠምቀን፡ አምነነው ስንመጣ፥ እግዚአብሔር ንስሐችንንና በእርሱ ላይ ያለንን እምነት ይመለከትና፡ ሰነዱን ይልካል። ሰነዱም ዋስትናው ነው። በእናንተ ላይ ተይዞ የነበረው ነገር ሁሉ፡ በሙሉ ንስሐ እንደተወገደ፡ ማረጋገጫው ነው። ሃሌሉያ! ርስቱም ተገዝቷል፡ እናንተም ለዋስትናው ሰነዱን ይዛችኋል።

110 ማንም ሰው ከመሬታችሁ ሊያወጣችሁ ቢሞክር፡ ርስቱ የእርሱ እንደሆነ ቢናገርም፡ እናንተ ግን ሰነዱ በእጃችሁ አለ። እስቲ ይሞክር። ሰነዱን ስለያዛችሁ፡ በምድሪቱ ላይ ሊያወጣችሁ የሚችል ምንም ዓይነት ሕግ የለም።

111 በእግዚአብሔር ማረጋገጫና የይዞታ ማረጋገጫ ድንበር ሊያልፍ የሚችል፡ ምንም ዓይነት ዲያብሎስ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ወይም የሃይማኖት ትምህርት የለም፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ መሆናችንን ለይቶ አውቆልናልና። እርሱ እንደተነሳ እኛም እንደምንነሳ እርግጠኞች ነን፡ ምክንያቱም ቀድሞውኑ በመያዣ መልኩ በእርሱ ውስጥ ተነስተናልና። አሜን።

112 ያረጀ ነገሮች... ለሚሞተው ሰውነታችን ምን ያደርጋል? አመለካከታችንን ይቀይራል፡ ሐሳባችንን ይለውጣል። ፍቅራችንንም መሻታችንንም በላይ ባለው ነገር ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል። ሲጋራ ማጨስ፡ መጠጥ መጠጣት፡ ቁማር

መጫወትና፡ ቀድሞ ታደርጓቸው የነበሩት ነገሮች ሁሉ፡ የሞቱ ናቸው። ከእናንተ በታች ናቸው።

113 ሕያው ተደርጋችኋል። ይህ ሕያው የሚያደርግ ኃይል አካላችሁን ቀድሞውኑ፡ ወደ ንጥቀት ሁኔታ ያመጣዋል። የጴንጤቆስጤ ሰዎች እዝያ፡ በመንፈስ ቅዱስ ህያው በተደረጉ ጊዜ አስተውሉ። አዳምጡኝ። በጴንጤቆስጤ ቀን፡ በዚያ የነበረው ጴንጤቆስጤ ቡድን፡ ሰነዳቸውን ከእግዚአብሔር በተቀበሉ ጊዜ፡ እርግጥ ነው፡ ያ ነፍሳቸውን አከበረው። ጮኹ። በእያንዳንዳቸው ላይ የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች አዩ። አካላቸውንም በጣም ሕያው ስላደረገው፡ ከዚያ በኋላ በምድራዊ ቋንቋ መናገር እንኳ አልቻሉም። አካላቸውን ወደሚሄዱበት ሰፍራ ወደሆነው፡ ወደ ሰማያዊ ቋንቋ ሕያው አደረገው። የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይል ሟች አካላቸውን በጣም ስላናወጠው፡ መላው ሟች ቋንቋቸው ተቀየረ፡ ወደማይሞት ቋንቋ ተለወጠ። ምንኛ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነው! ምን? የራሰ የሆነ ነገር።

114 “ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ያ መንፈስ፡ በሚሞተው አካላችሁ ውስጥ ቢኖር፡ እርሱ ለሚሞተው ሰጋችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።” እንግዲያውስ እኛ በሕያው እግዚአብሔር ኃይል ሕያው ተደርገናል።

115 ልሳኖች፡ እነርሱን ለመናገር፡ ወደ አዲስ ወደ ሰማያዊው ቋንቋ ሕያው ሆኑ፥ ወደ ንጥቀት ከፍ ተደረጉ፡ ቀድሞ ከኖሩበት ድባብ ወደ ተለየ ድባብ ከፍ አሉ። እንዲሁም፡ በውስጣቸው በገባው፡ በዚያ አዲስ ሕያው በሚያደርግ ሕይወት፡ ቋንቋቸው ሕያው ሆነ። በአዲስ ልሳን ተናገሩ። ኦህ፡ አዎን!

116 አሁን እነርሱን ተመልከቱ። እንዲሁም፡ ከዚህ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በኋላ፡ በግዛቱ ላይ ያለውን ተሰፋ ሁሉ እንዲሰጣቸው ታስቦ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ቃል የተገባው የእግዚአብሔር ቃል ተሰፋ ሁሉ፡ ተሰፋው ለእነርሱ ሕያው ይሆን ዘንድ፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ተሰጣቸው። ስለዚህ፡ በታመሙት ላይ እጃቸውን ጫኑ፡ እነርሱም ተፈወሱ። በአዲስ ልሳን ተናገሩ። ያ በእግዚአብሔር ተሰፋ ውስጥ ስለነበረ፡ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን አደረጉ። ኢየሱስም፡ የእግዚአብሔር ልጆች የነበረውን፡ ያንን ግዛት ርስት ለእነርሱ ሊመልስ በሞተ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ምን እንደሆነ በተግባር አሳየ።

117 ይህንን ወደ ማኅበራዊ ወግ ለመለወጥና በድርጅት ውስጥ ለማስገባት እንዴት እንደፍራለን? ይህን ለማድረግ ምንም መብት የለንም።

118 ዛሬም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ያንን መልእክት የሚያምኑ ቅን ልቦችን እየፈለገ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ቃል የተገባው ነገር ሁሉ፡ ለዚያ አማኝ የተዘጋጀ ነው። በሙሉነቱ ስትቀበሉት፡ እግዚአብሔርም እንደምታደርጉት ሲያውቅ፡ ለዚያ ማረጋገጫውን ሰነድ ይሰጣችኋል። ያኔ የተገባው ተሰፋ ሁሉ የእናንተ ውርስ ይሆናል፡ መንፈስ ቅዱሰም ያንን ለእናንተ ሕያው ለማድረግ እዚያ ይገኛል። ኦህ፡ ማይ! ም—ምን ዓይነት ሰዎች ልንሆን ይገባል? የእግዚአብሔር ታላቅ መንፈስ ቅዱስ ያንን ኃይል ሊያደርግ እዚህ መገኘቱን ማየት ምንኛ ድንቅ ነው! እስቲ አስቡት። መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ ለዚህ ዘመን ምስክር ሊሆን፡ እዚህ አለ። ኢየሱስ እንዲሁ ብሏልና። እርሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ነው።

ያንን ከዚያ ለማጥፋት ማንኛውም ሰው እንዴት ይደፍራል?

119 "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡" ዮሐንስ 14፡ 12። "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።" ዋስትናው ያ ነው። ሰዎች በአንድ ላይ ተቀምጠው፡ እነዚያ ምልክቶች ሲገለጡ ስናይ፡ ያ ርስት የእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ ሰነዱ እዚያ መኖሩን የሚገልጽ ዋስትና ነው። አሜን።

120 ስለዚህ፡ እኛም ደግሞ፡ ትንሣኤ ነን። አሜን። አሁን በትንሣኤያችን ውስጥ ነን። ሃሌሉያ፡ ቀድሞውኑ፡ ከዓለም ነገሮች፡ ወደ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃላት ተነስተናል። ወደፊት ሳይሆን፥ አሁን ተነስተናል። ይህም መያዣዎቹ ናቸው።

121 ይህ የእግዚአብሔር ተሰፋ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናት መንፈሱን እንደሚያፈስ፡ እነርሱም ያንን እንደሚያደርጉ ተናግሯል። አስተውሉ፡ በታመሙት ላይ እጃቸውን ጫኑ፥ በእግዚአብሔር ተሰፋ ውስጥ የነበረው ነገር ሁሉ ተፈጸመ። "በመጨረሻዎቹ ቀናት መንፈሴን፡ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ። ሽማግሌዎቻችሁ ሕልምን ያልማሉ። ወጣቶቻችሁም ራእይን ያያሉ።" እርሱም የገባቸው እነዚህ ሁሉ የተለያዩ ተሰፋዎች፡ ሁሉም ነገር እዚያው በእግዚአብሔር ተሰፋ ውስጥ ይገኛሉ። ኢየሱስም ያንን ለእኛ ቤዝልን። እኛም...

122 ወይም፡ እኛ፡ ለዚያ ርስት የተወሰንን፡ በዚያ ርስት ለመሆን የተወሰንን ከሆንን፥ ልክ በዶሮዎች ጎጆ ውስጥ እንደሚመላለስ ንስር ነን። ለዚያ ግዛት የተወሰናችሁ ከሆናችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ለመፈለግ እዚህ አለ። ባገኛችሁም ጊዜ፡ ጥሪውን ትለያላችሁ። የምትኖሩበትን ዘመን ታውቃላችሁ። እነዚህ ነገሮች ሊሆኑ እንደሚገባቸው ታውቃላችሁ። ወዲያውኑ እርሱን ለመገናኘት በንጥቀት ወደ ላይ ትነሳላችሁ፡ አሁንም በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጣችኋል። ኦህ፡ ምንኛ ታላቅ ተሰፋ ነው! እነዚህን ነገሮች የሚሰጠን፡ የሰማይ አባታችን ምንኛ ድንቅ ነው!

123 በዚያ ቀን፡ ሙታንን ወደ ሕይወት እንዲመልሱ፡ መንፈሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረታቸውን ሕያው ያደርገዋል። በሙታንም ላይ ሰውነታቸውን አስተኙ፥ እነርሱም ሕያዋን ሆኑ። በደንብ አዳምጡኝ። ኢየሱስ ያደረገውን ያንኑ ነገር አደረጉ፡ ምክንያቱም በእርሱ ላይ የነበረው፡ ያው መንፈስ በእነርሱም ላይ ነበርና። አንድ መንፈስ አንዱን ሰው እንዲህ እንዲያደርግ ካደረገው፡ ሌላኛውንም እንዲሁ እንዲያደርግ ያደርገዋል። አንድ...

124 ታዲያ ይህ በእርሱ ላይ መጥቶ ሳለ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አለኝ እያለ፡ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዴት ይክዳል? ሊያደርገው አይችልም።

125 አስተውሉ። በግሪክ **ዞዊ** የተባለው፡ የእግዚአብሔር ሕይወት፡ በእነርሱ ውስጥና በመካከላቸው በመንቀሳቀስ፡ አእምሮአቸውን ለቃሉ ሕያው አደረገው። አሁን፡ ይህንን በዝግታ ልናገር። በሕዝቡ መካከል የሚንቀሳቀሰው የእግዚአብሔር መንፈስ፡ የሰውን አእምሮ ለእግዚአብሔር ተሰፋ ሕያው ያደርገዋል። አያችሁ? እርሱ ይህን ያደርጋል። ተመልከቱ። እኔም አሁን ስ—ስለ... ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በእርሱ ውስጥ፡ ሕያው ስለመሆን እየተናገርኩ መሆኑን፡ እንድትረዱ ለማሳየት እየሞከርኩ ነው።

126 እንዲሁም፡ ከጅምሩም፡ እነርሱ የእርሱ ባሕርያት ብቻ ነበሩ። እግዚአብሔር ገና ከጥንት ጀምሮ፡ ከሚሊዮኖች ዓመታት በፊት፡ "**በዚህ** ቀን፡" "ጆን ዳዊ አገልጋዬ ይሆናል፡" ቢል እንኳ ይሆናል። አሁን፡ ጆን ዳዊ በኃጢአት

ተወልዶ፡ በበደል ተቀርጾ፡ ሟች ስለሆነ፡ ውሸት እየተናገረ ወደ ዓለም መጣ። ነገር ግን፡ ምናልባት፡ ትንሽ የሃይማኖት ስሜት ይሰማው ይሆናል። ሄዶም ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀላል። ምናልባት የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን ይቀላቀላል። አላውቅም። ማንኛውንም ነገር ሊቀላቀል ይችላል። ነገር ግን፡ አንዴ ብቻ በእግዚአብሔር ድባብ ውስጥ ይግባ። አያችሁ? ያ ንስር እናቱ ማን እንደሆነች እንዳወቀ ሁሉ፡ ጀን ዳዊ አባቱ ማን እንደሆነ ማወቁ አይቀሬ ነው። ሊረዳው ይገባል። አያችሁ? ጀን ዳዊ ማለት፡ ቃል የሆነው የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፡ የተነገረው፡ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ያንን ቃል ይፈልገዋል። ይኸውላችሁ። ይጠራዋል፡ የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል፡ የእግዚአብሔር ቃል ወደሆነው፡ ወደ እግዚአብሔር መገኜት ያመጣዋል።

127 ተመልከቱ። እግዚአብሔር ኢየሱስን ሲያይ የነበረው ያንኑ ነው። “ተፈጸመ፡” ባለ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ከ—ከኢየሱስ ጋር የጨረሰው ያ የተፈጸመ ሥራ ነበረ። ዕቅዱ ሁሉ ተፈጽሞ ነበር።

128 የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ሲመጣ፡ እናንተም በእውነት እርሱ ከተናገራቸው የእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ከሆናችሁ… አሁን፡ ካልሆናችሁ ግን፡ ጥያቄ ውስጥ ትገባላችሁ ትዋከባላችሁ፡ **ወዲህና ወዲያ** ትሮጣላችሁ፡ ሁሉንም ነገር ታደርጋላችሁ፡ ነገር ግን ወደ እውነት እውቀት ከቶ አትመጡም። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] ከእነርሱ አንዱ ከሆናችሁ ግን፡ አሮጌው ነገር ወዲያውኑ ያልፋል፡ አያችሁ፡ እናንተም አዲስ ትሆናላችሁ፡ የመዳንም ዕቅድ ይፈጸማል። እግዚአብሔር እንድታደርጉት፡ ስለ እናንተ የተናገረውን እያንዳንዱን ቃል ለመታዘዝ ዝግጁ ትሆናላችሁ፡ አያችሁ። ለቃሉ ትገዛላችሁ። ውሉ፡ በትክክል፡ የውሉ ማረጋገጫ፡ የይዞታ ሰነዱ የእናንተ ይሆናል። ዕዳዎቹ ሁሉ ተከፍለዋል። ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን እንደነበረው ሁሉ፡ ሁሉም ተሰርዟል።

129 አሁን ይህ ሕያው የሚያደርግ መንፈስ፡ በሌሎች ሰዎች ላይ እንዴት እንደሚሠራ እናስተውል።

130 አሁን፡ ብዙም እንደማልናገር ነግሬአችሁ ነበር፡ ቃሌን ለመጠበቅ ሃያ ደቂቃዎች ብቻ ነው ያሉኝ፡ ያንን ካደረግሁ፡ አስተውሉ፡ ይህም እኔ ባልኩት ጊዜ ውስጥ፡ በ—በአንድ ሰዓት ገደማ ውስጥ ለመጨረስ ነው።

አሁን ይህ ሕያው የሚያደርግ ኃይል መሆኑን አስታውሱ። የሚመጣውም…

131 አሁን፡ ስለዚህ ብዙ ፌዝ አለ። ምንም ሳያገኙ፡ በእርግጥ እንዳገኙት የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ። ብዙ ሰዎች የሚያደርጉት ሌሎች ክርስቲያኖች ሲያደርጉ ባዩት ነገር የተሳሳተ ግንዛቤ ስላደረባቸው ነው። ሰይጣን ከእነዚህ መካከል ማንኛውንም ማስመሰል ይችላል። ይህንን እናውቃለን። እንደ ሚሲዮናውያን፡ በሁሉም ቦታ ተመሳሰሎ ማየት ትችላላችሁ፥ ጩኸት፡ ጭፈራ፡ በልሳን መናገር፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮችን ማየት ትችላላችሁ። በሁሉም ቦታ ተመሳሰሎ ማየት ትችላላችሁ። በትክክል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በሚክዱ አረማውያንና ሰዎች መካከልም እንኳ ይህ ይታያል። አያችሁ? እነርሱ ራሳቸው፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ያደርጋሉ።

132 ነገር ግን ወደ አማኝ የሚመጣው እውነተኛውና፡ ትክክለኛው ሕያው የሚያደርግ መንፈስ፡ ለእግዚአብሔር ቃል ሕያው ያደርገዋል፡ ይህም እንደገና

ወደ ንሰር ምግብ፡ ወደሚኖርበት ሰፍራ መመለስ ነው። “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።”

133 ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን እንደነበረው፡ ይህ ሕያው የ—የሚያደርግ መንፈስ በሌሎች ሰዎች ላይ እንዴት እንደመጣ እናስተውል።

134 በጴንጤቆስጤ ቀን እንዴት እንደነበሩ፡ እንዳደረጉ እናስተውል፡ እያወራን ባለነው በዚህ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ሕያው ተደርገው እንደሆነም እስቲ እንይ። በጴንጤቆስጤ ቀን፡ ሁሉም እዚያ ላይኛው ክፍል ይጠብቁ ነበር። በውስጣቸው፡ ይፈሩ ነበር። አይሁዶች፡ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ ብለው፡ ፈርተው ነበር። ነገር ግን ምን ሆነ? ይህ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ከሰማይ በወረደ ጊዜ፡ ድፍረት በላያቸው ላይ ሆነ። ከጥቂት ሰዓታት በፊት እርግጠኛ ያልነበሩበት፡ የሆነ ነገር፡ የሆነ መረዳት መጣባቸው። እርሱ እንደሞተ ያ—ያውቁ ነበር።

135 እንደተነሳም ያውቁ ነበር። በመንገድ ላይም አነጋግረውት ነበር። “ነገር ግን ያ ነገር ለእነርሱም ነበር፡ ወይስ እንዲሁ ለእርሱ ብቻ፡ ለኢየሱስ ብቻ ነበር? ”

136 ነገር ግን እዚህ በጴንጤቆስጤ ቀን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ይኸውም የይዞታ ማረጋገጫው በአማኞች ላይ ወረደ። ይህም የትንሣኤው ተካፋይ አደረጋቸው፡ የኅብረቱም ተካፋይ አደረጋቸው። መንፈስ ቅዱስ መጥቶ እንደሚነሱ አረጋገጠላቸው፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከፈሪነት ወደ ጀግንነት፡ በተዘዋዋሪ ተነስተው ነበር።

137 ያ—ያሰቡት የነበረውን ያንኑ ቃል ፈርተውት ነበር። ይህ እንዳያመልጣችሁ። ፈርተው ነበር። እርሱ ያ ቃል መሆኑን ያውቁ ነበር።

138 አይሁዶች እንኳ ይህንን ማመን ነበረባቸው። ኒቆዲሞስም፡ “ረቢ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር እንደሆንህ እናውቃለን። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል ማንም የለምና። አሁን፡ ይህን እናውቃለን። ይህን እንገነዘባለን” አለው።

139 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ... ጴጥሮስ በፊቱ እንኳ ምሎ ነበር። ሁሉም በሰቅለቱ ጊዜ ትተውት ሸሽተው ነበር።

140 አሁን ግን እዚህ በዚህ ላይኛው ክፍል፡ በእግዚአብሔር ፊት ተሰብስበው ነበር። ከዚያም፡ በድንገት፡ ይህ መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ ወረደና፡ ሕያው አደረጋቸው። ሕያው የማድረጉም ሥራ ሲከናወን፡ ያመኑትንና እውነት መሆኑን ያወቁትን መልእክት ለመመስከር አልፈሩም። አለባለዚያ ግን፡ ይፈሩት ነበር።

141 ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ፡ ስንት የፕሬስቢቴሪያን፡ ስንት የሜቶዲስት፡ ስንት የባፕቲስት፡ እውነቱን እያወቁ ስለ እርሱ ግን መቆም የሚፈሩ፡ ስንት የጴንጤቆስጤ አባላት ናቸው? በእናንተ ላይ የወረደው፡ ምንድን ነው ብዬ ለመጠየቅ እገደዳለሁ? የትንሣኤው አካል ናችሁን? ለአንድ ሰው ንድፈ ሃሳብና ሃሳብ ብላችሁ ዝም ለማለት ትደፍራላችሁን? ወይስ፡ እውነተኛውን ድፍረትና እውነተኛውን ወ—ወንድነት ይዛችሁ ወጥታችሁ፡ ትክክለኛውን “ትክክል፡” ስህተቱን ደግሞ “ስህተት” ለማለት ትችላላችሁን? የትንሣኤው አካል ናችሁ፡ ወይስ የሃይማኖት መግለጫዎች ስብስብ አምላኪዎች ናችሁ? ቤተ ክርስቲያን

ተመላላሾች ሆናችሁ፡ ሰማችሁም እዚያ ሆኖ፡ ነገር ግን በኃጢአትና በበደል ሙታን ናችሁን?

ሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል የማያምን ሁሉ ኃጢአተኛ ነው።

142 እነዚያ ፈሪሳውያን በብዙ ነገሮች፡ እውነት እንደሆኑ ያምኑ ነበር። “እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፡” ይሉ ነበር። ያ ቃል እስከሚሰበክ ድረስም፡ ነበሩ። ነገር ግን ያ ቃል ተሰብኮና ተረጋግጦ ሲመጣ፡ ትክክል መሆኑን ያወቁትንና የመሰከሩለትን፡ ያንን ነገር ውድቅ በማድረጋቸው ኃጢአተኞች ሆኑ። “እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ካልሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል ማንም የለምና፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር እንደሆንህ እናውቃለን።”

143 ዛሬ የት ነው ያለነው፡ ብዬ እሰባለሁ? እጠይቃችኋለሁ። ይህ ትንሣኤ የት ነው የሚያገኘን? ወጥታችሁ ለመቆም ትደፍራላችሁን? እግዚአብሔርን በቃሉ ለማመን ትደፍራላችሁን? ለሕይወት የተወሰናችሁ ከሆናችሁ፡ በእርግጥ ታደርጉታላችሁ። ንስር ከሆናችሁ ደግሞ፡ ላታደርጉት አትችሉም፡ በውስጣችሁ የሆነ ነገር አለና። ወይስ፡ የሆነ ቦታ የሃይማኖት መግለጫ፡ “እኔ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። እኔም እንደ እናንተ ጥሩ ነኝ” በማለት፡ ማገልገል ትፈልጋላችሁ? አያችሁ? የልጅነት መብት ከሌላችሁ፡ ፈጽሞ አታዩትም፡ ልታዩትም አትችሉም። ነገር ግን ይህን የልጅነት መብት ከያዛችሁ፡ የእናንተ አካል ስለሆነና፡ እናንተም የእርሱ አካል ስለሆናችሁ ሳታዩት አትቀሩም።

144 የወለደችኝን እናቴን እንዴት ልክዳት እችላለሁ? የራሱ ደም በእኔ ውስጥ ያለውን አባቴን፡ እንዴት ልክደው እችላለሁ? ቻርለስ ብራንሃም አባቴ መሆኑን እንዴት ልክድ እችላለሁ? ላደርገው አልችልም። ለስድቡም ሆነ ለማንኛውም ነገር ለመቆም ዝግጁ ነኝ፡ ምክንያቱም እኔ ልጁ ነኝና። ሃሌሉያ!

145 እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንኩ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሆኑን፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን እንዴት ልክድ እችላለሁ? የምንኖርበትንም ሰዓት ሰናይ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትንሣኤ ያስፈልገናል። ትንሣኤ! ወንዶችና ሴቶች ወጥተው ለእግዚአብሔር ለተረጋገጠው ቃሉ እንዲቆሙ፡ እምነትን ኃይል የሚሰጥ፡ ትንሣኤ ያስፈልገናል።

146 “እንግዲህ፡ ለክርስቶስ የሚሆኑ ወጣቶች ፕሮግራም አለን፡” ትሉ ይሆናል። ያ መልካም ነው። “ቤተ ክርስቲያናችን ሰብሰባ አላት፡ **በጣም** ብዙ አባላትን እንፈልጋለን” ትላላችሁ። ያንን አልቃወምም። ያ መልካም ነው። ነገር ግን ያ ድባቡ ብቻ ነው። ያ ምናልባት የአሮጊት ዶሮ ላባ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እዚያ ውስጥ በትክክለኛው ድባብ ውስጥ ከገባችሁ፡ የንስር እንቁላል ከሆናችሁ ንስር ይፈለፈላል። እግዚአብሔርም ይህንን ታዩ ዘንድ አስቀድሞ ከወሰነላችሁ፡ ሳታዩት አትቀሩም፡ በትንሣኤ ውስጥ እየወጣችሁ ነው። ባፕቲስቶች የተወለዱት በዚያ መንገድ ነበር፡ ሜቶዲስትም የተወለዱት በዚያ መንገድ ነበር፡ በዚያ ዘመን በነበረው ትንሣኤ ውስጥ ነበር፡ ነገር ግን ከንስር ይልቅ ወደ ዶሮነት ተለወጡ።

147 በቅርብ ጊዜ እንደተናገርኩት፡ ከቱሰን ወደ ታች ስወርድ፡ አንድ በጣም የሚገርም ነገር ተመለከትኩ። እዚያ ሽቦ ላይ አንድ ጭልፊት ተቀምጦ አየሁ።

ያ ጭልፊት ማንነቱን ካጣ ቆይቷል። ከንሰር ቀጥሎ ያለ ወፍ ነበር። ንሰርን ሊከተል ግን አይችልም፥ በፍጹም፡ አይችልም። ንሰርን ሊከተል የሚችል ምንም ነገር የለም። ነገር ግን እርሱ ጭልፊት ነበር።

148 ክርስቶስ ንሰሩ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ቢያንስ ጭልፊት መሆን ይገባታል። እነርሱ ከሌሎቹ ወፎች ሁሉ በላይ ከፍ ብለው መብረር ይችላሉ። ነገር ግን ያ ጭልፊት ደክሟል። ማንነቱንም አጥቷል። በስልክ ሽቦዎች ላይ ተቀምጦ የሞተ ጥንቸል ካለ ይጠብቃል። እንደ ጭልፊት ከመብረር ይልቅ፡ እንደ ጥንብ አንሳ ይዘልላል።

149 ኦህ፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ የገዛ ውድ ወገኖቼ የሆናችሁ እናንተ የጴንጤቆስጤ ሕዝቦች ሆይ! ቤተ ክርስቲያን ማንነቷን እያጣች ነው። ትኩስ መና ለማግኘት፡ በዚያ በላይ ባለው፡ በሰማያዊ ሰፍራ ከመብረር ይልቅ፡ ወደ ታች ወርዳ በሆነ በሞተ የሥርዓት ሃይማኖት መግለጫ ላይ እየተደገፈች ነው።

150 ጭልፊት የገዛ መናውን ያድን ነበር፡ ዛሬ ግን መኪና የረገጠውንና ጥንብ አንሳዎች የሚበሉትን ይበላል። እንደ እሱ ይዘልላል። እሱንም ይመስላል።

151 እራሳችንን በዚህ ዘመናዊ ዓለም አስጌጠናል፡ ሴቶቻችን ጸጉራቸውን ይቆርጣሉ፡ አጫጭር ሱሪዎችንም ይለብሳሉ፡ ወንዶቻችንም በመድረክ ላይ ቆመው እውነትን ለመናገር የሚያስችል የጀርባ አጥንት የላቸውም። ለቃሉ ለዘብተኛ ከሆንን ቆይተናል።

152 ኦህ አምላክ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስን ላክና የሆነ ቦታ ያሉትን፡ ምንም ቢፈጠር በዚያ ለመቆም፡ ዝግጁ የሆኑትን፡ የሰንበት ትምህርት ጽሑፎችን ለመጠበቅ፡ በስልክ ሽቦ ላይ የሚቀመጡትን ንሰሮች ሣይሆን፡ ወደማይታወቀው ከፍታ የሚበሩትን እነዚያን ፈልግ። ቃሉ፡ በሃይሉ አዲስነትና በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ይኑረኝ። ትንሣኤ፡ መያዣ ያለው ትንሣኤ ያስፈልገናል። ወዳጄ ሆይ፡ እንዲህ ባለው በዓለም ጥንብ ረክተህ ከሆነ፡ የሆነ ችግር አለ ማለት ነው።

153 እህቴ፡ ወንድሜ፡ ሌላ የትንሣኤ ቀን ለማየት፡ በሕይወት ላልኖር እንደምችል፡ እያወቅሁ፡ ይህንን በእግዚአብሔር ፍርሃት ልንገራችሁ። ነገር ግን አንድ እርግጠኛ ነገር አለ፡ በእግዚአብሔር ቃል እውነተኛና፡ አስቀድሞ የተወሰነለት የእግዚአብሔር ልጅ፡ ያን የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰማ ጊዜ፡ ተነስቶ ሊቀበለው ይወጣል። ይህም እውነተኛውንና ሕያውን ቃል ለመገናኘት የሚሄድበት፡ መያዣ ነው። ልክ እንደ እሱ፡ ሙሽራይቱም ሙሽራውን ትገናኛለች። የአካሉ ክፍል ናትና።

154 አስተውሉ፡ ማንነታችንን እያጣን ከቆየን፡ ብዙ ጊዜ ሆኗል። አንዳንዶቻችን፡ ረቡዕ ምሽት እንመጣለን። ሌሎቹ ደግሞ **ሁ ላቭስ ሉዚ** ለማየት፡ ከቤተ ክርስቲያን ለመቅረት፡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፡ ሁሉንም ዓይነት ዓለማዊ ነገሮችና፡ መዝናኛዎችን ለማየት ቤት ይቀመጣሉ። ካጣነው ብዙ ጊዜ ሆኗል።

155 ሴሚናሪዎቻችንና፡ ትምህርት ቤቶቻችን፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጸሎት ስብሰባዎችን ቦታ እንዲተኩ፡ ብዙ የቲኦሎጂ የ—የሃይማኖት ትምህርት፡ መዝናኛና ሁሉንም ዓይነት ነገር የያዙ ሪኪዎችን ዘመናዊ ሰዎችን እያወጡ ነው። ዘመናዊዎቹ ሊያደርጉት የሚሞክሩትን እነርሱን ወደ ውስጥ ለማምጣት በማሰብ፡ የአለባበስ ሥርዓታቸውን ተከትለናል። በዚህ ግን ልታሸንፏቸው

አትችሉም። እነርሱ ከእናንተ ይልቅ ያ አላቸው። እናንተ በእነርሱ ግዛት ውስጥ... በእነርሱ ሜዳ ላይ ምንም ሥራ የላችሁም። እውነተኛው ጥምቀት ወደሚያበራበት፡ እውነተኛው የትንሣኤ ኃይል ወዳለበት፡ ወደ እናንተ ሜዳ ይምጡ። እንደ እነርሱ ያለ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት አትሞክሩ። እንደነርሱ ያለ ፓስተር እንዲኖራችሁ አትሞክሩ። **ይህንን፡ ያንን፡ ሌላውን** ለማድረግ፡ ወይም ከዓለም ጋር ለመተባበር አትሞክሩ። እነርሱ ከሆሊውድ ጋር ያንጸባርቃሉ።

156 እውነተኛው ወንጌል በኃይል ይበራል። ንስሮች ይህንን ይሰማሉ። እነርሱ ነጸብራቅ አይፈልጉም። የሚፈልጉት ብርሃንን ነው። በትሕትና፡ በፍቅርና፡ በኃይል ማብራት፡ እውነተኛ ንስር የሚፈልገው ይህንን ነው። በጓሮ በረት ውስጥ በመጫር እርሱን ደስ ማሰኘት አትችሉም። ይህን ሊያደርግ በፊጹም አይችልም። እንዲህ ብላችሁም ልትነግሩት አትችሉም፡ ምክንያቱም አያምነውምና።

157 ያ ድምፅ ከሰማያት ሆኖ፡ “ሞቼ የነበርኩ፡ እነሆም ሕያው ነኝ” ብሎ ሲጮህ፡ ያኔ የሆነ ነገር ይሆናል። “ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነኝ። በመጨረሻዎቹ ቀናት እንዲህ ይሆናል፡ ከመንፈሴ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ።” ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! “ሟች ቋንቋችሁን ሕያው አደርጋለሁ። ሟች ልሳናችሁን ሕያው አደርጋለሁ። በትንሣኤ ከእኔ ጋር እንደማመጣችሁ ማስረጃ እሰጣችኋለሁ።” የተራቡ-ልብ ያላቸው ንስሮች ይህንን ለማግኘት ያላቸውን ኃይል ሁሉ ይጠቀማሉ። ሌላውን ነገር ሁሉ ሽጠው፡ የሚገዙት፡ እጅግ የከበረ ዕንቁ እርሱ ነው። አሜን።

158 ወዳጄ ሆይ፡ እግዚአብሔር ይርዳን። አብያተ ክርስቲያኖቻችን ማንነታቸውን እያጡ ነው።

አሁን በፍጥነት ወደ አንዳንድ ነገሮች እንለፍ።

159 ፍርሃት ውስጥ የነበሩትን፡ የእነዚያን ደቀ መዛሙርት ድርጊት ተመልከቱ። ኢየሱስ እውነት እንደሆነ ያውቁ ነበር፡ ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ነገሩ በወቅቱ ከነበረው ተወዳጅ አሳብና፡ ዝነኛ ሃይማኖት፡ ማለትም እጅግ ጥብቅ ከሆኑት ሃይማኖቶች፡ ሳ-... ከፈሪሳውያን፡ ከሰዱቃውያንና፡ ከመሳሰሉት፡ ከእምልኮ ሰርዓቶቻቸው፡ ከጎሳዎቻቸው፡ ከሃይማኖት ተቋሞቻቸው ጋር የሚቃረን ነበር። እ—እነርሱ ያንን “የኑፋቄ ትምህርት” ይቃወሙ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ የተረጋገጠው ቃል ነበረ።

160 ኢየሱስም በመንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። “ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም አያየኝም። እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡” ሲል አካሉን ሳይሆን፥ በእርሱ ውስጥ የነበረውን ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ያኔ እንዳደረገው ሁሉ፡ የታዘዙ ልጆችን ለመጥራት፡ አሁንም በቤተ ክርስቲያን ላይ ነው።

161 “ሁልጊዜ አባቴን ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁ። ከእናንተስ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? ” በሌላ አነጋገር፡ **ኃጢአት** ማለት “አለመመን” ነው። “ቃሉ ስለ እኔ የተናገረውና፡ ያላደረግሁት ምን አለ? ” ይሄው ነው ነገሩ። “ቃሉ አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውንና፡ እኔ ያላደረግሁትን አሳዩኝ። ማን ሊወቅሰኝ ይችላል? ማንስ በእኔ ላይ ጣቱን ቀስሮ፡ የአባቴን ቃል አልፈጸምኩም ሊል ይችላል? ” ኦህ፡ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ወደዚያ ደረጃ በደረሰች ጊዜ! “በአለማመን ሊወቅሰኝ የሚችል ማን ነው? ”

162 ኦህ፡ ክርስቲያኖች ሆይ፡ እንደ ጭልፊት ሳይሆን፡ እንደ ንስር ተለዩ። ያ ጭልፊት ለሰላሳ ነው፡ ወደ ታችም ይወርዳል። ንስር ግን እንዲህ ሲያደርግ በፍጹም አታዩትም። ፈጽሞ እንዲህ አያደርግም። ከሰማያዊው፡ የራሱን ምግብ ያድናል። እግዚአብሔር እንደዚያው አድርጎ ሰርቶታልና። የሞተ ነገር ሳይሆን፡ ትኩስ መናን ያገኛል።

163 ዕብራውያን፡ በምድረ በዳ ሲያልፉ፡ የሞተ መና፡ ለመብላት ሞክረው ነበር። ተበላሽቶ ነበር። በ—በውስጡም ትል ነበረበት። ምን ማለታችን እንደሆነ ታውቃላችሁ። ዝም ብሎ የተበከለ፡ የበሰበሰ ነው። ትል ገብቶበታል።

164 ከዓመታት በፊት የሞተን ምግብ ለምን እበላለሁ? በመልክና በቅርጽ ሊኖር ይችላል፡ ነገር ግን ትኩስ አይደለም። በእያንዳንዱ ትውልድ፡ አዲስ ምግብ ማግኘት አለብን። ንስርም እንዲሁ በጉዟችን ላይ፡ በእያንዳንዱ ትውልድ፡ ያንን ምግብ ይፈልጋል። አስተውሉ።

165 አሁን እንደገና አንዳንድ ሰዎችን እንውሰድ። አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን እንውሰድና፡ ምን እንዳደረጉ እንመልከት።

166 በመጀመሪያ እስጢፋኖስን እንመልከት፡ በዚያ በሳንሄድሪን ሸንጎ መካከል እንዴት እንደነበረ እንመልከት። ያ ሸንጎ፡ ታላቅ አማኞች ነን የሚሉ ሰዎች ስብሰብ፡ ወይም እነዚያ አማኞች ሊሆኑ ይገባቸው የነበሩ ሰዎች፡ አመጡትና ሊኮንኑት ሞከሩ። “ለምን፡” “እናንተ አንገተ ደንዳኖች፡ ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ፡ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፡” አላቸው። የዘላለም ሕይወት ያ ነው። “አባቶቻችሁ በነቢያት ላይ እንዳደረጉት፡ እናንተም ዛሬ እንዲሁ ታደርጋላችሁ።” እነርሱም ጥርሳቸውን አፋጩበት። ይህንን መስማት አልፈለጉም ነበር። የቤተ ክርስቲያናቸውን መግለጫ ይቃወም ነበር። የሐይማኖት ተቋማቸውን ይቃወም ነበር። ያንንም ሰው በድንጋይ ወግረው ገደሉት። እርሱም እጆቹን ዘርግቶ፡ ወደ ሰማይ ተመለከተና፣ “ሰማያት ተከፍተው፡ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ፡” አለ። ለምን? ወደ ኢየሱስ እቅፍ የወሰደው፡ ያ የትንሣኤ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ በእርሱ ውስጥ ነበረና።

167 አሁን፡ በፍጥነት አስተውሉ። በታላቅ ሪቫይቫል ውስጥ የነበረውን፡ ፊልጶስን ተመልከቱ። እዚያ ጋር በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መካከል ትልቅ የትብብር ስምምነት ስለነበረ፡ እያችሁ፡ ማንም ሰው ያንን ለማድረግ በማይደፍርበት ሥፍራ ሪቫይቫል እያደረገ ነበር። ታላቅ ሪቫይቫል እያደረገ ነበር። የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይልም ተናገረው፡ እንዲህም አለው፡ “እስጢፋኖስ... ” ምናልባት እንዲህ ብሎት ይሆናል፡ “ታላቅ ሪቫይቫል እያደረግህ ነው፡ ነገር ግን እንድታነጋግረው የምፈልገው አንድ ሰው አለ።”

168 እስጢፋኖስም ምንም ያህል ትችት ቢኖርበትም፡ ምንም ቢሆን፡ ታዛዥ ነበር። “ኦህ፡ እስጢፋኖስ፡ መሄድ አትችልም።”

“ኧረ፡ እችላለሁ። እግዚአብሔር ተናግሯልና።”

169 ወደ በረሃም ወጣ፡ በዚያም ያንን ጃንደረባ አገኘው። ምን ተፈጠረ? እርሱም፡ “በ... በፍጹም ልብህ፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ካመንህ፡ አጠምቅሃለሁ” አለው። ባጠመቀውም ጊዜ...

170 ተመልከቱ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን መነቃቃት ትቶ፡ ወደ በረሃ፡ ወደ አንድ ሰው እንዲሄድ፡ በዚህ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ህይወትን አገኘ። ኦህ፡ ይህ ከሁሉም ምክንያቶች ጋር የሚቃረን ይሆናል። አያችሁ? “እነዴ፡ **እዚህ** እኮ አሥር ሺህ ሕዝብ ይፈልግሃል።” ነገር ግን **እዚያ** ውጭ፡ አንድ የሚጠብቅህ አለ። አያችሁ? ሕያው የሚያደርገው ኃይልም እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ስፍራ ላከው። ሃሌሉያ!

171 ወንዶችና ሴቶች ሆይ፡ በሁለት እግራችሁ እንድትቆሙ ያደርጋችኋል። እግዚአብሔር እንድታደርጉት የሚፈልገውን ነገር እንድታደርጉ ያደርጋችኋል። ሌላ ሰው ስለእሱ የሚለው ግድ የለኝም። ጎረቤት፡ “ኦህ፡ ያ ሰው አእምሮውን ስቷል። ሌሊቱን ሙሉ ይጸልያል፥ መጽሐፍ ቅዱስ ያነባል” ይል ይሆናል። የሚሉትን ግድ የለኝም። ዋናው እግዚአብሔር እንድታደርጉት የጠራችሁ ነገር ነው። በትክክል። “ኦህ፡ እነዚህን የድሮ ዓይነት የጴንጤቆስጤ ሪቫይቫሎች፡ ልናደርግ አንችልም” ይላሉ። ኦህ፡ አዎ፡ እኛም፡ እንችላለን። በውስጣችሁ ሊኖራችሁ ይችላል። ሌሎቹ ምንም ቢሉ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እናንተ አብላጫ ናችሁ።

172 አስተውሉ፡ ከዚያ በኋላ፡ ታዘዘ። አሁን በደንብ ስሙ። እግዚአብሔርን፡ ለቃሉ ከታዘዘ በኋላ፡ ተልዕኮውን በፈጸመ ጊዜ፡ በጴንጤቆስጤ የተቀበለው ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነጠቀው፡ አካሉንም ሕያው አደረገው። በብዙ ማይሎች ርቀት፡ በመንፈስ ተወሰደ፡ በሌላ አገር የሆነ ቦታም ተገኘ። የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይል! ጴንጤቆስጤዎች ከሆንን፡ “ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ያው ኃይል፡ በሚሞተው ሰውነታችሁ ውስጥ ቢኖር።” አያችሁ? እሺ። አስተውሉ።

173 ሌላ በዚህ ሕያው በሚያደርግ ኃይል የተሞላ ሰው እንውሰድ። ከረጅም ጊዜ በፊት፡ ሄኖክ የሚባል አንድ ሰው ነበረ። አዲስ ነገር በመጣ ጊዜ፡ የሆነ ነገር መጥቶ፡ “እንግዲህ፡ አሁን ወደ አሮጌው ትምህርት መመለስ አለብን፡ ወይም **ወደዚህ፡ ወደዚያ**፡ ወይም **ወደሌላ** እንመለስ” ባለ ጊዜ፡ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር ተመላለሰ። እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ፡ ሄኖክ አንዲትም ቃል አላሳለፈም። ከእግዚአብሔር ጋር ተመላለሰ። እርሱ ምን ነበር? እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። ለዚያ ዘመን የተጠራ ንስር ነበር።

174 ጊዜው ሲደርስም፡ በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ተሞልቶ ነበር! አስታውሱ፡ በእግዚአብሔር ፊት ለአምስት መቶ ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ ተመላልሷል፡ አንድም ጊዜ ቃሉን አላዛነፈም። አንድም ጊዜ ጠባዩን አላበላሸም። አንድም ጊዜ ቢሆን ምስክሩን ከመጠበቅ በቀር ሌላ አላደረገም። እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ፡ ሄዶ አደረገ። ምንም ክርክር አልነበረም፡ ዝም ብሎ ሄዶ አደረገው። ሌላ ሰው ምንም ቢያስብ፡ ሄዶ አደረገው። ለምን? በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ተሞልቶ ነበርና። ያ አዛውንት የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስም፡ እግዚአብሔር መሰላሉን አወረደና ወደ ቤቱ ተራምዶ ወጣ። ሕያው አደረገው፡ ሟች አካሉንም በንጥቀት ወደ ላይ ወሰደው። አሜን። ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ያ ነው።

175 በምድር ላይ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ፡ ኤልያስን ተመልከቱ። በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ተሞልቶ ነበር፡ በዘመኑ የነበሩትን ያንን የጃኪ ኬኔዲ ዓይነት

የፀጉር አቆራረጥ ይቃወም ነበር። ለአሮጊቷ ኤልዛቤል ስለ እርሷ ያለውን አመለካከት ነግሯት ነበር። ለእነዚያ ሰባኪዎችና ካህናት ትክክለኛውንና ስህተቱን ነግሯቸው ነበር፡ እነርሱ ግን አላመኑትም ነበር። ነገር ግን እነዚያን ፊታቸውን-የሚቀቡ ሴቶችንና መሰል ነገሮችን፡ በጣም ይቃወም ነበር። በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል በጣም ተሞልቶ ስለነበረ ምንም ሊጎዳው አልቻለም። እግዚአብሔር ከሰማያት መግቦታል፡ አውጥቶትም ለብቻው አስቀምጦት ነበር። ሕያው በሚያደርግ ኃይልም ተሞልቶ ነበርና፡ የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ፡ ዮርዳኖስ ተከፈለ፡ እርሱም ዝም ብሎ ተሻገረ፡ ሰረገላም ተልኮለት ወደ ቤቱ ወሰደው፡ በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል እጅግ ተሞልቶ ነበርና። እርሱ እውነተኛና፡ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ። አዎን።

176 አስተውሉ፡ እርሱ ተተኪ ነበረው፡ ሰሙም ኤልሳዕ ይባላል። ኤልሳዕም የዚህ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ እጥፍ ድርሻ ነበረው። አያችሁ? ከእርሱ እጥፍ ድርሻ ነበረው። አሁን፡ ለሰማንያ ዓመታት ያህል ሰበከ፡ ወይም ዕድሜው ሰማንያ ዓመት ገደማ ነበር። ታሞም ሞተ። አሁን፡ እርሱ እንደ ኤልያስ ወደ ቤቱ በንጥቀት አልሄደም። አያችሁ? ሁለቱም እዚያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተወክለዋል፥ አንዳንዶቹ ቅዱሳን ይሄዳሉ፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ያርፋሉ። ነገር ግን ኤልያስ በንጥቀት ወደ ላይ ሲወሰድ፥ ኤልሳዕ ግን በሕያው የሚያደርግ ኃይል ተሞልቶ፡ በእግዚአብሔር፡ አንቀላፋ። ከመሞቱ በፊት ትንቢቱን ተመልከቱ። አያችሁ?

177 አሁን፡ ላሳያችሁ። ብትሞቱም፡ ወይም የትም ብትሆኑ ግድ የለኝም፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ፈጽሞ አይለቅም። ከሞተ ከብዙ ዓመታት በኋላ፡ ሥጋው በሰብሶ፡ ትሎችም በልተውት ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን፡ የሞተ ሰው ተሸክመው ሲሄዱ፡ በዚያ አጥንት ላይ ጣሉት፡ በዚያም ውስጥ ያ ሰው እንደገና ወደ ሕይወት እስኪመለስ ድረስ የሚያደርግ ታላቅ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነበር። ሃሌሉያ! በዚያ የእግዚአብሔር ቅዱስ ላይ የነበረው፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ ፈጽሞ ሰላልተለየውና በዚያ አጥንቶች ላይ ሰለቆየ፡ ከሙታን አስነሳው።

178 ኦህ፡ አስታውሱ፡ የእርሱ ሙሽራ ከሆንን፡ ከሥጋው ሥጋ፡ ከአጥንቱም አጥንት ነን። ሞት ያንን ሕያው የሚያደርግ ኃይል ምንም አይረብሸውም። “ምንም እንኳ ትሎች ይህንን አካል ቢያጠፉትም፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን አያለሁ።” ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ምንኛ... ምን እንደምል አላውቅም። እንደ እኔ ላለ ሽማግሌ ሰው፡ በሃምሳ-ሰድሰት ዓመቴ የመጨረሻው ዘመኔ በቅርቡ እንደሚመጣ እያወቅሁ፡ ይህ ምንኛ ታላቅ ተስፋ ነው።

179 ከትንሽነቴ ጀምሮ፡ ይህንን ለማብሰር እዚህ ቆሜአለሁ። ነገር ግን በእኔ ውስጥ ያለ፡ ምንም ጥሩ ነገር እንደሌለ፡ ያደረግሁትም፡ ምንም ነገር እንደሌለ አውቃለሁ፡ ነገር ግን በውስጤ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል አለ፥ እርሱም አንድ ቀን በወጣትነቴ፡ ከዓለም ነገሮች፡ ወደ ዘላለም ሕይወት ሕያው አደረገኝ። ኦህ፡ የሆኑት ነገሮች! ራእዮችን አይቻለሁ፡ ነገሮችንም አስቀድሜ ተናግሬአለሁ። እርሱ እስካሁን አንዲትም ነገር እንዲወድቅ አላደረገም። በሌሎች ልሳኖች ተናግሬአለሁ። ትንቢት ተናግሬአለሁ። እነዚህን ሁሉ ያደረግሁት በውስጤ በሚኖረው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነው። አንድ ቀን...

180 ቤዛዬ አሁን ሕያው ነው። አንድ ቀን እርሱ በሚመጣበት ጊዜ፡ እነዚህ አጥንቶች በአየር ላይ እርሱን ለመገናኘት፡ እንደገና ይነሳሉ። በባሕር ውስጥ ብትቀብሩኝ፡ ብታቃጥሉትም፡ በፈለጋችሁበት ቦታ ብታደርጉት ግድ የለም። ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ዘላለማዊ ነው። ዊው! አሁን የትንሣኤው ስሜት ይሰማኛል። አዎ፡ ጌታዬ። ለዓመታት ነበረኝ። በውስጤ ነው።

181 በእናንተ ውስጥ ነው። ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ በሚሞተው አካላችሁ፡ ውስጥ፡ ቢኖር፡ ከዓለም ነገሮች ለይቶ፡ ወደ እግዚአብሔር ቃል ብቻ ሕያው አድርጎአችኋል። ከዚህ ሕይወት ወደ ዘላለም ሕይወት ሕያው አድርጎአችኋል። ቀድሞ በኃጢአትና በበደል ሙታን የነበራችሁ አሁን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር በሰማያዊ ሰፍራ ለመቀመጥ፡ ከላይ በሚመጣው መና ለመመገብ፡ የእግዚአብሔር እጅ ሲገለጥ ለማየትና፡ የዚህን ዘመን ተስፋ ለማረጋገጥ፡ አብራችሁ ሕያው ተደርጋችኋል።

182 "በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል። ሲበሉ፡ ሲጠጡ፡ ሲያገቡና፡ ለጋብቻም ሲሰጡ ነበር። በሎጥ ዘመንም እንደነበረው፡ የሰው ልጅ በምድር ላይ በሚገለጥበት ሰዓት እንዲሁ ይሆናል፡" ከእንግዲህ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ አይደለም። ያ ንስር በሚበርበት በመጨረሻው ዘመን እንደ ትንቢታዊ መልእክት "የሰው ልጅ፡" ሆኖ ይመለሳል፥ አንበሳ ሆኖ አይደለም፥ ወይም በመሥዋዕት ዘመን እንደነበረው በሬ ሆኖ አይደለም። አያችሁ?

183 በእያንዳንዱ ጊዜ፡ የሃይማኖት ኃይል የዓለምን ፖለቲካዊ ኃይል ተግዳሮት ለመጋፈጥ ይወጣ ነበር። አንበሳው፡ ይኸውም የሃይማኖት ኃይል በተነሳ ጊዜ፡ የሮማውያንን ኃይል ለመጋፈጥ ሄደ።

184 ከዚያም የመሥዋዕቱ ሰዓት ሲመጣ፡ በሬው ሄደ፡ እርሱ የጌታ የመሥዋዕት እንስሳ ነውና።

185 ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ፡ ተሐድሶ አድራጊዎች መጡ፡ የሰው ፊት ያለው ፍጥረት መጣ። ተሐድሶ አድራጊዎቹም ከሉተር፡ ከዌስሊ፡ ኦህ፡ ከካልቪን ጀምሮ፡ እስከ ጴንጤቆስጤ ዘመን ድረስ፡ ወደ ታች፡ ቀጠሉ።

186 ነገር ግን በወጣው በመጨረሻው መልእክት፡ የሚበር ንስር መጣ። አሁን የንስር ጊዜ ነው፡ የመገለጥ ዘመን ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል የተገለጠበት፡ የእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠበት ጊዜ ነው። ኦህ፡ ልጆች ሆይ፡ ወደዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግቡ። ግቡና በፍጹም ልባችሁ፡ እመኑት፡ እግዚአብሔርም ይሞላችኋል።

187 አሁን እዚህ ጋር ተመልከቱ። አሁን፡ አስታውሱ፡ "እኛ ከሥጋው ሥጋ፡ ከአጥንቱም አጥንት" እንደሆንን እናገኛለን። እግዚአብሔር አጥንቱንና ሥጋውን ከመቃብር እንዳስነሳው ሁሉ፡ መያዣው ያለውን ሰው መደበቅ አይችሉም። ሞት ሊይዘው አይችልም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣሉ። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳቸዋለሁ።" ኦህ፡ ማይ! ትንሣኤ! ምክንያቱም፡ እኛ እኮ ልክ በትንሣኤ ውስጥ ነን። እርሱ ሲነሳ፡ እኛም ከእርሱ ጋር ተነስተናል። የባለቤትነት ማረጋገጫውን መልሶ ልኳል። እኛም እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ይዘነዋል። "እርሱ ለዘላለም ሕያው ነው፥ ትናንት፡

ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።” ዕብራውያን 13፡8 ይህንን ያረጋግጣል። እርሱ ያው ነው።

188 የእርሱ መሲሐዊ የሆኑት፡ የተቀቡት ይህንን ያምናሉ። መሲሕ ምንድን ነው? መሲሕ ምንድን ነው? **መሲሕ** ማለት “የተቀባው” ማለት ነው። አሁንም እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ይፈጽም ዘንድ፡ ቤዛና፡ የተቀባው ይሆን ዘንድ፡ ለዚያ ቀን የተቀባው በመሆኑ መሲሕ ከሆነ፡ እግዚአብሔርም ያንን አካል ካስነሳው፡ የእርሱ ሙሽራ ለዚህ ዘመን የተቀባችው ናት፡ እርሷም ቀድሞውኑ በትንሣኤ ከእርሱ ጋር ተነስታለች፡ ምክንያቱም፡ “እነዚህ ሁለቱ አንድ ናቸውና።” አሜን።

189 ያ—ያየሁትን ያህል በዚያው መንገድ መናገር በቻልኩ እላለሁ። ይህን ለማድረግ የሚያስችል ዕውቀትና ትምህርት በኖረኝ እመኛለሁ። አያችሁ? እ—እንደምታዩት ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር፡ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ፡ ምን ማለቴ እንደሆነ እንድታዩ ያንን በልባችሁ ውስጥ እንዲያኖረው፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

190 ትንሣኤ፡ አሁን በትንሣኤ ውስጥ ነን። በትንሣኤ ከእርሱ ጋር ተቀምጠናል፡ ነገር ግን ሕይወት ያላቸው ብቻ ናቸው የተቀመጡት።

191 ሕይወት የሌላቸው ግን አይደሉም። እነርሱ አያውቁትም። ፈጽሞ አያውቁትም። መንፈስ ቅዱስን እየተቀበልን ነው፡ እየዳንን ነው እያሉ ያስባሉ፡ ነገር ግን ንጥቀቱም አስቀድሞ አልፏቸው ይሄዳል። “ኤልያስ አስቀድሞ መጥቷል፡ እንደወደዱም አደረጉበት፡ እናንተ ግን አላወቃችሁትም፡” አለ። አያችሁ?

192 አስተውሉ። ሞት የእግዚአብሔርን ሕያው የሚያደርግ ኃይል ሊያስቆመው አይችልም። አስተውሉ። ሞት ሊያግደው አይችልም።

193 እናንተም፡ “እንግዲህ፡ እናቴ በመንፈስ-የተሞላች ሴት ነበረች። አባቴም ቢሆን፡ እንደ እርሱ በኃይል የተሞላ ሰው አይቼ አላውቅም። ነገር ግን ሞተ፡ ወንድም ብራንሃም” ትሉ ይሆናል። እርግጥ ነው። ያ ግን ሕያው የሚያደርገውን ኃይል አላቆመውም።

194 ሙሴ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነበረው። ይህን ታምናላችሁ? ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ፡ በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ ሰው አልነበረም። ምክንያቱም ራእይን ማየት ብቻ ሳይሆን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት-ለ-ፊት ይነጋገር ነበርና።

195 አንዲት ነቢይት፡ ማርያም እንኳ፡ በአንድ ወቅት ቃሉን ተቃወመች። እርሱም፡ “እግዚአብሔርን አትፈሩም? አገልጋዬን ሙሴን፡ አስቡ። በዚህ ዘመን፡ በዓለም ላይ እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም። እንደ ሙሴ ያለ ማንም አልነበረም። እኔ ሙሴን አነጋግረዋለሁ። እርሱ ተናግሮ፡ እውነት ያልሆነ ምን አለ? አያችሁ? እኔ ሙሴን እናገራለሁ። እግዚአብሔርን አትፈሩምን? በእርሱ ላይ አንዲትም ቃል አትናገሩ” አላት። በዚያውም ቅጽበት በ—በለምጽ ተመታችና ልትሞት ደረሰች። ከዚያም በኋላ፡ ብዙም አልቆየችም። ሙሴ ግን ጸለየላት።

196 ሙሴም ከመቶ ሃያ ዓመት አገልግሎት በኋላ፡ ወይም ከሰማንያ ዓመት አገልግሎት በኋላ፡ ወደ ተራራው ወጣ፥ ከመቶ ሃያ ዓመት ህይወት በኋላ፡ ወደ ተራራ ወጣና ሞተ፡ በሸለቆ ውስጥም ተቀበረ። ነገር ግን ያ ሕያው የሚያደርግ

ኃይል በእርሱ ላይ ነበር። ከሰምንት መቶ ዓመታት ገደማ በኋላም፡ እነሆ፡ በመገለጥ ተራራ ላይ ቆሞ ታየ። አሜን። እርሱ ምን ነበር? በዚያ ትንሣኤ ውስጥ ተካትቶ ነበር። እርግጥ ነው፡ ተካትቶ ነበር። የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነበረው። እነሆም፡ ቆሞ ታየ።

197 ኢዮብን፡ አብርሃምን፡ ይስሐቅን፡ በትንሣኤ ቀን የነበሩትን ቅዱሳን ተመልከቱ፡ ኢዮብና እነዚያ ሁሉ ያ ታላቅ ማለዳ እንደሚመጣ ያውቁ ነበር። ከክርስቶስ በመቶዎች ከሚቆጠሩ፡ ዓመታት በፊት፡ "ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ አውቃለሁ፡" ባለ ጊዜ ያውቅ ነበር። በእርግጥም፡ የኢዮብ መጽሐፍ፡ ከዘፍጥረት በፊት እንደተጻፈ፡ ይነገራል፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ጥንታዊው መጽሐፍ ነው።

198 አሁን እኛ እንደምንለፍበት ሁሉ፡ እርሱም በመከራ ውስጥ ነበር። ባለቤቱ፡ እንኳ፡ በምድር ላይ ለእርሱ እጅግ ቅርብ የሆነችው ሰው፡ "እግዚአብሔርን ሰድበህ ለምን አትሞትም? " አለችው፡

199 እርሱ ግን፡ "እንደ ሰነፍ ሴት ተናገርሽ። እግዚአብሔር ሰጠ፡ እግዚአብሔርም ነሳ፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን" አላት።

200 ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በወረደና፡ ትንቢት መናገር በጀመረ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ፡ በመጨረሻውም ቀን በምድር ላይ እንደሚቆም አውቃለሁ። ምንም እንኳ ትሎች ይህን አካል ቢያጠፉትም፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን እያለሁ" አለ። የሚቀበርበትንም ቦታ አዘጋጀ። "ይህንን መሬት እንገዛለን፡" አለ። እዚያም ገዛና ራሱን ቀበረ።

201 በኋላም፡ አብርሃም የተባለ ሰው መጣ። ቤተ ክርስቲያኒቱ እያደገችና፡ እየተሰፋፋች መጣች። አሁን፡ አብርሃምም፡ እንዲሁ፡ እግዚአብሔር ሰለጠራው፡ ዘላለማዊ፡ የዘላለም ሕይወት፡ ይኸውም፡ የእግዚአብሔር መያዣ ነበረው። አሁን አስተውሉ። እርሱ በሞተ ጊዜ፡ ወይም ሣራ በሞተች ጊዜ፡ በፍልስጤም ውስጥ፡ በኢዮብ መቃብር አቅራቢያ፡ አንዲት መሬት ገዛና ሣራን ቀበራት። አብርሃምም ሞተና ከሣራ ጋር ተቀበረ። አብርሃምም ይ—ይስሐቅን ወለደ።

202 ይስሐቅም፡ በሞተ ጊዜ፡ በዚያው መሬት ውስጥ፡ ከአብርሃም ጋር አንቀላፋ። አሁን፡ ይስሐቅም ያዕቆብን፡ በወለደ ጊዜ...

203 ያዕቆብ እዚያው ግብፅ ውስጥ፡ ሞተ። ነገር ግን ነቢይ በመሆኑ፡ አሁን፡ ይህ መያዣ፡ ይኸውም ሕያው የሚያደርግ ኃይል ሰለነበረው፡ እንዲህ አለ፡ "ዮሴፍ ሆይ፡ እዚህ እንዳትቀብረኝ። ነቢይ ልጄ ሆይ፡ ወደዚህ ና። እግዚአብሔር ባነከሰኝ በዚያ ወገቤ ላይ እጅህን ጫን። እዚህ እንደማትቀብረኝም በሰማይ አምላክ ማልልኝ" አለው። በዚያ ሰው ውስጥ ምን ነበረ? ግብፅስ እንደማንኛውም ቦታ ለምን ጥሩ አልሆነችም? እርሱ ነቢይ ነበር። ያ ትንሣኤ የት እንደሚሆን ያውቅ ነበር። በግብፅ ሳይሆን፥ በፍልስጤም ውስጥ እንደሚሆን ያውቅ ነበር። እንዲህም አለ፡ "በዚያ ባነከሰኝ ወገቤ ላይ እጅህን ጫን፡ ባገለገልኩትም አምላክ ማልልኝ። አንተ ነቢይ ልጄ ነህና፡ እነሆ፡ አጥንቴን እዚህ እንዳትቀብረው። ወደዚያ ማዶ ወሰደህ ቅበረኝ።"

204 ዮሴፍም፡ እንዲሁ፡ ነቢይ ሰለነበረ፡ ባነከሰ አባቱ ላይ እጁን ጫነ። እንዲህም አለ፡ "በአብርሃም፡ በይስሐቅና፡ በያዕቆብ አምላክ እምላለሁ፡ እዚህ አልቀብርህም" አለ። ወሰደውም በዚያች ምድር ቀበሩት። ለምን? ለምን?

205 ዮሴፍም በሞተ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ “እዚህ እንዳትቀብሩኝ። እዚህ እንዳትቀብሩኝ።” ለምን? እግዚአብሔር በየትኛውም ቦታ አምላክ ቢሆንም፡ እርሱ ግን ዕቅድ አለው። ዮሴፍ ነቢይ ነበር። እንዲህም አለ፡ “አንድ ቀን፡” ቃሉን፡ አዳምጡ፡ “ጌታ አምላክ ይ-ጎ-... ይጎበኛችኋል፡ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል። በምትሄዱበትም ጊዜ፡ አጥንቴን ይዛችሁ ሂዱ።”

206 ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል በእነዚያ አጥንቶች ውስጥ ነበር። ኦህ! “ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ፡ በእናንተ ቢኖር፡ እርሱ ለሚሞተው ሥጋችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።”

207 “አጥንቴን እዚህ እንዳታስቀምጡት። እዚያ ከተሰፋው ቃል ሰዎች ጋር አብራችሁ ቅበሩት።”

208 ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፡ እዚህ ጋር፡ አንድ ጥቅስ አለኝ፡ ማቴዎስ 27፡ 51። ኢየሱስ ከሙታን በተነሳ ጊዜ፡ ኢዮብ ይህ መምጣቱን አይቶ ነበር፡ እንዲህ አለ፡ “ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ አውቃለሁ። በመጨረሻው ዘመንም፡ በምድር ላይ ይቆማል። ምንም እንኳ ትሎች ይህን አካል ቢያጠፉትም፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን እያለሁ። እየዋለሁ።” ያውቁ ነበር። እርሱ ነቢይ ነበር። አብርሃም ነቢይ ነበር። ይስሐቅ ነቢይ ነበር። ያዕቆብ ነቢይ ነበር። ዮሴፍም ነቢይ ነበር። እንደ ቃሉም፡ የእግዚአብሔር መገለጥ ነበራቸው። በዚያም የትንሣኤ ማለዳ፡ ያ መጥቶ በእርሱ ያመኑትን ሁሉ በተቤዠ ጊዜ፡ እነርሱም፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ አብረው ተነሱ።

209 ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ የአጥንቶቹ ትቢያ እንኳ አንዲት ማንኪያ በማይሞላበት በዚያ በኢዮብ መቃብር ውስጥ ገባ። ከእነዚያ ሁሉ በመቶዎች፡ በመቶዎችና፡ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በኋላ፡ አጥንቶቹ በሰብሰው ነበር። ተ—ተመልሶ ሄደ፡ ወደ ምድር ጋዝነት ተለውጦ ነበር፡ እንዲሁ ተራ ትቢያ ብቻ ነበር እዚያ የቀረው። ነገር ግን፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ እንደ እግዚአብሔር ቃሉና፡ እንደ ተሰፋው፡ በመቶዎች፡ አዎ፡ በሺዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በኋላ፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ከመቃብር ሲወጣ፥ ኢዮብ፡ አብርሃም፡ ይስሐቅ፡ ያዕቆብ፡ ሁሉም፡ ከእርሱ ጋር ከመቃብር ወጡ።

210 መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላል። ቅዱስ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 27 ከቁጥር 51 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ቅዱሳን ብዙዎች ተነሱ፡ እርሱም በትንሣኤ ማለዳ ሲነሳ፡ ከእርሱ ጋር ተነሱ ከመቃብር ወጡ።” ለምን? ያ መያዣ ነበራቸው። ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነበራቸው፡ አያችሁ፡ ከሙታንም ተነስተው፡ በትንሣኤው ከእርሱ ጋር ሄዱ። በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል ተሞልተው ስለነበር፡ ከእርሱ ጋር በትንሣኤው ደስ አላቸው። ያ እውነተኛ የትንሣኤ ማኅተም ነበራቸው።

“ደህና፡” እናንተም፡ “ምነው በብሉይ ኪዳን በኖርኩ” ትሉ ይሆናል።

211 አንድ አፍታ ቆዩ። በ1ኛ ተሰሎ-... ተሰሎንቄ፡ ምዕራፍ 4፡ ከቁጥር 16 ላይ ያለውን፡ እንድታነቡት እፈልጋለሁ። “ወንድሞች ሆይ፡ ተስፋ እንደሌላቸው፡ እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፡ አንቀላፍተው ስላሉቱ፡ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደ ሞተና፡ እንደ ተነሣ ካመንን፡” እንዲሁ እንዲሁ የምናስመስል-ሳይሆን፡ ነገር ግን በእውነት እናምናለን፡ “እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።”

212 ሕያው የሚያደርግ ኃይል ያላቸው የአዲስ ኪዳን ቅዱሳንም፡ እንዲሁ፡ በሁለተኛው መምጣቱ ጊዜ፡ ይነሳሉ፥ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሁሉ በአጥንታቸው ላይ ሕያው የሚያደርግ ኃይል እንደነበረው ሁሉ፡ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር የሚያሳዩ፡ መነጠቆች ኃይሎችና፡ የመሳሰሉት በእርግጥ ይነሳሉ። የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸው እነዚያ ነቢያት፡ በዚያ የትንሣኤ ማለዳ ከእርሱ ጋር ተነሱ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ እያንዳንዱም ሰው የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይልም በአጥንቶቹ ላይ ያለው ሰው፡ በትንሣኤው ከእርሱ ጋር እንደሚመጣ በተገባው በእግዚአብሔር ተስፋ ከእርሱ ጋር ተነሱ።

213 በታመሙት ላይ እጃችንን መጫናችን፡ እያስደንቅም። እርስ በርሳችንም የምንዋደደው፡ እያስደንቅም። ወንድማማቾችና እህትማማቾች ነን።' በእግዚአብሔር ቃል ስለታረምን እርስ በርስ ልንጠላላ አይገባም። እርስ በርስ ልንዋደድና፡ ልንከባበር ይገባል። ታውቃላችሁ፡ ይህን ካላደረጋችሁ፡ አይጠቅማችሁም።

214 አሁን በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ እዚሁ፡ የተቀመጠ አንድ ሰው አለ። ከጥቂት ቀናት በፊት... ያ ሰው ያምናል። ይህ ልጅ ጆሮው ላይ ካንሰር ነበረበት፡ ነገር ግን ስለ እሱ ምንም አይናገርም ነበር። እዚያ እቤት ውስጥ ይሠራ ነበር። ከእርሱ፡ ከሞዝሊ ወንድሞችና፡ እዚህ ካለው ወንድም ዳውሰን ጋር አደን ሄደን ነበር። እዚህ ከወንድም ዊሊያም ልጅ ጋር፡ እያደንን ነበር። በአጋጣሚ ወደ ጆሮው ተመለከትኩና፡ ጆሮው በጣም አብጦ አየሁ፡ እናም፡ እኔም አልኩት፡ "ዶናቫን፡ ምን ሆነሃል? ይሄኛው ጆሮ!"

215 እርሱም፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ብዙ ጊዜው ነው። ምን እንደሆነ አላውቅም" አለኝ።

216 እ—እዚያው እጁን ያዝኩት። ጆሮው ላይ ትልቅ ካንሰር ነበረ። አንዲትም ቃል አልተናገርኩም፥ ዝም ብዬ ያዝኩትና፡ "ወንድሜ፡" ብዬ አሰብኩ! ከዚያ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ፡ ጠባሳ እንኳ አልቀረም ነበር። ለሰማይ አምላክ የነበረው እክብሮት፡ በዚያም ሕያው በሚያደርገው ኃይል፡ ያንን ካንሰር ገደለውና እዚያ ኋላ ያለው የዶናቫን ዊርትስንም ሕይወት አተረፈ። በትክክል።

217 እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው? እዚህ ፊኒክስ ያላችሁ ሰዎች ሆይ፡ ተመልከቱ። ይህንን ያመናችሁትን ራሳችሁን ተመልከቱ። ይህ ያላቸውንና፡ እጃቸውን በእናንተ ላይ የሚጭኑትን ሰዎች ተመልከቱ። ምን እንደሚፈጠር ተመልከቱ። ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነው። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።" በታመሙት ላይ እጃቸውን ቢጭኑ፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ ከንስር ወደ ንስር፡ የሆነ ነገር ይሆናል። አሁን፡ ከንስር ወደ አሞራ፡ አይሠራም። ንስር ወደ ንስር፡ ከጓሮ በረት፡ ወደ ሰማያዊው ከፍታ ያነሳል። ሁለቱም በእምነት ውስጥ ሲሆኑ፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።"

218 ያው የእግዚአብሔር ሕያው የሚያደርግ ኃይል በእነዚህ በሁለቱ ነቢያት፡ በኤልያስና በኤልሳዕ ውስጥ ተወክሎ ተመልከቱ። አስተውሉ፡ ያው ቃል ነው፥ አንደኛው **መድረስ** ሲሆን፡ ሌላኛው ደግሞ **መነጠቅ** ነው። **መድረስና መነጠቅ**። አያችሁ? እርሱ ተነጥቆ ነበር። እኛ ደግሞ እንደርስባቸዋለን፥ በአየር ላይ እንገናኛቸዋለን። "በአየር ላይ ልንገናኛቸው እንነጠቃለን።"

219 አስተውሉ፡ አንድ ወፍ ራሱን ለማመጣጠን፡ ሁለት ክንፎች ያስፈልጉታል። ልክ ነው? ኤልያስ የመነጠቅ ክንፍ ነበረ፡ ኤልያስ። ኤልሳዕ ደግሞ የትንሣኤ ክንፍ ነበረ። አያችሁ? ሁለቱም፡ በአንድነት፡ በሕይወት ያሉትን ቅዱሳንና አልፈው የሄዱትን ቅዱሳን ይወክላሉ።

220 አስታውሱ፡ ከጊዜ መጋረጃ ባሻገር አልፈው እንዲያዩ፡ ሕያዋን ተደርገዋል። እነዚያ ነቢያት፥ መጋረጃውን አልፈው እንዲመለከቱና እስከዚህ ዘመን ድረስ እንዲያዩ በዚያን ጊዜ እንዴት ሕያው ተደርገው ነበር!

221 ጳውሎስን ተመልከቱ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት እነዚህ ሰዎች ምን እንደሚመስሉ፡ ምን እንደሚያደርጉና ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው እንደሚጠሩ ተናግሯል። ሕያው በሚያደርግ ኃይል የተሞላ፡ ነቢይ ነበር፡ እንደሚፈጸምም አስቀድሞ ተመልክቷል። ይህንን እናምናለን፡ አይደል? እርሱ ሕያው የሚያደርገውን ኃይል ተቀብሎ ነበር።

222 ዛሬ ያለውን ሕያው የሚያደርግ ኃይል ተመልከቱ፡ አንዲትም ክስተት ሳይቀር፡ ነገሮችን አስቀድሞ ይናገራል። አንድም ጊዜ አይወድቅም። ሕያው የሚያደርግ ኃይል፥ የሰው ኃይል አይደለም፡ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። የትንሣኤው ማረጋገጫ፡ የሆነው ኃይል፡ ቀድሞውኑ ከእርሱ ጋር ሕያው እንደሆንን ዋስትና እንዲሆነን፡ የይዞታ ማረጋገጫ የላከው ከሙታን የተነሳው ኢየሱስ ነው።

223 አስተውሉ፡ እዚህ ያላችሁ ቢዝነስ ሜን፡ **ከጊዜ መጋረጃ አልፎ ማየት**፡ የምትለውን ያችን ትንሽ መጽሐፍ ታስታውሳላችሁ?

224 ዕድሜዬም እየገፋ ሲመጣና፡ ቀኖቼ እያጠሩ መሆናቸውን ሳውቅ፡ በእውነቱ... ከጥቂት ጊዜ በፊት እነዚያ እመቤቶች የዘመሩትን፡ አሁን ለአሥራ ሰምንት፡ ወይም ለሃያ ዓመታት ያህል የነበረኝን፡ **ጌታ ሆይ፡ ከእርሱ ጋር ማውራት እፈልጋለሁ** የምትለውን መዝሙር እከፍታለሁ፡ ከዚያም ወደ ውጭ ወጥቼ መጸለይ እጀምራለሁ፡ ያኔ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ይመጣል፡ እረፍትም አገኛለሁ፡ ቀና ብዬ እመለከትና፡ “ወደዚያ ማዶ ተመልከት፡” እላለሁ!

225 በዚያች ማለዳ፡ ወደዚያ ባሻገር መነጠቄን አስታውሳለሁ። ባለቤቴ፡ እዚያ ኋላ የተቀመተችው፡ በዚያች ማለዳ ከአጠገቤ በአንድ አልጋ ላይ ተኝታ ነበር። ተነሳሁና፡ ቀና ብዬ ተመለከትኩ። እሷም፡ ተኝታለች። እኔም፡ “ለጌታ አንድ ነገር ለማድረግ ካሰብኩ፡ ብትፈጥን ይሻላል፡ ጃል። ሃምሳ ዓመት አልፎሃል” አልኩኝ። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ነጠቀኝ፡ ወደዚያም ተመለከትኩ። እዚህ በዚህ ጠረጴዛ አጠገብ፡ ይህ የተከበረ ቅዱስ መጽሐፍ እዚህ ተቀምጦ፡ የወንጌል አገልጋይ ሆኜ እንደቆምኩት ሁሉ፡ በእርግጠኝነት እነዚያን ቅዱሳን አየሁ።

226 እኔ በጌታ ስም ተናግሬ ያልተፈጸመ ነገር ነግሬያችሁ አውቃለሁን? ካለ፡ እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ። በመድረክ ላይ በነበረን፡ ጊዜ ሁሉ፡ ነገሩ ፍጹም ትክክል አልነበረምን? ሁልጊዜም፡ ልክ እርሱ እንዳለው አልሆነምን? ይህ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነበረ።

227 እዚያ ቆሜ፡ ያንን ጊዜ ተመለከትኩ። በሺዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ፡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች፡ እየሮጡ ሲመጡ፡ ሲያቅፉኝና፡ ሲጮሁ አየሁ። ዞር ብዬ

ወደኋላ ስመለከት አልጋው ላይ ተኝቼ ራሴን አየሁት። “ኦ ጌታ ሆይ፡ የጊዜውን መጋረጃ አልፌ እንድመለከት ፍቀድልኝ።”

228 ምንድነው እርሱ? እኛን የሚነጥቀን ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነው። ያ ታላቅ ሕያው የሚያደርግ ኃይል። በመጨረሻዎቹ ቀናት የመጣው ሕያው የሚያደርግ ኃይል።

229 አሁን፡ እዚህ አሪዞና ውስጥ ያለሁት ለዚሁ ነው። እዚህ ፊኒክስ ውስጥ፡ በዚሁ መድረክ ላይ ቆሜ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**” ብዬ ስናገር የሰሙኝ፡ ብዙ ሰዎች እዚህ ተቀምጠዋል። ሰንቶቻችሁ ታስታውሳላችሁ? “አሁን ሂዱ። የሆነ ነገር ሊፈጠር ነው” እል ነበር።

230 ሰባት መላእክት ሲመጡ አየሁ። ሃያ-ሰባት ማይል ከፍታና፡ ሰላሳ ማይል ሰፋት ሆኖ፡ ደመናው፡ እዚህ ሲንሳፈፍ **ላይፍ** መጽሔት አላወጣውም ወይ? ፍሬድ ሶሰማን፡ እነዚህ ሌሎቹ፡ ጂን ኖርማንና፡ እነርሱ፡ እዚያ ኋላ የተቀመጡት አላዩትምን? እነዚያ ሰባቱ መላእክት እዚያ ኮረብታው ላይ ሲገለጡ እዚያው ቆመው ነበር። በዙሪያው ያሉትን ኮረብታዎች፡ ለብዙ ማይሎች ያህል፡ እንዲህ አናወጣቸው። ሰባት መላእክት እዚያ ቆመው ነበር። በእጄ ሰይፍ አሰጨበጡና፡ “ወደ ቤትህ ሂድና የተሰጡህን እነዚህን ሰባቱን ማኅተሞች ክፈት፡” አሉ። ይኸውና፡ ስለ ጋብቻና ፍቺ፡ ስለ እባቡ ዘርና ስለ እነዚህ ሁሉ ሲከራከሩባቸው የነበሩት ነገሮች፡ እውነተኛው ምስጢር እዚህ አሉ። ይህም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው።

231 ምንድን ነው እሱ? ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጣ፡ እርሷንም ወደምንጠጋበት ወደዚህ ሰዓት የሚያዘጋጃት፡ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነው። ሕያው የሚያደርግ ኃይል!

ኦ አምላክ ሆይ፡ እንድንቀበለው እርዳን። እንድናምነውም እርዳን።

232 አያችሁ፡ ሆኖም ግን ይጠቅማችሁ እንደሆነ፡ ወይም እንዳልሆነ፡ የሚወስነው፡ ለርሱ ባላችሁ አመለካከት ላይ ነው። አያችሁ? ያንን ማመን አለባችሁ። ካላመናችሁት፡ ቅንጣት ያህል ጥቅም አይሰጣችሁም።

233 ሽማግሌው ሳሙኤል በዚያ ሕዝብ ፊት ቆሞ፡ እንዴት እንዲህ እንዳለ፡ “እኔ በጌታ ስም ተናግሬ ያልተፈጸመ ነገር ነግሬያችሁ አውቃለሁን? ለመኖርያዬስ፡ ከእናንተ ገንዘብ ለመንኩን? ”

“አይ፡ ነገር ግን ለማንኛውም፡ ንጉሥ እንፈልጋለን” አሉ።

234 ዛሬም ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ናት። የገዛ ሐሳባቸውን ይፈልጋሉ። ለእናንተ ቅንጣት ያህል ትኩረት አይሰጡም። ዝም ብለው ያልፋሉ። እንግዲህ፡ ይህም የሚያሳየው፡ ሕያው የሚያደርገው ኃይል እዚያ አለመኖሩን ነው።

235 “ኦህ፡” እናንተም፡ “እንግዲህ፡ በልሳን ተናግሬያለሁ። ዘልያለሁና ጮኼያለሁም” ትላላችሁ። ያ ሁሉ መልካም ነው።

236 ነገር ግን ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል እዚያ ካለ፡ ትረዱታላችሁ። ልክ እንደዚያች ትንሽ ንሰር፥ ያቺ እናቱ ናት። ያ ቃሉ ነው። ያ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠው ያንን ነው። አስቀድሞ የተነገረውም ያንን ነው። በትክክል የሆነውም ያው ነው። ያለምንም

ጥርጥር፡ አሁን በመያዣ ደረጃ በትንሣኤ ውስጥ ነን፡ ቅዱሳኑም በአየር ላይ ለመነጠቅ እየተዘጋጁ ነው።

237 ስለዚህ፡ ኢየሱስ፡ በዚህ ሕያው በሚያደርግ ኃይል እጅግ ተሞልቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ለመገንባት አርባ ዓመት የፈጀባችሁ፡ የመሰላችሁን፡ ይህን ቤተ መቅደስ ብታፈርሱት፡ በሦስት ቀን ውስጥ አስነሳዋለሁ።”

238 ለምን? ለምን ኢየሱስ እንዲህ ሊል ይችላል? ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ኢየሱስ እንደዚህ ያለ ነገር ለምን ሊናገር ይችላል? ራሱ መሆኑን ያውቅ ነበር። አሜን። ይህ ልባችሁ ውስጥ እንዲሰረጽ ማድረግ በቻልኩ እመኛለሁ። እሱ ማን እንደነበረ ያውቅ ነበር። ያውቅ ነበር፡ እያንዳንድን ቃል፡ እግዚአብሔር ስለ እርሱ የጻፈውን እያንዳንዱን ቃል፡ ፈጽሟል። ዳዊት የተናገረው ስለእሱ መሆኑን ያውቅ ነበር።

239 መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ስለ እናንተ ሰዎች መሆኑን ታውቃላችሁን? በክርስቶስ ያላችሁን ስፍራ ታውቃላችሁን? በክርስቶስ ከሆናችሁ፡ አዲስ ፍጥረት ናችሁ። ይህ ቃል ለእናንተ፡ እንደ ዕለት ተዕለት ሕይወት መሆኑን ታውቃላችሁን? ታዲያስ፡ እርግጥ ነው። የእናንተ ነው። እናንተ ንስር ናችሁ። ምግባችሁም ያ ነው።

240 በእግዚአብሔር ኃይል፡ እንደሚያደርገው፡ ያውቅ ነበር፡ ምክንያቱም እንደሚያደርገው ትንቢት ተነግሮ ነበርና። እንዲህ ለማለት ያልፈራው ለዚህ ነው፡ “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት። በሦስት ቀን ውስጥም አስነሳዋለ፡ ምክንያቱም ዳዊት ብሏል፡ ‘ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም፡ ቅዱስህንም መበሰበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።’” ከሰውነቱ አንድም ህዋስ እንደማይበሰብስ ያውቅ ነበር። በሰባ-ሁለት ሰዓት ውስጥ መበስበስ ይጀምራል። “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት። በነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ፡ እንደገና አስነሳዋለሁ፡” አለ። ለምን? እያንዳንዱን ቃል ሕያው በሚያደርገው በዚያ ሕያው በሚያደርግ ኃይል እጅግ ተሞልቶ ነበርና። ወደ ኋላ መለስ ብሎ እግዚአብሔር ስለ እርሱ የጻፈውን ቃል ሁሉ ተመለከተ፡ ነቢዩም እንደፈጸመው ተናገረ። ይህም ደግሞ፡ እንደሚፈጸም ያውቅ ነበር።

241 አሁን፡ እግዚአብሔር በተናገረው በእያንዳንዱ ቃል ላይ፡ መንፈሳችሁ “አሜን” ብሏልን፡ እንደ አማኝ፡ በሕይወታችሁ ተፈጽሟልን?

242 በሆነ ነገር ላይ ወደኋላ ብላችሁ፡ “እንግዲህ፡ ቤተ ክርስቲያኔ የምታስተምረው ሌላ ነው፡” ትላላችሁን? እንግዲያውስ ጭልፊት ሆይ፡ ተጠንቀቅ።

243 አስተውሉ። ንስሮች ያምናሉ። በእነርሱ፡ ምንም ጥያቄ የለም። ያምናሉ። አስተውሉ።

244 አሁን፡ ቃሉ ሰላለ እንደሚሆን ያውቅ ነበር። ስለ እርሱ የተጻፈው ቃል ሁሉ መፈጸም ነበረበት። እንዲህ እንደሚያደርግ አስቀድመው ትንቢት በተናገሩት በቅዱሳን ነቢያት አማካኝነት፡ በእግዚአብሔር ኃይል የተጻፈ መሆኑን ያውቅ ነበር።

245 ትንቢት ደግሞ ፈጽሞ አይወድቅም። ሊወድቅ አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል ሊወድቅ አይችልም። እሱም... በመንፈስ ተጽፏል... አሁንም፡ ደግሞ፡

ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ያ መንፈስ፡ በእናንተ ማንነት፡ በሰውነታችሁ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፡ እርሱ ለሚሞተው አካላችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል። እንግዲያውስ፡ ተኩሱት፡ አቃጥሉት፡ የፈለጋችሁትን አድርጉበት፡ አላግጡበት፡ አፍርሱት፡ አቃሉት፡ የፈለጋችሁትን አድርጉ። እግዚአብሔር እንደሚያስነሳው ተናግሯልና፡ ያስነሳዋል። እያንዳንዱም የእግዚአብሔር ቅዱስ ያ ተስፋ በውስጡ አለው፡ ይህም እውነት መሆኑን ያውቃል። ስለዚህ፡ አትፍራ፡ ወንድሜ፡ እኛ ቀድሞውኑ በትንሣኤ ውስጥ ነን።

246 ከመጨረሳችን በፊት፡ በመለወጥን ተራራ ተመልከቱ። ለውጥ፡ መለወጥ፡ በዚያ ላይ ሁላችንም ተወክለን ነበር። ዛሬ የምናየውን ተመልከቱ። ዛሬ የምናየውን ነገር፡ ይኸውም የእግዚአብሔርን ሕይወት የሚሰጥ ኃይል ብቻ አስተውሉ። ሁላችንም እዚያ ነበርን። የሞቱ ቅዱሳን፡ በሙሴ ተወክለው ነበር፡ ደግሞም ያ ትንሣኤ ነበረ፥ እንዲሁም የከበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበረ። አልሳዕ... ሙሴ፡ ኤልያስና፡ ኢየሱስ፡ ሁሉም በተራራው ላይ ቆመው ነበር፥ የሞቱ ቅዱሳን፡ የተነጠቁ ቅዱሳንና፥ የከበረው ኢየሱስ ነበሩ። ኦህ፡ ማይ!

247 ደህና፡ እናንተም... አንድ ሰው ሲናገር ሰምቻለሁ። እንዲህ ይላሉ፡ “እናንተ ሰዎች፡ አያችሁ፡ እንዲህ ያለ ኃይል ካላችሁ፡ ወጥታችሁ ምን ማድረግ እንደምትችሉ ለሰዎች መናገር ነበረባችሁ።” እንዲህ ያለ ነገር፡ ከእውነተኛ ክርስቲያን ይራቅ። አያችሁ? በእርግጥ፡ እኛ ምንም ኃይል አለን አንልም። የ...

248 ነገር ግን አንድ ነገር እናደርጋለን። ይህ ሁሉ ኃይል በላያቸው ላይ ሆኖ፡ ዙሪያቸውን ሲመለከቱ፡ “ኢየሱስን ብቻ አዩ።” እውነተኛ፡ ትክክለኛ አማኝ ደግሞ የሆነን የሃይማኖት ተቋም ስለመደገፍ፡ ወይም ስለ ምንም ነገር ግድ አይሰጠውም። እርሱ የሚፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ያም እናንተ ያንን የከበረውን ክርስቶስን እንድታዩ ነው፡ ልዩነት የሚያመጣው እርሱ ብቻ ነውና። እውነተኛው፡ ትክክለኛው የመለወጥ ተራራ ልምምድ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ያከብራል። ሙሴን አላከበረም፡ ኤልያስን አላከበረም፡ ራሳቸውንም አላከበሩም፡ ሌላ ምንም ነገር አላከበሩም፡ ነገር ግን የከበረውን ክርስቶስን አዩ። በማንኛውም እውነተኛ አማኝ፡ ልብ ውስጥ ያለውም፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር ነው። ሕዝቡም እንዲያዩት ለማድረግ የሚጥረው ያንን ነው።

249 “እንግዲህ፡ መጥታችሁ ቡድናችንን ብትቀላቀሉ፡ **ይህን** ወይም **ያን** ብታደርጉ፡” ማለት አይደለም። ኧረ፡ እንዲህ አታድርጉ። እንዲህ አታድርጉ።

250 የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን፡ ክርስቶስ፡ ሲከብር ተመልከቱ፥ በዚህ ታላቅ የትንሣኤ ሰዓትም፡ የዚህን ቀን ተስፋ ፈጽሙ። አስተውሉ። ይህም ከእርሱ ጋር መሆናችንን፡ ከሥጋው ሥጋ፡ ከአጥንቱም አጥንት መሆናችንን ማወቁ፡ ደስታን ይሰጣቸዋል። ምንኛ ደስታ ነው! እውነተኛ አማኝ ግድ የሚለው ስለዚሁ ነገር ብቻ ነው።

251 እነርሱ ስለ ቤተ እምነት ግድ የላቸውም። ስለ ድርጅትም ግድ የላቸውም። ሌሎች ሴቶች ስለሚያስቡትም ግድ የላቸውም። ግድ አይሰጣቸውም። በጭራሽ። እነዚህ ሌሎች ሴቶች... የሚያደርጓቸውን ነገሮች አያደርጉም። እነርሱ... እነዚህ ወንዶችም እነዚያን ነገሮች አያደርጉም። ከድርጅት እንዳይባረሩ በመስጋት ወይም የምግብ ዋስትና እንዳያጡ በመፍራት፡

ከአንድ ድርጅት ጋር ተጣብቀው፡ አያኅበድዱም። ለእነዚህ ነገሮች ግድ የላቸውም። ለእነርሱ እነዚህ ነገሮች ከንቱ ናቸው።

252 አንድ የልብ መሻት ብቻ ነው ያላቸው፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሮ ማየት ነው። አኗኗራቸው ከእግዚአብሔር ጋር መሆን አለበት። ከኢየሱስ ክርስቶስ ክብር በቀር፡ ሌላ ምንም፡ መሆን የለበትም። ኢየሱስስ ምንድን ነው? ቃሉ ነው። ልክ ነው? አሁን፡ አስተውሉ፡ ያንኑ የተረጋገጠውን መንገዱን ማየት፡ ትንሣኤውን ያረጋግጣል። አሁን ምንድነው? እንዲህ ባለው ተስፋ በተገባው ቃል፡ ህይወታችሁን ማየት፡ "እርሱ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡" አሁንም ሕያው መሆኑን ያረጋግጣል።

253 በአገሪቱ ያሉ በሮች ሁሉ ቢዘጉብኝ አይገደኝም። ያ፡ እ... ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት፡ በቀደም፡ ሃምሳ-ስድስት ዓመቴን ይዣለሁ። ቅጽበት ልወስድ እችላለሁ። በልብ ድካም ዕድሜ ክልል ውስጥ ነኝ። በእነዚህ በሌሎች ዘመናት ሁሉና፡ በሌሎች ነገሮች ውስጥ ነበርኩ። ታዲያ፡ ምን ለውጥ አለው? ሕፃን በነበርኩበት ጊዜም ቢሆን ግድ አልነበረኝም። አሁንም በየትኛው ሰዓት ብጠራና፡ ካርዴ ከመደርደሪያው ቢመዘዝ ተራዬም ቢደርስ፡ ምንም ለውጥ አያመጣብኝም። በዚህች ምድር ላይ እንደኖርኩ እንኳ ባያውቁ ግድ የለኝም። ለእኔ ምንም ለውጥ የለውም። እዚህ ምድር ላይ እንደነበርኩ የሚገልጹ ትላልቅ ሐውልቶችና ሕንፃዎች ሊኖሯቸው አይገባም።

254 ሰዎች እንዲያውቁት የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህም "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን" ነው። በልቤ ውስጥ የእርሱን ማረጋገጫ ይዣለሁ። አንድ ቀን... ምንም እንኳ፡ በባሕር ውስጥ ብሰጥም። አፍሪካ ውስጥ ልገደል እችላለሁ። ምን እንደሚደርስብኝ አላውቅም። ነገር ግን አንድ የማውቀው ነገር አለ፡ ማረጋገጫውን ይዣለሁ። ሃሌሉያ! በሮች ሁሉ ሊዘጉ ይችላሉ። ያ ለእኔ ቅንጣት ታህል ልዩነት የለውም። የሆነን ሰው ወይም ድርጅት፡ ወይም እራሴን፡ ወይም ከቡድኖቼ አንዳቸውን፡ ወይም ሌላ ምንም ነገር ለማክበር እየሞከርኩ አይደለም። ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳና፡ መንፈሱም ሕያው መሆኑን እንዲያዩ እፈልጋለሁ። "እርሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።"

255 ኢየሱስ፡ "አትፍራ። ሞቼም ነበርኩ፡ እነሆም ለዘላለም ሕያው ነኝ፡" ማለቱ ምንም አያሰደንቅም።

256 "ምክንያቱም አሁን በእርሱ ተቤዥተናል፡ ከእርሱም ጋር ተነስተናል፡ አሁንም (ወደፊት ሳይሆን) በእርሱ በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል።" አሁን፡ ይህ መንፈስ በእኛ ውስጥ ሲኖር፡ ያ የባለቤትነት ማረጋገጫ፡ እዳዎች ሁሉ እንደተሰረዙ ያሳያል። ምን? ክርስቶስ ሕያው ነው። **እኔ** አይደለሁም የምኖረው፥ **እኔ** አይደለሁም። "ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ይኖራል።" **እናንተ** አይደላችሁም የምትኖሩት፡ ነገር ግን ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ይኖራል፥ ምክንያቱም የእርሱ ሕያው ቃል በእናንተ ውስጥ ይኖራልና፡ ይህም የሜቶዲስት፡ የባፕቲስት፡ የጴንጤቆስጤ ሐሳቦቻችሁና፡ ሌላውም ነገር ሁሉ፡ እንደተሰረዘ እንደተደመሰሰ ያሳያል። ኢየሱስ ክርስቶስም...

257 ልክ በገለጥ ተራራ እንደነበረው፡ ነቢያትና ሌላው ነገር ሁሉ ተጠናቅቋል። የሉተራን፡ የሜቶዲስት፡ የፕሬስቢቴሪያን ዘመናት ሁሉ፡ ደህና ነበሩ፡ ነገር

ግን፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው። እርሱን ስሙት” ተባለ፡ ይህም የዚህ ዘመን ቃል፡ የማኅተሞቹ ዘመን ነው። በእነዚህ ዓመታት ሁሉ፡ ተሰውረው የነበሩት፡ ምስጢራት ሁሉ፡ ሲገለጡ... ያ ታላቁ የዘመን ፒራሚድ ተሰረዘ፡ የራስ ድንጋዩም፡ የዳዊት ኮከብ በሰፍራው እንዲያርፍ ተስተካከለ። የሕያው እግዚአብሔር ታላቋ ቤተ ክርስቲያን እንደ ንስር ክንፍ ትነሳለች፡ ወደዚያ ወደ ክብርም ትወሰዳለች። አዎን።

258 አሁን፡ አሁኑኑ፡ በሰውነታችን ውስጥ፥ በአዲስ ልሳን በመናገር፡ በትንቢትና፡ ወደፊት በማየት፥ በታመሙት ላይ እጅ በመጫንና፡ እነርሱም በመፈወሳቸው፡ ዓለምና፡ የዓለም ነገሮች ሁሉ፡ የሞቱ ናቸው። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል፡ አሁንም ኃይሉን ይዘናል። ሃሌሉያ!

በዚያ የትንሣኤ ማለዳ፡
የሞት ማኅተሞች ሲፈቱ፡
እንነሳለን፡ (ሃሌሉያ!) እንነሳለን። (አሜን!)

259 ይህ እንዳይሆን ሊያግዱን የሚችሉ በቂ አጋንንት በገሃነም ውስጥ የሉም። ለዚህ ዘመን በእግዚአብሔር አስቀድመን ተወስነናል። የእግዚአብሔር ቃል በእኛ በኩል ራሱን ይገልጣል። በእግዚአብሔር ቃል ተሰፋም፡ በእግዚአብሔር ፊት እንኖራለን። ከመነሳት ሊያግደኝ የሚችል አንድም ጋኔን በገሃነም የለም። በዚያች ማለዳ በፊቴ ሊዘጋው የሚችል፡ አንድም በር የለም። ማኅተሞቹ ተሰብረዋል። ሃሌሉያ!

260 እኔ ነጻ ነኝ። እኔ ንስር ነኝ። ከእንግዲህ በረት ውስጥ አይደለሁም፡ ነገር ግን ነጻ ነኝ። ከሙታን ተነስቻለሁ፡ ወደ አዲሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ገብቻለሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን፡ እዚህ የተቀመጣችሁ፡ በዚያ የእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላችሁ፡ እያንዳንዱ ወንድና ሴት፡ ወጣት ወይም ልጃገረድ፡ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ናችሁ። እናንተም ንስር ናችሁ።

261 ዛሬ፡ ሕያዋን ነን፡ የትንሣኤውንም ደስታ ለዘላለም እናጣጥማለን። እርሱ ሕያው ስለሆነ፡ እኛም ደግሞ፡ ሕያዋን ነን። እርሱም በውስጣችን እየኖረ፡ ሕያዋን ያደርገናል። እርሱን ከሙታን ያስነሳው ያ መንፈስ፡ በውስጣችን እያደረ፡ በዚያ ታላቅ የዘላለም ትንሣኤ ላይ ሟች ሰጋችንን፡ ሕያው ያደርገዋል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

262 ኦህ፡ ዓለምን ውሰዱ፡ የፈለጋችሁትን ማንኛውንም ነገር ውሰዱ፡ ኢየሱስን ግን ለእኔ ሰጡኝ። አሜን። እወደዋለሁ። ለእኔ፡ የዓለም ሁሉ ነገሬ ነው።

263 የእርሱ አካል ስለሆናችሁ፡ እኔ የእናንተ አካል ነኝ፡ እናንተም የእኔ አካል ናችሁ። በአንድነትም፡ የእርሱ፡ አካል ነን።

264 ኦህ፡ ክርስቲያን ሆይ፡ ምን ዓይነት ዕድል ነው ያለን! ቅዱስ ጳውሎስ ሊኖረው አልሞ እንኳ የማያውቀው ዕድል አለን። ሄኖክ፡ ኤልያስና፡ ሌሎች ሁሉ ያልነበራቸው ዕድሎች አሉን። አሁን ያለን ዕድሎች!

265 የሆነ ቦታ እዚያ ማዶ አንዲት ትንሽ በግ አለች፡ እርሷም ወደ በረቱ እስክትገባ ድረስ እርሱ አይረካም። በእግዚአብሔር እርዳታ፡ በራእይና፡ **በሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ወደ ባሕር ማዶ እመለሳለሁ። እስከማውቀው ሁሉ ድረስ፡ ያች የመጨረሻዋ ትንሽ በግ ምናልባት እዚያ ነፍስ

እንዳላቸው እንኳ በማይታሰብበት ሰፍራ ያለች፡ ጥቁር በግ ልትሆን ትችላለች። እግዚአብሔር ግን ሁሉን ያውቃል። እስከ ሕይወቴ የመጨረሻ ቀን ድረስ፡ የትም ብትሆን፡ ያቺን አንዷን ለመፈለግ እጥራለሁ።

266 እነዚህን ጥብቅ ነገሮች በመናገሬ ወንድሞቼን እንዳላስከፋሁ ተስፋ አደርጋለሁ። እኔ... ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድትሄዱ ስለማልፈልግ አይደለም። በእርግጥም፡ ቤተ ክርስቲያን እንድትሄዱ እፈልጋለሁ። በምትሄዱበት በማንኛውም ቦታ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ። ነገር ግን "እኔ፡ **የዚህ** አባል ነኝ፡ ወይም **የዚያኛው** አባል ነኝ፡" በማለት፡ ተስፋችሁን እዚያ ላይ ብቻ አታድርጉ። ኦህ፡ ወንድሜ፡ እህቴ ሆይ፡ የክርስቶስ ሁኑ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ፡ ነገር ግን የክርስቶስ ሁኑ። አሜን።

267 ያ—ያ መያዣ፡ በውስጣችሁ ከሌለ፡ አሁኑኑ ወደ ሕይወት ሕያው እንዲያደርጋችሁ ፍቀዱለት። አሁን አትቀበሉትምን?

268 ይህ ክፍል በእርሱ ተሞልቷል። በመላ ሰውነቴ ይሰማኛል። የእግዚአብሔር ኃይል፡ ታላቁ የራዕዮች ባለራዕይ፡ እዚህ እንዳለ አውቃለሁ፡ ነገሮችን ተናግሮ የማይወድቅበት ታላቁ ትንቢት ተናጋሪ፡ እርሱ ተናግሮ ማንም "አይሆንም፡" ሊለው የማይችል እርሱ ሲከፍት ማንም ሊዘጋ የማይችል ታላቁ እዚህ እንዳለ አውቃለሁ። ሞቶ የነበረው ሕያው የሆነው፡ ዛሬም፡ እዚህ ፊኒክስ ውስጥ፡ አዲስ-በበቀሉ አበቦች መካከል እየተመላለሰ፡ ሕያው ሆኖ ይኖራል።

269 በዚያ የትንሣኤ ማለዳ በእያንዳንዱ ሊሊና ጽጌረዳ አበባ ጉንጭ ላይ የጤዛ ጠብታዎች መኖራቸው፡ አያስደንቅም። ለምን? ከመሬት ውስጥ እንደወጣ ያውቅ ነበርና፡ የሆነ ቦታም ለዘላለም የሚፈካ አበባ አለ። አንድ ቀን ሰፍራውን ይይዛል። በትክክል።

270 የደስታ እንባ በጉንጮቻችን ላይ ቢፈስ፡ ምንም አያስደንቅም። ያንኑ ተመሳሳይ የለውጥ ኃይል ሲሰማን ልባችን መንቀጥቀጡ መርገብገቡ፡ በምንም አያስደንቅም እንዲያውም ከሰማይ በሚመጣ ቋንቋ እንድንናገር ሲያደርገን፡ ወደ ሕይወታችን በመምጣት ይሞላናልና።

271 እዚያ ወደ እርሱ መገኘት በጣም ሕያው ተደርገናል፡ ትንቢት መናገር፡ አስቀድሞ ማየት፡ ወደፊት የሚሆነውን መናገርና፡ ሁሉም ነገር ከቃሉ ጋር ፍጹም ይገጥማል። ከቃሉ ጋር የሚቃረን ትንቢት ከሆነ ግን፡ አትመኑት። ነገር ግን ከቃሉ ጋር የሚስማማ ከሆነ፡ ቀድመውኑ የተነገረ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው።

272 "አትፍራ። ሞቼ ነበርኩ፡ እነሆም ለዘላለም ሕያው ነኝ።" ይህ የእያንዳንዱን የዚህን ቃል ፊደል በልባችሁ ውስጥ የሚያትመው የእግዚአብሔር የትንሣኤ ማኅተም ነው። ማኅተሙ ምንድን ነው? "በሰው ሁሉ የተነበባችሁ፡ ደብዳቤዎች ናችሁ።" ያንን ታውቃላችሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር የራሱ ሲያደርጋችሁ፡ ከክርስቶስ ጋር እንደተነሳችሁና፡ አዲስ ፍጥረት እንደሆናችሁ፡ በትንሣኤው ማኅተም አትሞአችኋል።

273 ዛሬ ጠዋት ካልታተማችሁ፡ ራሳችንን ዝቅ ሰናደርግ እንዲሁ አድርጉ።

274 [አንድ ወንድም በሌላ ልሳን መናገር ይጀምራል። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—እርታዒ።]... ጌታ። ያንን ሰማችሁ?

275 አሁን ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ አስቡ። ሮሜ 8፡11፡ “ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው ያ መንፈስ በእናንተ ቢኖር፡ ለሚሞተው አካላችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።”

276 ሰዎች ሆይ፡ ወደ ፊት ምንድነው የምንጠብቀው? ምንስ ተረፈ? ፎርሞሳንና መላውን ዓለም ተመልከቱ። አቶሚክ ሚሳይሎችና ሌላውም ነገር ሁሉ ዓለምን ለመምታት ተዘጋጅተው ባለበት፡ ሰዎች በጣም ተጨንቀው፡ ፈርተውና፡ እየጮሁ ነው። እነዚህ የፊልም ተዋናዮች ደግሞ፡ እዚያው ሆነው፡ የተለያዩ ቀልዶችን ይቀልዳሉ፡ ልክ አንድ ትንሽ ልጅ፡ በሌሊት በመቃብር ሰፍራ ውስጥ እያፏጨ ሲያልፍ፡ ሁሉም ነገር ደህና መሆኑን ሰዎችን ለማሳመን እንደሚሞክረው ነው። አትታለሉ። የጌታ መምጣት በደጅ ነው።

277 በቀደም፡ አንድ ዓሣ አጥማጅ መጥቶ የነገረኝን፡ አስተውሉ፡ እዚያ ማዶ በባሕር ወሽመጥ ውስጥ፡ ይህም፡ የሆነ ወጣ ገባ ወይም መሰል ቦታ ላይ ተቀምጦ ነበር። ይህም፡ እንዴት፡ በግሪክ ያ የመሬት መንቀጥቀጥ ከመከሰቱ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ አብዛኛውን ጊዜ በዚያ የጠዋት ሰዓት የሚመገቡት ዓሦች ሁሉ፡ ሳይመገቡ እንዴት እንደቀሩ ነገረኝ። ምን ሆኖ ነበር? በውኃው ወለል ላይ አልነበሩም። ለሁለተኛ ጊዜም ሲከሰት፡ ያው ነገር ተደገመ። የሆነ ነገር ሊፈጠር እንደሆነ በዚያኑ ጊዜ አወቀ። ዓሦቹ በዚያ ሰዓት አይመገቡም ነበር።

278 በዓሦች የሚመገቡት የባሕር ወፎችና፡ ሌሎችም መመገባቸውን አቆሙ። በዚያ በማለዳ ነበር፡ የሚመገቡት። ከገደላገደልና ከመሳሰሉት ነገሮች ርቀው፡ በዳርቻው ላይ ዝም ብለው ተቀመጡ። ምክንያቱም፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ የባሕር አረም ከመሬት በታች፡ ከባሕሩ ወለል ላይ መፍላት ጀመረ። አያችሁ? ዓሦቹ ሳይከሰት በፊት ያውቁት ነበር።

279 ወደ ሕንድ ሰሄድ፡ ጋዜጣ ላይ፡ “የመሬት መንቀጥቀጡ ያበቃ ይመስላል” የሚል፡ አነበብኩ። ለቀናት ያህል፡ ትንንሽ ወፎች በድንጋያማው ውስጥ ወደሚገኙት ጎጆዎቻቸው አልተመለሱም ነበርና። ከብቶቹም በቀኑ ሙቀት ጊዜ... በጥላ ስር ባሉት መጠለያዎቻቸው ዙሪያ፡ አልቆሙም ነበርና። በጎቹ ሜዳው መሃል ላይ ቆመው፡ እርስ በርሳቸው ይደጋገፉ ነበርና። የመሬት መንቀጥቀጡ ከመከሰቱ ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በፊት ጀምረው፡ ወደ ድንጋዮቹ አቅራቢያ አልሄዱም ነበር።

280 ለምን? እነዚያ በጎች አውቀውት ነበር። የሆነ ነገር ሊፈጠር እንደሆነ ያውቁ ነበር። እነዚያ ወፎች የሆነ ነገር ሊፈጠር እንደሆነ አውቀው ነበር። እነዚያ የባሕር ወፎች የሆነ ነገር ሊፈጠር እንደሆነ አውቀው ነበር። እነዚያ ዓሦች የሆነ ነገር ሊሆን እንደሆነ አውቀው ነበር። እነዚያን እንስሳት ወደ መርከቡ የመራቸው ያው አምላክ ነው።

281 በመንፈስ-የተሞላችሁ ሕዝቦች ሆይ፡ የሆነ ነገር ሊሆን እንደሆነ፡ አይታያችሁምን? ዓለምን ጠራርጎ የሚያልፍ ታላቅ **የሆነ** ነገርን አትጠብቁ፥ ከጌታ ኢየሱስ መምጣት በቀር ሌላ ምንም የለም። አስታውሱ፡ የጌታን ቃላትና ተስፋ ብቻ አስታውሱ።

282 ፊጥናችሁ አትገቡም? ከእነዚያ ትልልቅ ግንቦች ራቁ። አሁን ትንሣኤው ቀርቧል። በዚያ ትንሣኤ ውስጥ እንደሚሄድ ያላወቀ ሰው እዚህ ካለ፡ ምናልባት የትንሣኤ ኃይል በውስጣቸው እንዳረፈ እርግጠኛ ያልሆኑ!

283 ምንም እንኳ ትሎች ይህን አካል ቢያጠፉት፡ አቶሚክ ቦምብ ላያችሁ ላይ ቢፈነዳ እንኳ፡ ያንን ሕይወት ሰጪ የሆነውን የትንሣኤን ኃይል፡ ፈጽሞ ሊያጠፉ አይችልም። አይ፡ በጭራሽ። እህቴ፡ ወንድሜ፡ ክቡር ስማችሁ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፏል። ማንም ሊያጠፋው አይችልም። በደሙ የተገዛውን ስምህን ከዚያ መጽሐፍ ለማጥፋት የሚያስችል፡ በቂ ማጥፊያ፡ በዓለም ውስጥ የለም።

284 ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ካልሆናችሁ፡ አሁን በዕድል ለመሞከር አ—አታድርጉ። እያችሁ? ሌላ ቦታ የታገደን የመንገድ ጥሰህ በማለፍ ሳትሞት ልትተርፍ ትችል ይሆናል፡ ይህንኛውን እገዳ ግን ጥሰህ አታልፍም። አይ፡ በፍጹም። ዋጋህን ታገኛለህ። ይህን ማድረግ አይጠበቅብህም። አሁን ቀይ መብራት እየበራ ነው። የራስህን ሀሳቦች ወደ ጎን በል፡ የዚህን ዓለም ነገሮችም ወደጎን በላቸው።

285 ኑ። በዚህ ታላቅ የትንሣኤ ሰዓት፡ በዚህ ታላቅ የትንሣኤ በዓል አከባበር ላይ አብረን እንነሳ። በዚህ ሳምንት በልባችሁ ልታከብሩት ትችላላችሁን? ካልቻላችሁ ግን፡ እስቲ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር አንሱ?

286 እንዲህ በሉ፡ "አምላክ ሆይ፡ ስለዚህ ነገር እርግጠኛ አይደለሁም። ይህን ሁሉ ማድረግ እችል እንደሆነም አላውቅም። ትረዳኛለህ? ጌታ ሆይ፡ እጄን ወደ አንተ አነሳለሁ። እርዳኝ።" እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ያ ጥሩ ነው። "ጌታ ሆይ፡ እ—እ—እሻሃለሁ። እርዳኝ። መ—መ—መነሳት እፈልጋለሁ። እ—እፈልጋለሁ። አሁኑኑ መያዣው እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ። ልክ መሆኑን ማወቅ እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ፡ ልክ መሆኑን ማወቅ እፈልጋለሁ። ምንም ስሕተት እንደሌለው፡ አውቃለሁ-... " ያኔ ምንም ዓይነት ስህተት አይገኝባችሁ። አይሆንም... ያኔ በጣም ይረፍድባችኋል። ቀኑ ዛሬ ነው። ኦህ! ቀኑ ዛሬ ነው። አትዘግዩ።

287 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ሰሰብክ ነበር። አንድ አረጋዊ ጥቁር ሰው ከህንጻው በስተጀርባ መጥቶ፡ አገኘኝ። እንዲህም አለኝ፡ "ሬቨራንድ፡ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ። አንተ ትክክል ነህ እላለሁ" አለ። አክሎም፡ "ከረጅም ጊዜ በፊት፡ ለጌታ ነግሬዋለሁ፡ በዚያች ማለዳ ቲኬቴ በእጄ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በትክክል ምልክት መደረጉን ማወቅ እፈልጋለሁ" አለ። "እዚያ ወንዙ ዘንድ ብዙ ችግር ይኖራል፡" አለ። "እ—እ—እኔም ወደዚያ ወንዝ፡ እወርዳለሁ፡" አለ። "እ—እዚያ ምንም ዓይነት ችግር እንዲገጥመኝ አልፈልግም። ሁሉንም ነገር እዚሁ ማስተካከል እፈልጋለሁ፡" አለ። በትክክል።

288 ቪዛችሁን ይዛችኋል? ቪዛ ከሌላችሁ... ፓስፖርት ሊኖራችሁ ይችላል፡ ነገር ግን፡ ቪዛ ከሌላችሁ፡ ወደ ምድሪቱ መግባት አትችሉም። ያንን ታውቃላችሁ። ሁሉንም ነገር አዘጋጅታችኋል? ካልሆነ፡ የምታደርጉበት ጊዜ አሁን ነው።

289 ትንሽ ከተሸበራችሁ፡ አትፍሩ። አሁን፡ እዚህ ውስጥ ወደ መቶ የሚጠጉ እጆች ተነስተዋል። ስለዚህ ትንሽ እንኳ ከፈራችሁ፡ አሁን ለነገሩ እልባት እንስጠው።

290 አሁን፡ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉን አውቃለሁ። አንዳንዶች፡ "ኑና፡ እጃችሁን ልጨብጣችሁ" ይላሉ። ሌሎች ደግሞ፡ "ኑና፡ በመሠዊያው ፊት ተንበርከኩ፡"

ይላሉ። እነዚህ ሁሉ ጥሩ ናቸው። በእነርሱ ላይ የምናገረው አንዲትም ቃል የለኝም፡ በፍጹም፡ እነርሱ በሚሉት በማንኛውም ነገር ላይ፡ ምንም የምለው የለም።

291 ነገር ግን የእኔን መንገድ ልንገራችሁ። “ያመኑ፡ ሁሉ… ” ወደ መሠዊያው መምጣት እንዲታምኑ አያደርጋችሁም። ከአገልጋዩ ጋር እጅ መጨበጥ እንድታምኑ አያደርጋችሁም። ነገር ግን በእግዚአብሔር የተጠራችሁና፡ ንስር ከሆናችሁ፡ ገና ከመጀመሪያው፡ ያ ጩኸት ይነግራችኋል። ታምናላችሁ። በእውነት ካመናችሁ፡ እኔ ከእናንተ ጋር እጸልያለሁ።

292 ያ ትንሽ ንስር በዚያ በረት ውስጥ ከእንግዲህ ይቆያል ብላችሁ ታስባላችሁ? አይ፡ አይ። ሃህ-ኡህ። አይ። ወዳጄ ሆይ፡ አንተም ከእንግዲህ እዚህ አትቆይ። አሁን በንጥቀት እ—እንነሳ። ይህን ለማድረግ የእግዚአብሔር ጸጋ እዚህ አለ።

293 የሰማይ አባት ሆይ፡ ወደ ፍጻሜው ሰዓት እየቀረብን መሆናችንን ተገንዝበናል። አሁን እዚህ የምንቆይበት ረጅም ጊዜ የለንም። እንደ ዕድሜያችን ሳይሆን፡ እንደ ዘመኑ ጊዜው ማለቴ ነው። እዚህ የተቀመጡ ብዙ ወጣቶች ይህ ሲሆን፡ በሕይወት ይኖራሉ ብለን እናምናለን። ዛሬውኑ እንኳ ሊሆን ይችላል። ደቂቃውን ወይም ሰዓቱን አናውቅም። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ፡ “እነዚህ ነገሮች ሲከናወኑ ስታዩ” ብለኸናል፡ እነርሱም አሁን ለረጅም ጊዜ እየተከናወኑ ነው።

294 እንደ ሳይንቲስቶች አባባል ከሆነ፡ ጊዜው በጣም አልፎብናል። ከስድስት፡ ወይም ከሰባት ዓመታት በፊት፡ እኩለ ሌሊት ለመሆን ሦስት ደቂቃ ብቻ ቀርቶን ነበር። ሰዓቱ እየቆጠረ፡ ስንት ሰዓት እንደሆነ አናውቅም፡ ነገር ግን ልክ እዚያ ላይ እንዳለን እናውቃለን።

295 አምላክ ሆይ፡ ማረጋገጫው እንዲኖረን፥ ልባችንም እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል “በአሜን” ሲያጸድቅ ለማየት፡ ወደ እኛ የገባው፡ ያ መንፈስ ራሱ፡ ማንነታችንን ሕያው ሲያደርገው ለማየት እንሻለን።

296 አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ወንድሞቼን ያንን እንዲያዩ አድርጋቸው። ወንድሞቼን፡ ያ መንፈስ መጥቶ ቃሉን ሕያው ሲያደርግ እንዲመለከቱ አድርጋቸው። ጌታ ሆይ፡ እህቶቼም ያንኑ እንዲያዩ አድርግ። ከዚያም፡ አምላክ ሆይ፡ ለዚያ ቃል ሕያው እንዳይሆኑ የሚያግዳቸውን ማንኛውንም ነገር ካዩ፡ በፍጥነት ያስወግዱት። አባት ሆይ፡ ይህንን ሰጠን። አሁን ሁሉም ነገር በእጅህ ነው። በብዙ ነገር እንደወደቅኩና፡ አሁንም እንደምወድቅ አውቃለሁ፡ ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ የማውቀውን ሁሉ አድርጌያለሁ። አሁን ግን በእጅህ ነው። ያንተ ናቸው። አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ስም፡ ተቀበላቸው።

297 አሁን ደግሞ እዚህ ላላችሁና ለአካላችሁ ፈውስ ለሚያስፈልጋችሁ። ስንት አማኞች አላችሁ? እጃችሁን አንሱ። “እስከማውቀው ድረስ፡ በልቤ አማኝ ነኝ።” ስንቶቻችሁ ያንን ይዛችኋል? ያለምንም ጥርጥር፡ አሁኑ፡ በልባችሁ፡ ከሙታን እንደተነሳችሁ፡ ታውቃላችሁ? ታውቃላችሁ? ኡህ፡ ማይ! ታዲያ እንዲህ ባለ ስብሰባ ላይ ምን ሊፈጠር ይችላል? እርፍጅያለሁ፡ ነገር ግን አሁኑ ምን ሊሆን ይችላል? ምን ሊሆን እንደሚችል እስቲ አስቡ። መያዣው ልክ በውስጣችሁ ይገኛል። አያችሁ? እናንተ፡ እጃችሁን ያነሳችሁት፡ ለእግዚአብሔር፡ መ—

መሐላ እንደገባችሁ ነው፡ ይህም፡ “አንድ ነገር እንደሆነልኝ አውቃለሁ። መሆን የሚገባኝ ቦታ ላይ ባልሆንም እንኳ” እንዳላችሁ ነው።

298 እኔም ቢሆን አልደረስኩም። አይ፡ ጌታዬ። መሆን ከሚገባኝ ቦታ ገና ብዙ እቀራለሁ። ነገር ግን ይህንን አንድ ነገር አውቃለሁ፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሬያለሁ። የሆነ ነገር እንደሆነልኝ አውቃለሁ። ብዙ... አሁን እንደ ሽማግልነቴ ሳይሆን፡ ከብዙ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ነው፡ የሆነው።

299 ያንን ቀን አውቃለሁ፡ ያ **ታላቅ** ፈተና በገጠመኝ ጊዜ፡ ወደዚያ ሆስፒታል የገባሁበትን፡ ባለቤቴ ስትሞት አይቻለሁ፡ እኔ ግን ለሕይወቷ እጮህ ነበር፡ “ከመንገድ ዳር ቆሜ ከመሰበክና፡ ለታመሙት ከመጸለይ በቀር ምን አደረግሁ? ”

በዚያን ጊዜ ሰይጣን፡ “እንግዲህ፡ እርሱ ጸሎትህን አይሰማም” አለኝ።

300 ስትሞት አይችያታለሁ፡ ነገር ግን በውስጧ ያ የትንሣኤ ኃይል እንደነበረ አውቃለሁ። እነዚያ አጥንቶች እንደገና ይነሳሉ።

301 ትንሿ ልጄ እዚያ ተጋድማ አየኋት። እጄንም በላዩዋ ላይ ጭኜ፡ “አምላክ ሆይ፡ አትውሰዳት፡” አልኩ።

302 መጋረጃውን የዘጋውና፡ “ከእንግዲህ አልሰማህም፡” ያለ ይመስል ነበር።

303 ሰይጣንም እንዲህ አለ፡ “ይሄውና። አንዲት ቃል ብቻ... ” እግዚአብሔር የለም ቢለኝ እንደማልቀበለው ስለሚያውቅ፡ ያንን አላለኝም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አይወድህም፡ ስላንተ ግድ የለውም አለኝ። አያችሁ? በሁሉም ምክንያታዊ ነገር ላይ ተነሰቶ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አንተ ገና፡ የሃያ ዓመት ወጣት ነህ። ሚስትህ እዚህ የሬሳ ክፍል ውስጥ ተኝታለች። ልጅህም ወደዚያው እየሄደች ነው። ደ——ደግሞም... አንተ እርሱ ታላቅ ፈዋሽ ነው፡ እርሱ **ይህ** ሁሉ ነገር ነው ትላለህ። እሰቲ፡ ተመልከት፡ እርሱ ምን ያደርጋል? አንዲት ቃል እንኳ መናገር ሳያስፈልገው፡ ወደ ታች ብቻ ብመለከት ይበቃ ነበር። ራሱን ብቻ ቢነቀንቅ፡ ይበቃ ነበር፡ ፈውሱም ይከናወን ነበር። ነገር ግን፡ አየህ፡ እርሱ አይወድህም። ስላንተ አያስብም። በዚህ ጨለማ ሰዓት ጸሎትህን መስማት እንኳ እንቢ ብሎ፡ ልጅህን እንድትሞት እየተዋት ነው” አለኝ።

304 የተናገረው ነገር ሁሉ ፍጹም እውነት ነበረ። “ታዲያ ምን አተረፍክ? ቀኑን ሙሉ፡ መቆም እስኪያቅትህ ድረስ ትሠራለህ። ሌሊቱን ደግሞ፡ እስከ ስድስትና ሰባት ሰዓት ድረስ አትተኛም። በመንገድ ዳር ቆመህ፡ ትሰብካለህ። ወደ ሆስፒታል ትመላለሳለህ። ቤት ገብተህ፡ ወንበር ላይ፡ ለአንድ ሰዓት ወይም ለሁለት ሰዓት እንቅልፍ ትወስድና፡ እንደገና ወደ ሥራ ትሄዳለህ። በቀጣዩም ሌሊት፡ ያው ነው። አሁን ደግሞ፡ እነሆ ዕድሜህ ሃያ-አንድ፡ ሃያ-ሁለት አካባቢ ነው። የምታውቃቸው ጓደኞችህ፡ ወጣት ወንዶችና፡ ሴቶች ሁሉ፡ እብድ ይሉሃል። ምን አደረግህ? ራስህን ሞኝ አደረግህ። አይታይህምን? ” እኔም ከእርሱ ጋር ለመስማማት ተቃርቤ ነበር።

305 ነገር ግን በውስጤ ያለ የሆነ ነገር፡ ያ ሕያው የሚያደርግ ኃይል ነበረ። እንዲህም አልኩ “ጌታ ሰጠ፡ ጌታም ነሳ። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን።”

ተስፋዎቼ ሁሉ ሲፈርሱ፡
ብቸኛ ተስፋና ድጋፌ እርሱ።

በክርስቶስ ላይ፡ ያ...
[በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—እርታዒ።]... የሚያሰምጥ
አሸዋ ነው።

እነሆ፡ በድል ድምፅ ይመጣል፡
ያኔ በእርሱ ው—ውስጥ እገኛለሁ፡
በጽድቁ ልብስ እጎናጸፋለሁ።

306 በራሴ ጽድቅ አይደለም፥ እኔ ምንም የለኝም። የእኔማ እንደ ረከሰና፡ እንደ ቆሸሸ ጨርቅ ነው። በሰብከቴ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት መሞከርን አልመኝም። በራእዮቼም ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ አልሞክርም። ወደ መንግሥተ ሰማያት የምሄደው የእርሱን ጸጋ በልቤ ስለያዝኩ ነው። ጸጋው፡ ለዚያ ነው የምሄደው። የምንሄደውም በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

307 ኦህ፡ ወዳጆቼ፡ እናንተ የዚህ አካል ክፍል ናችሁ። እናንተ የእግዚአብሔር ትናንሽ ልጆች ናችሁ። አሁን፡ ይህንን የምናገረው ተሰፋችሁን ለመገንባት ነው። ካገኛችሁ...

308 በእናንተ ዘንድ ሞገስን ካገኘሁና፡ እውነቱን ከነገርኳችሁ... የነገርኳችሁም፡ ከዓመታት በፊት፡ ነ—ነቢዩ የተናገረውን ነው። ራሴን የእርሱ ነቢይ እያደረግኩ አይደለም። አይ፡ ወዳጄ። ነገር ግን እውነቱን እየነገርኳችሁ ነው። እርሱ ትክክል ከሆነው ነገር ውጭ ሌላ ተናግሮ ያውቃልን? እዚህ ፊኒክስ ውስጥ፡ ለሃያ-ዓመታት ያህል፡ አውቃችኋለሁ፡ **ከእርሱ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ፡** ከሚለው ዝማሬ ጊዜ ጀምሮ፡ በወንድም አውትላው፡ እና ወንድም ጋርሲያ ቤተ ክርስቲያን፡ እንተዋወቃለን። እስካሁን በጌታ ስም ተናግሬ ሳይፈጸም የቀረ ነገር ተናግሬ አውቃለሁን?

309 አስታውሱ፡ ያለው አንድ ተስፋ ብቻ ነው። ይህንን ሕይወት የሚሰጥ ኃይል ይኑራችሁ። እርሱ ይይዛችኋል። ሌላው ነገር ሁሉ ሲፈርስ፡ እርሱ ደግፎ ይይዛችኋል።

310 አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ አንተ ሃይማኖትህን ጠበቀሃልን" ሲሉኝ?

እኔም፡ "አይ፡ እርሱ ነው እኔን የጠበቀኝ" እላቸዋለሁ።

311 ጠበቀኝ። እኔ አልጠበቅኩትም። የእኔ መጠበቅ፡ ወይም አለመጠበቅ አይደለም። እርሱ እኔን አመጠበቁ፡ ወይም አለመጠበቁ ነው። የያዘልኝ እርሱ ነው።

312 እንዲህ ማድረግም አልነበረበትም። በእያንዳንዱ ዛፍ ላይ መላእክት ተዘጋጅተው ነበር፡ እንዲህም ይሉ ነበር፡ "ዝም ብለህ ጣቶችህን ብቻ ፍታ። እንዲሁ ብቻ ጠቁም፡ ከመስቀሉ ላይ መውረድም አይጠበቅብህም። እንዲሁ በጣትህ ጠቁምና፡ ምን እንደሚሆን ተመልከት።" እያችሁ፡ ያ የሚያፌዙ ሰብሰብ። ነገር ግን ያንን አድርጎ ቢሆን ኖሮ፡ ዛሬ ይህ ምስክርነት አይኖረኝም ነበር፥ እናንተም አይኖራችሁም ነበር። ነገር ግን እርሱ በመስቀል ላይ ስለጸና፡ በዚያ ስለቆየ ነው፡ እኔም ከእርሱ ጋር የጸናሁት።

በክርስቶስ፡ በጸናው ዓለት ላይ፡ እቆማለሁ፥
ሌላው ሁሉ የሚሰምጥ አሸዋ ነው።

313 አሁን፡ የታመማችሁ ካላችሁ፡ እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁን ተጫጫኑ። እንጸልይ። አጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ እጆቻችሁን ጫኑ። ችግራችሁ ምንም ይሁን ምን፡ አሁን እምነት ይኑራችሁ። እውነቱን ነግሬያችሁ የማውቅ ከሆነ፡ አሁንም የምነግራችሁ ያንኑ ነው። እያችሁ? ኢየሱስ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል" ብሏል። እናንተም አማኞች ናችሁ፡ አሁኑኑ እጆቻችሁን አንስታችኋል። አትጠራጠሩ። እጃችሁን የጫናችሁበት ምስኪን የሚሰቃይ ሰው አለ። በናንተም ላይ እጁን የጫነ ሰው አለ።

314 ያንን ሕያው የሚያደርግ ኃይል፡ ኢየሱስን ከመቃብር ያስነሳውን ያንን ኃይል አስታውሱ። አሁን በ—በገዛ ሰውነታችሁ ውስጥ ባለው ነገር ላይ እምነት ይኑራችሁ። እጃችሁን ለጫናችሁበት ሰው እርዳታ ይሆንለታል። "እርሱ በእናንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፡ ለሚሞተው አካላችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።"

315 ውድ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ሰቆም፡ ወደ ቀትር ሰዓት እየተቃረብን ነው፡ ኢየሱስ፡ "አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውኸኝ? ተጠማሁ" ብሎ በጮኸበት ልክ በዚህ ሰዓት ላይ ነበር። ነቢዩ አስቀድሞ ተመልክቶ፡ "አጥንቶቼ ሁሉ፡ ተመለከቱኝ። እጆቼንና እግሮቼንም ወጉኝ፡" ማለቱ፡ ምንም አያስደንቅም። "ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጠረ። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ። ስለ በደላችንም ደቀቀ። የሰላማችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።" አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይህንን የእኛ መሆኑን እናውጃለን። ይህንን እንቀበላለን።

316 በዚህ የትንሣኤ ማለዳ፡ ጌታ ሆይ፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ከቃልህ እንደነገርኳቸው፡ ይህንን የተረጋገጠ እውነት፡ ቁጠርልኝ። እርሱ ፈራጅ ነው፡ እኛም እርሱ እንደተቤዠን ምስክሮች ነን። በእኛም ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ የትንሣኤው ኃይል አለ። እነሆ እጆቻችንም የጫንባቸው፡ እነዚህ ጓደኞቻችንም ታመዋል።

317 አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት በእምነታችን መካከል ሆነን፡ ዲያብሎስን እንገዳደረዋለን፡ እጆቻችን በሕዝቡ ላይ ተጭነው፡ እኔም እጆቼን በሕዝቡ ላይ ዘርግቼ። ሕዝቡን አጥብቆ ለመያዝ የሚሞክር ማንኛውም በሽታ፡ ማንኛውም ደዌ መከራ፡ በዚህ በተረጋገጠ እውነት መገኘት፡ ውጣ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ እነዚህ ሰዎች ዛሬ ነጻ ይሁኑ። ይህም፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የአምላካችን ቃል፡ "እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ" ብሏልና። አምላክ ሆይ፡ እጆቻችንም ወደ አንተ፡ ወደ ላይ ተዘርግተዋል።

318 የምድር ተክሎች ሁሉ ከምንጭህ እንደሚጠጡ፡ የበቀለው ተክልም፡ ከምንጭህ ሲጠጣ፡ በእርግጠኝነት መታነጽ፡ መጽናት እንደሚጀምር ነው። ማደግም ይጀምራል። የበቆሎ አገዳው፡ አበባው፡ ከምንጭህ የሚጠጣው ማንኛውም ነገር፡ ወደ አንተ ያድጋል።

319 ዛሬ ጠዋት፡ ጌታ ሆይ፡ ስንዝር ያክል፡ አድገናል። ይበልጥ ወደ ላይ መድረስ እንችላለን። ከምንጭህ እየጠጣን ነው። ጌታ ሆይ፡ በውስጣችን የትንሣኤ ኃይል ያለብን፡ ያንተ ፍጥረቶች ነን። ስለ ወንድሞቻችንና ስለ እህቶቻችን ጸሎታችንን ትስማ ዘንድ እንጸልያለን። ይህ ኃይል ያላቸውን፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ውድ

ሕዝቦች የሚያደናቅፍ ደዌ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ፥ ይልቀቃቸው። ጌታ ሆይ፥ ሁሉም መልካም ይሆናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

320 ታምኑታላችሁን? እንዲህ ያለውን ነገር ትታችሁ መሄድ ትችላላችሁን? እንዴት ትችላላችሁን? ራሳችሁን፥ በግድ ማራቅ ያለባችሁ ነው፥ የሚመስለው። እንዲህ ይሰማችኋል? እ—እ—እኔ... ምናልባት እኔ ብቻ፥ ልሆን እችላለሁ... ነገር ግን እንደዚህ በአንድነት በተቀመጣችሁበት ሕዝብ መካከል ሰመጣ፥ አንድ እንግዳ የሆነ፥ ስሜት ተሰማኝ። የማይታይ ሆኖ፥ የሆነ ቦታ፥ የማይታይ ሆኖ፥ ልክ እንደ ሬዲዮ፥ ወይም ቴሌቪዥን ሞገድ፥ ብቻ ምንም ይሁን፥ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደሚያልፍ ሁሉ፥ ክርስቶስ በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳለ አውቃለሁ። እስቲ ቤዛችንን አሰቡ! ቶኒ፥ እርሱ እዚህ አለ። አሜን።

321 የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ሲፈጸም የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በውስጣቸው ካላቸው፥ መላእክትንና የእርሱን መገኘት፥ በየዘመናቱ እንዳዩት ዛሬም ከሚያዩ ሰዎች፥ ይ—ይበልጥ ደስተኛ ማን ሊሆን ይችላል! እነሆ፥ የሚያዩ ሰዎች ቃላት፥ ትንቢት ተነግሯል ልክ እንደተባለውም ተፈጽመዋል። እኛም ዛሬ በመምጣቱ ዋዜማ ላይ እንገኛለን። ኦህ፥ ምንኛ አስደሳች ጊዜ ነው!

322 እናየዋለን። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፥ እርሱ እዚህ ይሆናል። እርሱ እስኪመጣ ድረስ፥ ትጸልዩልኛላችሁ? [ጉባኤው፥ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ከፊቴ አደገኛ ፈተናዎች አሉ። አውቀዋለሁ። እያችሁ? ውሃ እንደመጠጣት፥ በቀላሉ ሕይወታችሁን ሊያጠፉ ከሚችሉ አረማውያን ጋር እገናኛለሁ፥ ሕይወታችሁም በቀላሉ ያልፋል። ወደ እነርሱ ግዛት ትሄዳላችሁ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በቀላሉ፥ የሚገዳደሩ አጋንንት ያጋጥሟችኋል። ነገር ግን አምላካችን ድል ያልነሳበትን ጊዜ አይቼ አላውቅም። እኔ የምሄደው በስሙ ነው፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፥ እርሱም የዘላለም ሕይወት ተስፋ፥ ትንሣኤና ሕይወት ነው። "ሕያው የሆነ በእኔም የሚያምን፥ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። በእኔ የሚኖርና የሚያምንም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" ይህ የእግዚአብሔር የዘላለም ቃል እንደሆነ አምናለሁ። እናንተም ያንኑ ታምናላችሁ? ["አሜን።"] ትጸልዩልኛላችሁ? ["አሜን።"] እኔም እጸልይላችኋለሁ። ዳግመኛ እስክንገናኝ ድረስ እግዚአብሔር ይጠብቀን።

323 አሁን ለአንድ አፍታ በሁለት እግራችን እንቁም። (የምትሉት ነገር አለ? )

ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

324 ይህችን ትንሽ መዝሙር ባንዘምር ስህተት ይሆንብናል፥ አይደል? **እወደዋለሁ** የሚለውን፥ መዝሙራችንን አስታውሱ፥ በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ አለ አይደል? እስቲ እንዘምረው። ውድ፥ እህቴ፥ ከቻልሽ... እህቴ ሆይ፥ ስለ ምትጫወችው ነገር፥ ላመሰግንሽ፥ እወዳለሁ። መልካም።

እወደዋለሁ፥ እወደዋለሁ
እርሱ አስቀድሞ ወዶኛልና
በቀራንዮ መስቀል ላይ
መዳኔን ገዝቶልኛልና።

አሁን መዝሙሩን እንቀይራለን።

እምነቴ ወደ አንተ ትመለከታለች፥

አንተ የቀራንዮ በግ፡
መለኮታዊ አዳኝ፥
አሁንም ስጸልይ ስማኝ፡
ኦህ፡ በደሌን ሁሉ አስወግድልኝ፡
ኦህ፡ ከዛሬ ጀምሮ
እኔ ፈጽሞ ያንተ ልሁን!

325 ይህ በውስጣችሁ የሆነ ነገር አይፈጥርም? ከልብ የመነጨ እንዲህ ያለ ነገር... የ—የ—የኢዮቤልዩ ዝማሬዎችን እወዳለሁ። በእርግጥኝነት፡ እወዳለሁ። ነገር ግን በአምልኮ መንፈስ ውስጥ ስትሆኑ፡ እነዚያን ጥንታዊና ጣፋጭ መዝሙሮች አትወዱም? መንፈስ ቅዱስ በኤዲ ፔሮኔትና እነዚያን ታላላቅ ጥንታዊ መዝሙሮች በጻፉት ላይ ይንቀሳቀስ እንደነበረ አምናለሁ። ይህን አታምኑም? ፋኒ ክሮስቢ፡ እንዲህ ስትል እንደጻፈችው፥

ኢየሱስ፡ ሆይ፡ አትለፍብኝ
ትጸሎቴን ስማኝ፥
ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ፡
አትለፍብኝ።

አንተ የመጽናናቴ ምንጭ፡
ከሕይወት ትበልጣለህ፡
ከአንተ ሌላ ማን አለኝ?
በሰማይ ሆነ በምድር?

326 ይህ አስደናቂ አይደለም? **እወደዋለሁ** የሚለውን መዝሙር እንድንዘምር ያደርገናል፡ አይደል? አሁን፡ **እወደዋለሁ** የሚለውን መዝሙር በምንዘምርበት፡ በዚህ ጊዜ... እርስ በርሳችን እንዋደዳለን። እርስ በርሳችን ካልተዋደድን፡ እርሱን ልንወደው አንችልም። አሁን እርስ በርሳችን እጅ እንጨባበጥ። ዝም ብላችሁ ቁሙና፡ ጠረጴዛውን ተሻግራችሁ፡ እጅ ለውጅ፡ ተጨባበጡ።

እኔ... (... ? ... )
መዳኔንም ስለገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

አሁን ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

327 ወንድም ዊልያምሰን እጋብዛለሁ፡ወጣቱ ወንድም ዊሊያምስ፡ ለአፍታ ወደዚህ እንዲመጣ እጠይቀዋለሁ። ይህንን ጉባኤ በጸሎት እንዲያሰናብት እጠይቀዋለሁ።

328 ወጣት ክርስቲያን የሆነውንና፡ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ነው ብዬ የማስበውን፡ ወንድም ዊሊያምሰንና፡ ትንሹን ቤተሰቡን እወዳቸዋለሁ። ከእነዚህ ጋር ብዙ ኅብረት አለኝ። ከእነዚያ ውድ የሞዝሌይ ልጆችና ከሁላቸውም ጋር፡ አብረን ነበርን፡ እንዲሁም እዚህ ፊኒክስ ውስጥ፡ በሙሉ ልቤ የምወዳቸው ብዙ የልብ ጓደኞች አሉኝ። በዚያን ዕለት ጠዋት፡ በዚያ ራእይ ውስጥ፡ “እስከ ዛሬ የወደድካቸውንና፡ የሚወዱህን ሁሉ፡ እግዚአብሔር ለአንተ ሰጥቶሃል፡” ያለኝ ይመስለኛል።

329 እዚህ መሬት ላይ ወድቃ የምታለቅስ፡ ከኃጢአቷ ንስሐ የምትገባ፡ አንዲት ወጣት ሴት እንዳለች አምናለሁ።

ለአንድ አፍታ ለእርሷ ራሳችንን ዝቅ አድርገን እንጸልይ።

330 ውድ አምላክ ሆይ፡ ይህች በፊኒክስ የቀረችው ያቺ ትንሿ በግ ናት? አምላክ ሆይ፡ እኔ አላውቅም። አንተ ግን ታውቃለህ። ነገር ግን፡ አንድ ቀን፡ ይሆናል። አባት ሆይ፡ ይህች፡ ግን እንዷ መሆኗ፡ አያጠራጥርም። ስለዚህ አሁኑኑ፡ እንድትረዳት እጸልያለሁ። በሩን በቸርነት ከፍተህ፡ እንዲህ በላት፡ "ልጄ ሆይ፡ ነይ። ከደከመውና፡ ከዛለው መንገድ ተመለሺ። እዚያ በጨለማው ውስጥ ስትሰናከዪ ነበርሽ። ዛሬ፡ አንቺን ለመውሰድ፡ ወጣሁ። አሁን እያናገረሽና ወደ በረቱ እያመጣሽ ያለው የእኔ መንፈስ ነው።" አምላክ ሆይ፡ ይህንን አድርግላት። በሕይወት አፋፍ መንታ መንገድ ላይ ላለችው... ለዚህች ወጣት። "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።" ውድ አምላክ ሆይ፡ ለዚህች ወጣት ክርስቲያን፡ ይህንን ስጣት። "ወደ እኔ የሚመጣውን፡ ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም።" ቅዱሳኑ በወጣቷ ዙሪያ ቆመው፡ እየጸለዩ ሳለ።

331 ጳውሎስ እንኳ ሳይቀር፡ ለሞት እስኪቃረብ ድረስ፡ ክፉኛ በድንጋይ ተወግሮ ሳለ፡ ቅዱሳኑ በእርሱ ዙሪያ ቆመው በጸለዩ ጊዜ፡ ሕይወት እንደተመለሰች አስታውሱ። ምክንያቱም፡ በእነዚያ ቅዱሳን አካላት ውስጥ የሕይወትን መንፈስ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ የመለሰው ሕይወት ሰጪው ኃይል ነበረ። አምላክ ሆይ፡ በእርግጥ በእምነት ጸሎት፡ ሞትን... ወይም ሞትን ከሰውየው ውስጥ በማስወጣት፡ ወደ ሕይወት፡ መመለስ ይቻላል። ውድ አምላክ ሆይ፡ ይህንን ስጠን።

332 አንተን በምንጠባበቅበት በዚህ ጊዜ ባርከን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንጸልያለን።

333 አሁን ራሳችሁን ዝቅ እንዳደረጋችሁ፡ ወንድም ዊሊያምስን እጋብዛለሁ።

65-0410 የትንሣኤው ማኅተም
ራማዳ Inn
ፊኒክስ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org